የ ጫ ት
ኢ ኮ ኖ ሚ

**ቆይታ**
ከዶ/ር ግርማ ጌታሁን
ጋር

**ፖለቲካዊ ሙስና**
“ትላልቅ ሙሰኞች” እና
“የፀረ ሙስና ትግሉ” ፈተናዎች

ወርሃዊ
መጽሔት

# ውይይት

#Weyeyet

የምክንያታዊነት ድምፅ

ውይይት 2ኛ ዓመት|ቁጥር 15|መስከረም 2010|ዋጋ 13ብር



# እሳትን ማዳፈን ወይስ እውነቱን መጋፈጥ?




# መልካም
# አዲስ ዓመት
# ይሁንልዎ!

ሐሳብ
**የሕዝብ ብዛት በረከት ወይስ መርገም?** ገጽ 6 - 8

ሐሳብ
**ማኪያቬሊያዊ ፖለቲካ እና መዘዙ** ገጽ 11 - 12

ሐሳብ
**ወይ አዲስ አበባ....!** ገጽ 14 - 17

**"[ቋንቋ] ሀገራዊ ስሜትን ለመፍጠር ያለው ችሎታ ሀገርን ለመበተንም ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል"**
*ዶ/ር ግርማ ጌታሁን*



ገጽ 18 - 22

ውይይት
**የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ እንደ አውሮፓዊው አቻው ለምን ዘመናዊ ማኅበረሰብን መፍጠር ተሳነው? (፫)** ገጽ 23 - 25

ትኩሳት
**ቂሊንጦ ለምን ተቃጠለ?** ገጽ 26 - 28

የአገር ነገር
**እውነትም መጪው ዘመን የኢትዮጵያ ከፍታ ነው!** ገጽ 29 -30

ጤና|አመጋገብ
**የጠላና የቢራ ግብግብ....** ገጽ 32

ጥበባት
**የማይጠራ ድፍርስ** ገጽ 33

ቴክኖሎጂ
**የሞባይል ባንክ አገልግሎት እና ስጋቶቹ** ገጽ 34


# ውይይት
#Weyeyet

**ሞላ ዘገየ እና ቤተሰቦቹ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
እየታተመ በየ30 የሚወጣ መጽሔት
ሚያዝያ 22፣ 2008 ተጀመረ!
አድራሻ፡- ቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 283
ፖ.ሳ.ቁ. 3845
አዲስ አበባ
ስልክ ቁጥር፡- +251118688992
ኢሜይል፡- weyeyet@gmail.com
ድረገጽ፡- www.weyeyetmagazine.com

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ሞላ ዘገዬ
ኢሜይል፡- molla.zegeye@yahoo.com

**ተባባሪ ማኔጂንግ ኤዲተር**
አበበ በየነ

**ዋና አዘጋጅ**
በሪሁን አዳነ
ክ/ከተማ: ቦሌ ወረዳ: 08 የቤትቁ. አዲስ
ኢሜይል፡- berihunq@gmail.com

**አዘጋጅ**
ጌታቸው በቀለ
ኢሜይል፡- getachewbekele750@gmail.com
ተስፋዬ ሽብሩ
ኢሜይል፡- tesfishyt@gmail.com

**ዲዛይን|ካርቱን**
ሀብ ዲዛይን
habdesign707@gmail.com

## አምደኞች
መስከረም አበራ
ዶ/ር ቴዎድሮስ ኃ/ማርያም
መብራቱ በላቸው
ሔኖክ አክሊሉ
ተሾመ ተስፋዬ
ቴዎድሮስ አጥላው
አበበ አሰመረ
ሔኖክ ይዘንጋው
ብሩህ ዓለምነህ

**አታሚ፡-**
ሰላሞን ከበደ ማተሚያ ቤት
ን/ስ/ላ/ክ/ከ ወረዳ 11
የቤት ቁጥር አዲስ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ማንኛውም ፅሁፎች ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# መጪው ዘመን የኢትዮጵያ ከፍታ ነው!!!



## ርዕሰ አንቀፅ

## እሳትን ማዳፈን ወይስ እውነቱን መጋፈጥ? የሰነን ፖለቲካ ይብቃ!

የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነሐሴ 27 እና 28 ቀን 2009 ዓ.ም. ባካሄደው መደበኛ ስብሰባው የ2009 ዓ.ም. የድርጅትና የመንግሥት ሥራዎች አቅድ አፈጻጸምን በጥልቀት በመገምገም መደበኛ ስብሰባውን ማጠናቀቁን የግንባሩ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ባወጣው መግለጫ አስታውቋል:: ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ባለፈው ዓመት በነሐሴ ወር የተጀመረው በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ የደረሰበትን ደረጃ፣ ያስመዘገበውን ውጤትና ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በዝርዝር መገምገሙን እና አቅጣጫ ማስቀመጡን አውስቷል መግለጫው:: ከጽሕፈት ቤቱ የወጣው መግለጫ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከግንባሩ አመራር ጀምሮ በሁሉም ብሔራዊ ድርጅቶች አመራርና አባላት እስከ ሕዝብ ድረስ በተካሄዱ መድረኮች የሥልጣን አተያይ ብልሽት የወለዳቸውን የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካ መገለጫ የሆኑት "ትምክህተኝነት"፣ "ጠባብነት"፣ "የሃይማኖት አክራሪነት"፣ ብልሹ አሠራርና ሙስና እንዲሁም በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ የተዛቡ አመለካከቶች ላይ ነጻና ግልፅ ትግል የተካሄደባቸው መሆኑን በዝርዝር መፈተሹን ገልጿል::

በአጠቃላይ የግንባሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ግምገማ፣ ባለፈው ዓመት ለተጀመረው ሕዝባዊ አመጽ መነሻ የሆኑ ዋና ዋና ጥያቄዎች በድርጅቱ ጥልቅ ተሐድሶ በመፈታት ላይ ናቸው የሚል ነው:: ግንባሩ የገጠሙኝን ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ለመቋቋምና ሕዝቡን ተጠቃሚ ለማድረግ በሚያስችል ቁመና ላይ እገኛለሁ እያለ ነው::

የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ይህን ይበል እንጂ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ አሁንም ትልቅ ፈተና የተደቀነበት ነው:: ለሕዝባዊ አመጹ መቀስቀስ ምክንያት የሆኑ መሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎች አሁንም አልተፈቱም:: የአገራችን ህልውና የሚፈታተኑ ቁልፍ ጥያቄዎች አሁንም እንዳሉ ናቸው:: ሐቀኛ መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች፣ መሠረታዊ የሥልጣን ክፍፍልና የእኩልነት ጥያቄዎች፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ጥያቄዎች፣ በየክልሎቹ የሚታዩትና ለግጭት መንስኤ የሆኑት የማንነት ጥያቄዎች ወዘተ. አሁንም አልተፈቱም:: አሁንም የመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱ የሚሻሻልበት ሁኔታ አልተመቻቸም፤ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት አክቲቪስቶች እስር ቤት ነው የሚገኙት:: በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል እየተደረገ ነው የሚባለው እና በኢሕአዴግ በኩል እንደትልቅ ስኬት የሚቆጠረው "ድርድር"ም በተነጻጻሪ የተሻለ አቅምና የሕዝብ ውክልና አላቸው የሚባሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ያገለለ ድራማ ነው:: እነዚህና ሌሎች ጥያቄዎች ሐቀኛና ዘላቂ መፍትሔ ባላገኙበት ሁኔታ አገር አማን ነው ማለት ራስን ከማታለል የዘለለ ትርጉም የለውም::

ችግሮችን በማስቀየስ፣ በማዳፈን እና ራሳችንን በመሸንገል መቀጠል አይቻልም:: በድሮ በሬ በማረስም ዘላቂ መፍትሔ አይገኝም:: በዚህ ከቀጠልን በችግር ላይ ችግር እየተደራረበ፣ በከረሙት ችግሮቻችን ላይ ሌሎች ችግሮች እየተከመሩ ወደማንወጣው አዘቅጥ መግባታችን ነው:: ከሥርዓቱ ጋር ተጣጋግተው የምቾት ሕይወት የሚመሩ አካላት እና ሥርዓቱ የእንጀራ ምንጫቸው የሆኑ ምላስ ረገጥኛም ካድሬዎች የሕዝቡን ችግር ሊረዱት አይችሉም፤ ቢረዱትም ያለውን ሥርዓት ከመደገፍ ውጪ አማራጭ እንደሌላቸው ስለሚገነዘቡ ሁሉም ነገር ሰላም ነው ብለው መኖርን ይመርጣሉ:: ለዚህ ነው መንግሥት በአፈጮሌ ካድሬዎችና የ'ኢስታብሊሽመንት' ሰዎች አማካይነት የሚደረግን ግንኙነት ትቶ በቀጥታ ከሕዝቡ ጋር መገናኘት ያለበት:: በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች አሁን የያዙትን ለማንም የማይጠቅም የተለመደ አካሄድ ትተው፣ የገጠሙንን ፈታኝ አገራዊ ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችል የአስተሳሰብ ደረጃ ላይ እንዲገኙ ያስፈልጋል:: መንግሥት እሳትን ለማዳፈን ከንቱ ሙከራ ማድረጉን አቁሞ እውነቱን ለመጋፈጥ ደፋር መሆን ይኖርበታል::

እንደዚህ ዓይነት ቁርጠኝነት በሌለበትና መሠረታዊ የፖለቲካ ችግሮች ባልተፈቱበት ሁኔታ ስለ ፍቅር፣ ሰላምና መግባባት ማውራት ባዶ ጩኸት ነው የሚሆነው:: "የኢትዮጵያ ቀን"፣ "የአንድነት ቀን"፣ "የፍቅር ቀን"፣ "የሰላም ቀን"፣ "የመግባባት ቀን" ወዘተ. ትርጉም የሚያገኙት ሐቀኛ ብሔራዊ መግባባት ሲፈጠር ነው:: በእርግጥ "የኢትዮጵያ ቀን"፣ "የአንድነት ቀን"፣ "የመግባባት ቀን"፣ "የሰላም ቀን" ወዘተ. እየተባለ መከበሩ መልካም ነው:: የሚደገፍ እንጂ የሚነቀፍ ሊሆን አይችልም:: ሆኖም "የሰላም ቀን" እውነትም "የሰላም ቀን" የሚሆነው መንግሥት ከሥርዓቱ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ማሳደዱን ሲያቆም ነው:: መግባባት የማያምኑበትን ሐሳብ ከማክበር ነው የሚጀምረው:: ሰላምና መግባባት ጠያቂውን ከማሰር ሳይሆን ጥያቄውን ለመፍታት ከመሞከር ነው የሚጀመረው:: ሰላም ከጠብ መንጃ አፈሙዝ አይገኝም:: ያለ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና እኩልነትም ጠንካራ ኢትዮጵያዊነትንና አንድነትን መገንባት አይቻልም::

***በውይይት መጽሔት ላይ የመጽሔቱ አቋም የሚንፀባረቀው በ‹ርዕሰ አንቀፅ› ላይ ብቻ ነው::***

# አዲስ ዘመን

በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር የ2010 ዓ.ም መባቻ - አዲስ ዓመት ላይ እንገኛለን:: የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በተመለከተ የአቡሻኽር ሊቃውንት ካስተማሩት ቀንጨብ አድርገን እናቀርባለን::

የዘመን አቆጣጠር፦ ዓመታትን፣ ወራትን፣ ሳምንታትን፣ ሰዓታትን፣ ደቂቃን በየስፍራቸው የሚገልጽ የሚተነትን የሚለካ ነው:: ዘመንን ለመቁጠር የሚያገለግለው ቀመር፦ ባሕረ ሐሳብ፣ በዐረብኛ አቡሻኽር፣ በአማርኛ የዘመን አቆጣጠር እንዲሁም መርሐ ዕውር ይባላል:: በአንዳንድ ሊቃውንት ዘንድም ሐሳበ ብርሃን፣ መጽሐፈ ሐሳብ በሚል ስም ይታወቃል::

"ሐሳበ ዘመን" የተባለበትም ሐሳብ ማለት ቁጥር ማለት ነው:: ዘመን ደግሞ በቁሙ ሆኖ ዘመናትን ዓመታትን፣ ወራትን ሣምንታትንና ቀናትን እስከ ሰዓታት፣ ደቂቃና ቅጽበት (ሰከንድ) ጊዜያት ሳይቀር የሚሰፍር ስለኾነ ነው:: እነዚህ ሁሉ በሐሳብ ተመርምረው፣ ተመዝነው፣ ተሰፍረው፣ ታውቀው፣ ተቆጥረው ሲያበቁ ምድብና ቀመር ተሰጥቶአቸው የሚገኙበትን ውሳኔና ድንጋጌ እያሰማ የሚጠራበት ስለኾነ ሐሳበ ዘመን ተባለ::

"ባሕረ ሐሳብ" ማለት ቁጥር ያለው ዘመን ማለት ነው:: ባሕር ማለቱ የትምህርቱን ስፋትና ጥልቀት የሚያመለክት ነው:: የዘመን አቆጣጠር ፈሊጥ ስለሚናገር ዘመንን በቁጥር እየሰፈረ ከዚህ ይህን ያህል አለፈ፣ ለዚህ ይህን ያህል ቀረ እያለ ያልተሟላውን የተረፈውን የሚነግር በመኾኑ የተሰጠው ስያሜ ነው:: (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ መጽሐፈ ሰዋስው ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ 1948፣ 261)::

"አቡሻኽር" የሐሳበ ዘመንን ትምህርት ካዘጋጁትና ካስፋፉት ሊቃውንት ዮሐንስ አቡሻኽር አንዱ ነው:: የሐሳበ ዘመን አቀራረቡ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ዝነኛና የተወደደ በመኾኑ መጽሐፉን በስሙ አቡሻኽር ብለውታል:: "መርሐ ዕውር" ተብሎ የተጠራበትም ምክንያት አለው:: መርሐ ዕውር- የዐይነ ሥውር መሪ፤ ዐይነ ሥውርን የሚመራ ለማለት ነው:: ዐይነ ሥውር እሾህ እንዳይወጋው፣ እንቅፋት እንዳይመታው ገደል ወድቆ እንዳይጎዳ መሪው ጠብቆና መርቶ ከቤት እንዲያደርሰው፤ የዘመን ቁጥርም ሰውን ጠብቆና መርቶ አጽዋማት በዓላት የሚውሉበትን ወደ ማወቅ ያደርሰዋልና::

በአጠቃላይ የዘመን አቆጣጠር አገልግሎት የሰው ልጆች ሁሉንም እንቅስቃሴዎች በጊዜ እየሰፈሩ እንዲያከናውኑ አምላክ የሰጠው ተፈጥሮአዊ ዕውቀትና ሀብት ነው::

## ርእሰ ዐውደ ዓመት

የዘመን መለወጫ በዓል ለዓመት መጀመሪያ እንደ መሆኑ መጠን፤ ለአውራኅም(ለወራትም) ጥንታቸው ነውና፤ በዓመቱ ወራት በመጀመሪያ ቀን ይከበራል:: የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ መስከረም ላይ ሲሆን የአውሮፓውያን ደግሞ ጃንዋሪ ላይ ይከበራል::

የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ መስከረም አንድ ቀን የሆነበትን ምክንያት ሊቃውንቱ ሲያትቱ (ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት) የዓመት ዑደታቸውን በጳጉሜን ወር ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው:: በዚህም ጊዜ ሌሊቱም ከቀኑ ጋር እኩል ይሆናል:: ለዘመን መታወቂያ ይሆን ዘንድ ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ተፈጠረ እንዲል ቅዱስ መጽሐፍ (ሄኖክ.2፣1-49)::

በአጠቃላይ በመስከረም ወር ቀንና ሌሊቱ እኩል 12 ሰዓት የሚሆንበት ወር ነው:: ምክንያቱም ከመስከረም 6 እስከ ታኅሣሥ 26 ድረስ ፀሐይ በምድር ወገብ አካባቢ ስለምትሆን ነው:: ከዚህም በላይ ኖህና ቤተሰቡ ከጥፋት ውኃ ድነው ምድር መድረቋን አበባና ፍሬ መስጠቷን የተመለከተው በዚህ ወር ነበር (ዘፍ.8፣8):: በዓመቱም (ከ12 ወር በኋላ) የዘመን መባቻ መጀመሪያ ወይም የዘመን መለወጫ አድርጎ አክብሯል ኩፋሌ (6፣ 24):: "በመጀመሪያ ወር መባቻ ለራሱ መርከብ ይሠራ ዘንድ ታዘዘ በእርሱም ምድር ደረቀች" ይህንንም በማስመልከት እኛም ምድር ስትደርቅ አበባ ማበብ ሲጀምር የዘመን መለወጫችንን በመስከረም ወር እናደርጋለን:: ከዚህም በተጨማሪ ከጨለማ (ከክረምት) ወራት ወደ ብርሃን መሸጋገራችን በማስመልከት ምሳሌያዊ በማድረግ የዘመን መለወጫችንን ከዚህ ጋር በማያያዝ እናከብራለን::

ሌላኛው ታሪካዊ ክስተት ደግሞ በዚህ ወር ንግሥት ሳባ ኢየሩሳሌም ደርሳ የጠቢቡ ሰሎሞንን ጥበብ አድንቃ ስትመለስ ዕንቁ ለጣትሽ በማለት በርካታ የከበሩ ዕንቁ በስጦታ የተበረከተላት በዚህ ወር በመሆኑ፤ የዘመን መለወጫን በወርኃ መስከረም እናደርጋለን:: በዚህም የተነሣ መስከረም አንድ ቀንም "ዕንቁጣጣሽ" በመባል ይታወቃል::

## የዘመን አቆጣጠራችን ከምዕራባውያን አንጻር

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ "ባሕረ ሐሳብ" በሚለው መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከምዕራባውያን የተለየበትን ምክንያት ሲያትቱ፦ "ዋናው ነገር አንድ ታላቅ ታሪካዊ ድርጊት ፈልጎ እርሱን መነሻ ማድረግ ነው:: ሮማውያን የሮም ከተማ የተቆረቆረችበትን ዘመን መነሻ አድርገውት ነበር:: ታላቁ እስክንድር የገነነበትም የዘመን መቁጠሪያ ሆኖ ነበር:: የእኛ ካህናትም 'ዘመነ እስክንድር' በሚል ስም ይጠቀሙበት እንደነበር የብራና መጻሕፍቶቻችን ይመሰክራሉ:: ሶርያውያን የዘመን አቆጣጠርን (ማለት በፀሐይ ቆጥሮ ለዓመቱ 365/6 ዕለት መስጠትን) ከሮማውያን በተዋሱ ጊዜ የዓመቱን መጀመሪያ ጥቅምት (ኦክቶበር) 1 ቀን ላይ አድርገውት ነበር:: በኋላ የሰማዕታት መታሰቢያ እንዲሆን በ460 ዓመተ እግዚእ ወደ መስከረም (ሴፕቴምበር) 1 ቀን ለወጡት:: ግብጾችና እኛ ርእሰ ዐውደ ዓመታችንን መስከረም 1 ቀን ያደረግነው ይህንን በመከተል ነው:: የዓመቱን መጀመሪያ በመስከረም ማድረግን ከሶርያውያንም ሆነ ከግብጾች ብናገኘውም ጀማሪው በ46 ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ይገዛ የነበረው ቄሳር ዮልዮስ ስለነበረ የዮልዮስ ባሕረ ሐሳብ (Julian Calendar) ይባላል::

ዮልዮስ ቄሣር በ46 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ባወጣው የዘመን አቆጣጠር ሥርዐት መሠረት ዓመቱን 365 ዕለት ከ6 ሰዓት አድርጎ ለአራቱ ወሮች 30፣30 ዕለት ለአንዱ ወር 28/29 ዕለት ለቀሩት ሰባት ወሮች 31፣31 ዕለት መድቦላቸው 12 ቦታ ከፈለው:: 12 ወሮች መሆናቸው ነው:: እኛ በዓመቱ ቀኖች ተስማምተን ቀኖቹን በወር ስንከፍል ተለያይተናል:: ዋናው ነገር ዓመቱ ውስጥ ባሉት ዕለቶች መስማማታችን ነው" ይላሉ::

ዓሥራት ገብረ ማርያም ደግሞ፦ "የዘመን አቆጣጠር" በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለጹት ዲዮናስዮስ የተባለው የሮማ መነኩሴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተወለደበት ዘመን በስሌት ለመድረስ የተከተለው መንገድ የታሪክ ክስተትን ነበር:: ይኸውም፦ የሮማ ከተማ የተመሠረተችበትን ዘመን ተነሥቶ በመቁጠሩ ነው:: የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ዘመን ለመወሰን የታሪክ ክስተትን አልተከተለችም:: እርስዋ የተከተለችው ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን 5500 ዘመንን ነው:: አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ይህን አባባል ሲያረጋግጡ እንዲህ ብለዋል:: "ኢትዮጵያ ዘመነ ብሉይን እንዲህ አስተካክላ 5500 ብላ ስትቆጥር ዘመነ ሐዲሷ ልዩ ሆኖ ከማንም ቁጥር አይገጥምም፤ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከምሥራቆቹም ከምዕራቦቹም ወትሮ በሰባት ዓመት ታጎድላለች:: ምክንያቱም ባለ ታሪኮቹን ትታ ወንጌል ተርጓሚዎችን ስለ ተከተለች ይመስላል::" ብለዋል:: በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያና የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት ሊኖረው ችሏል:: (ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ የዘመን አቆጣጠር፣ ገጽ 58-59)::



ተስፋዬ ሽብሩ

# የሕዝብ ብዛት

## በረከት ወይስ መርገም?

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ስለፈጣን የሕዝብ ብዛት ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር:: እርሳቸውም ሲመልሱ የሚወለዱት ሕፃናት እግር ይዘው እንጂ ሆድ ብቻ አይደለም በማለት ብዙዎችን ፈገግ የሚያስኝ መልስ ሰጥተው ነበር:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለጥያቄው ቀጥተኛ መልስ ለመስጠት ፈልገው እንጂ ችግሩ አሳሳቢ መሆኑ ተዘንግቷቸው አይመስልም:: እርሳቸው ይህን ይበሉ እንጂ የሕዝብ ብዛት ብቻውን ሀብት መሆን አይችልም:: የሕዝብ ብዛትን እንደ ሀብት (Resource) መጠቀም የሚቻለው በአገሪቱ ካለው አብዛኛው ሕዝብ የተማረና የሠለጠነ ባለሙያ ሆኖ በምርት ሂደት ላይ ተሰማርቶ አምራችና ሸማች ዜጋ ሲሆን ብቻ ነው:: በአገሪቱ ውስጥ ያለው አብዛኛው ሕዝብ ተገልጋይ ማለት (dependent) ከሆነ ሀብት በመሆን ፋንታ አገልግሎት ፈላጊ ይሆንና በአገሪቱ የምርት ሂደት ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል::

የማዕከላዊ እስታትስቲክስ መረጃ በኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት በፍጥነት እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል:: እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ መጀመሪያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 48 ሚሊዮን ብቻ ነበር:: በ2013 እ.ኤ.አ 88 ሚሊዮን ሕዝብ እንደሚኖርባት ይገመት ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ብዙ ሕዝብ የሚኖርባት የአሕጉሪቱ አገር ሆናለች:: ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በእጥፍ ጨምሯል:: በዚህ ጊዜ ማለትም ከ1990-2013 ባሉት ዓመታት በዓመት 3.6 በመቶ ዕድገት አሳይቷል::

በፍጥነት የሚጨምር የሕዝብ ብዛት በአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ያለው አሉታዊና አዎንታዊ ጎን ለረጅም ጊዜ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ ነው:: የሥነ ሕዝብና የምጣኔ ሀብት ምሁራን በጉዳዩ ዙሪያ የሚያነሱት ሁለት ገዢ ሐሳቦች አሉ:: የመጀመሪያው የሕዝብ ብዛት በፍጥነት መጨመር ለኢኮኖሚ ዕድገት እንቅፋት ሊሆን አእንደሚችል ይጠቅሳሉ:: በተቃራኒ ወገን ያሉት የሕዝብ ብዛት መጨመር ለኢኮኖሚ ዕድገት ጉልህ እመርታ እንዳለው ይጠቁማሉ:: በአሁኑ ወቅት በሥነ ሕዝብና በምጣኔ ሀብት ዙሪያ ማዕከላዊ የክርክር፣ ጭብጥ ሆኖ ብቅ ያለው በሕዝቦች የዕድሜ ደረጃ (መዋቅር) እና በምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት መካከል ስላላው ትስስር ነው::

የማኅበረሰብ ሣይንስ ባለሙያዎችና የሥነ ሕዝብ ምሁራን የምርምር ዝንባሌያቸውን ያደረጉት በሕዝቦች የዕድሜ መዋቅር ወይም እርከን (Age structure)፣ የውልድት ምጣኔ (Birth rate) እንዲሁም የሞት ምጣኔ (mortality rate) መቀነስና መጨመር ሊያስከትል የሚችለውን የኢኮኖሚ ዕድገትና ውድቀትን ነው በማለት ኬሊ ጄ የተሰኙ ምሁር፤ “The population debate in historical perspective: Revision Revised (2001)” በተሰኘ ጥናታቸው ይጠቅሳሉ:: የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት መጨመር በነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ውጤት አለ:: ነገር ግን ይህን ዓይነቱን አሉታዊ ገጽታ ለመቀነስ እያደገ ከሚመጣው ሕዝብ ብዛት ውስጥ አምራች የሆነውን ኃይል በመጨመር ወደ አዎንታዊ ውጤት መቀየር እንደሚቻል የምጣኔ ሀብት ምሁራን ይጠቁማሉ:: አምራች የሆነውን ኃይል በመጨመርና ምቹ የሥራ ከባቢን በመፍጠር ቁጠባንና ኢንቨስትመንት በማሳደግ የሕዝብ ብዛት ሊያስከትለው የሚችለውን ተግዳሮት ወደ መልካም አጋጣሚ መቀየር ይቻላል እንደባለሙያዎቹ ገለጻ::

### “ዲሞግራፊክ ዲቨደንድ” እና “ዲሞግራፊክ ትራንዚሽን”

“ዲሞግራፊክ ትራንዚሽን” በወሊድ ምጣኔና በሰዎች ህልፈተ ሕይወት መጠን ላይ ተመርኩዞ የሚሰላ የሕዝብ ዕድገት መጠንን የሚያሳይ ጽንሰ ሐሳብ ሲሆን ይህም የወለድ ምጣኔ ከፍ ያለ ሆኖ የሞት መጠን ዝቅ ያለ ሲሆን ከፍተኛ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ እንደሚኖርና የወሊድ ምጣኔና የሕዝብ ሞት መጠን ሁለቱም ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ሲሆኑ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ ዝቅ እንደሚል የሚገልጽ ሐሳብ መሆኑን ዶ/ር እሸቱ ጉርሙ በአዲስ አበባ የኒቨርስቲ የሥነ ሕዝብ ትምህርት ክፍል መምህር ያስረዳሉ::

የወሊድ ምጣኔ (Fertility rate) ከፍተኛ ሲሆን በርካታ ሕፃናት የሚወለዱ ከመሆናቸው አንጻር አገልግሎት ፈላጊ (dependent population) የሕዝብ መጠን ከፍ ያለ ሆኖ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ላይ ጫና የማሳደር ክስተት ይስተዋላል:: በአንጻራዊ መልኩ ደግሞ የወሊድ ምጣኔ ዝቅተኛ ሲሆን የሚወለዱ ሕፃናት ቁጥር አነስተኛ የአገልግሎቱ ፈላጊ (dependent Population) ቁጥር ዝቅተኛ ስለሚሆን ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽዖ የማድረግ ሁኔታን ይፈጥራል:: አገልግሎት ፈላጊ ሲባል በምርቱ ሂደት ላይ ያልተሰማሩትን የኅብረተሰብ ክፍል በተለይም ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች በጡረታ ዕድሜ ክልል ማለትም ከ60 ዓመት በላይ የሚገኙትን አረጋውያንን ማለት ነው:: እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች በምርት ሂደት ተግባር ላይ ሣይሆን ሕፃናቱ በትምህርት መቅሰም ተግባር ላይ የተሰማሩ በመሆናቸውና አረጋውያንም ደግሞ በጡረታ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው ተገልጋይ እንጂ አምራች ዜጋ ሆነው ለኢኮኖሚ ዕድገት በቀጥታ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ባለመኖሩ ተገልጋይ ወይም ተረጂ (dependent) ተብለው እንደሚጠቀሱ ዶ/ር እሸቱ ይጠቁማሉ::

የወሊድ ምጣኔና የሞት መጠን መቀነስ ለሕዝብ ዕድገት ዝቅተኛ መሆን አስተዋጽዖ የማበርከታቸውን ያህል የኑሮ ሁኔታ ማደግና የጤንነት አጠባበቅ ሥርዓት መሻሻል ደግሞ የአረጋውያን ዕድሜ እንዲጨምርና በጡረታ ዕድሜ ክልል ያሉ ነዋሪዎች ቁጥር እንዲበረክት ያደርጋል የሚሉት የሥነ ሕዝብ ምሁሩ ይህም ለሕፃናት ዕድገትና ትምህርት ይውል የነበረው በጀት ለአረጋውያን እንክብካቤና የጤንነት አጠባበቅ መሟላት ለሚያስፈልገው ወጪ እንዲመደብ ሊያስገድድ እንደሚችል ይገልጻሉ::

“ዲሞግራፊክ ዲቨደንድ” በአንድ አገር ውስጥ በሕዝብ ዕድገት መጠን ለውጥ ሳቢያ የሚከሰት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ተግባር ሲሆን ይህም የተገልጋዩ/የተረጂው ቁጥር ማለትም የሚወለዱት ሕፃናት ቁጥር ሲቀንስና የአረጋውያን ቁጥር ጨምሮ ቀደም ሲል ለሚወለዱት ልጆች ጤንነትና ትምህርት ይውል የነበረው በጀት ለአረጋውያን እንክብካቤና ክትትል ሲውል በፊት አገሪቱ ካላት በርካታ አምራች ዜጋ ልታገኘው የምትችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ነው:: ይህም ማለት አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ ወጣት አምራችና፣ ሸማች ዜጋ ሲሆን ኢኮኖሚውን በስፋት ስለሚያንቀሳቅሰው አገሪቱ ለምርታማነትና ለኢንቨስትመንት አመቺ ሁኔታ ላይ እንድትገኝ ያደርጋታል:: ሆኖም ግን ወጣቱና ሁሉም ዜጋ ሁሉም በቂ ገቢ ሊያስገኝለት በሚችል የሥራ ዘርፍ ላይ መሠማራት ይኖርበታል የሚሉት ዶ/ር እሸቱ ክስተቱ ጤናማ የተማረ ንቁና ቀልጣፋ አምራች ወጣቶችን በብዛትና በጥራት ወደ ሥራው ማሰማራት እንደሚያስችል ይናገራሉ::

ይህ ክስተት በዘመናት መካከል ለጥቂት ጊዜ ብቻ በተለይም አጋጣሚው ሲፈጠር ሊኖር የሚችለው ከ30-40 ዓመታት ብቻ ሲሆን አገራት ጥንቃቄ በተመላበት ዕቅድ ተመርተው በተለይም የሥነ ሕዝብና የኢኮኖሚ ዕድገት ሁኔታው ሊጣጣም በሚችል መልኩ ካልመሩት ክስተቱ ሳይጠቅም ሊያልፍ ይችላል:: በዚህ ረገድ ደቡብ ኮርያ፣ ታይላንድ፣ ቻይና፣ ሲንጋፖርና ሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ አገራት በሰፊው ተጠቃሚ መሆናቸውን የጠቆሙት ዶክተር እሸቱ እንደ ብራዚል፣ ሜክሲኮ ያሉ የላቲን አሜሪካ አገራት በ“ዲሞግራፊክ ትራንዚሽን” ውስጥ ቢያልፉም ከዲሞግራፊክ ዲቪደንድ እምብዛም ተጠቃሚ ሊሆኑ አለመቻላቸውን ይናገራሉ:: ምክንያቱም በአገራቱ የታየው ዲሞግራፊክ ትራንዚሽን

በበቂ ሁኔታ ለዲሞግራፊክ ዲቪደንድ አመቺ ባለመሆኑ የአጋጣሚው ተጠቃሚ ሳይሆኑ ጊዜው አልፎባቸዋል:: "ዲሞግራፊክ ቦነስ" ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ሐሳብ መሆኑን የጠቀሱት ዶ/ር እሸቱ በሕዝብ ዕድገት ምጣኔ ለውጥ ሳቢያ በአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ የሚታይ ፈጣንና ጠንካራ ለውጥ በመሆኑ አገራት ወጣትና አምራች ዜጎችን በስፋት በማቀፍ የሚያስመዘግቡትን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያመላክት መሆኑንም አስታውሰዋል::

ትክክለኛና የተቀናጀ የሥነ ሕዝብና የኢኮኖሚ ዕድገት ፖሊሲ ከሌለ የአምራችነት የዕድሜ ደረጃ ድርሻን ብቻ ማሳደግ የዲሞግራፊ ዲቪደንድ ተጠቃሚነትን ለማግኘት የሚያበቃ ዋስትና ሊሆን አይችልም የሚሉት የዘርፉ ምሁራን እንዲያውም ለወጣቱ ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረ ሥራ አጥነት ይባባሳል፣ ወንጀል ይበራከታል፣ የፖለቲካ አለመረጋጋትም በመፍጠር አገራቱን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሊወስዳቸው ይችላል በማለት ስጋታቸውን ይገልጻሉ::

ዶ/ር እሸቱም ይህንን ሐሳብ ይጋራሉ:: ፈጣን የሕዝብ ዕድገት (Rapid Population Growth Rate) በአንድ አገር ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት (Socio economic development) ላይ ብርቱ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል:: ፈጣን የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ የሚኖረው በርካታ ሕፃናት ሲወለዱና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአጠቃላይ በአገሪቱ የሕዝብ ቁጥር ላይ የሚጨመረው ተቀላቢና አገልግሎት ፈላጊ ብዛት በርካታ ሲሆን ነው:: ይህ ደግሞ እናቶች ወደ ምርት ተግባር ሳይሆን ሕፃናቱን ወደመንከባከብ እንዲያዘነብሉ የሕክምና ተቋማት የነፍሰጡር እናቶችንና የሕፃናቱን ጤንነት እንዲንከባከቡ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በየዓመቱ ወደ ትምህርት ተቋም ለሚገቡ አዳዲስ ተማሪዎች የመማሪያ ቦታና መምህራን እንዲያዘጋጁ ገበሬዎች ደግሞ ለተጨማሪ ሕፃናት ቀለብ እንዲያመርቱ ስለሚያደርግ አብዛኛውን የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት ለፍጆታ እንዲውል ያስገድደዋል:: በዚህም ምክንያት ለኢንቨስትመንት የሚውለውን የአገሪቱ ሀብት ውስን ይሆንና የልማት ተግባራት በብዛትና በፍጥነት እንዳያከናውኑ ያደርጋል በማለት የችግሩን አሳሳቢነት በግልቀት ይፈትሻሉ::

ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገቡ አገሮች ማለትም እንደ ኮርያ፣ ታይዋን፣ ቻይናና የመሳሰሉት አገራት የኢኮኖሚ ዕድገት ከመጀመራቸው በፊት የወሊድ መጠኑን የመቀነስ እርምጃ ወስደዋል:: በዚህ ምክንያት በየዓመቱ የሚወለዱ የልጆች መጠን ለመቀነስ በመቻላቸው ለፍጆታ (Consumption) ማለትም ለጤና አገልግሎት ለትምህርትና ለመኖሪያ ቤቶች ለቀለብ የሚውለውን ወጪ በመቀነስ ያንን ሀብት ለኢንቨስትመንት ለማዋል የላቀ የቴክኖሎጂ የኢንዱስትሪ ሽግግር ለማከናወን መቻላቸውን ዶ/ር እሸቱ ያስረዳሉ::

የአገር ኢኮኖሚን ኢንቨስት በማድረግ ልማትን ለማከናወን የሚረዳ ምቹ ሁኔታ ከሌለ ኢንቨስትመንትን ለማካሄድ የግድ ወደ ብድርና እርዳታ ጥያቄ መገባት ይኖርበታል:: ይህም በተለያዩ መስኮች ወደፊት መከፈሉ ስለማይቀር ምንም እንኳን የኢኮኖሚ ዕድገት ቢኖርም በሕዝቡ አኗኗር ላይ ለውጥ ለማምጣት ረጅም ጊዜ የሚወስድ ይሆናል የሚሉት ዶ/ር እሸቱ ፈጣን የሕዝብ ብዛት የሚያስከትለውን ተያያዥ ችግሮች ይዳስሳሉ::

የኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት ከተፈጥሮ ሀብት እና ምጣኔ ሀብት ዕድገት ጋር ይተሳሰራል:: ከዓመታት በፊት በአገሪቱ 48 ከመቶ የነበረው የደን ሽፋን እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ ተመናምኗል:: ይህም የሕዝቡ ብዛት በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያመጣው ጫና በመሆኑ ምጣኔ ሀብቱን እንደሚጎዳው ይታወቃል:: ሕዝብ በየጊዜው የሚጨምር ከሆነ የተፈጥሮ ሀብት መጎዳቱ አይቀርም:: በሕዝብ ብዛት የተነሣ የተፈጥሮ ሀብትን ለመቀራመት የሚደረግ ሩጫ የተፈጥሮ ሀብቱን አደጋ ውስጥ ሊከተው እንደሚችል የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች ያስረዳሉ::

ባለፉት ዐሥርት ዓመታት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የአካባቢ ጥበቃ መዛባት ገጥሟታል:: ለዚህም በዋናነት እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው በሕዝብ ብዛት የተነሣ የሚከሰተው ችግር ነው:: ከሥነ ምሕዳር መዛባት ጋር በተያያዘ የመሬት ለምነትና በቂ ምርት የመስጠት አቅም መቀነስ ዋነኛው ነው:: በርካታ የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠር የሚኖርና የኢኮኖሚ መሠረቱም ግብርና በመሆኑ መሬቱ በተደጋጋሚ በመታረሱ ምርታማነቱ አደጋ ላይ ወድቋል:: የሕዝብ ብዛቱ በየጊዜው በፍጥነት በመጨመሩ (2.6-3) የተለያዩ ዛፎችና ተክሎች ለማገዶነት እና ለሌሎችም ግብዓቶች በመዋላቸው የአገሪቱ የደን ሽፋን ከ40 በመቶ ወደ 4 በመቶ አዘቅዝቋል::

ዛፎችን ለተለያዩ ግብዓቶች መቁረጥና የመመንጠር መጠኑም በዓመት ወደ መቶ ሺሕ ሄክታር ደርሷል:: የደኖች መመናመን የአፈሩን ንጥረ ነገር በጎርፍ እንዲታጠብ በማድረግ አፈሩ ለምነቱን እንዲያጣና ምርታማነቱ እንዲቀንስ እያደረገ መሆኑን ካርላ ቤደሊ እና ሌሎች "Population growth and environment in Ethiopia (2001)" በተሰኘ ጥናታቸው የችግሩን አሳሳቢነት ለመጠቆም ሞክረዋል::

## የሕዝብ ብዛት፣ የምግብ ዋስትና እና የተፈጥሮ ሀብት

በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ከተከሰተው ድርቅ በተጨማሪ በከፍተኛ ፍጥነት የሚያድገው የሕዝብ ቁጥርና የአካባቢ መራቆት ችግር ላለፉት ሦስት ዐሥርት ዓመታት ኢትዮጵያ ላጋጠማት አስከፊ የምግብ እጥረት ዋነኛ ምክንያት ነው:: ከ1960ዎቹ ጀምሮ አገሪቱ እያደገ ከመጣው ሕዝቧ ጋር ራሷን በምግብ የመቻል ፈተናን ለማለፍ እንዳልቻለች ምሁራኑ ከላይ በተጠቀሰው ጥናታቸው አካተውታል::

ፈጣን የሕዝብ ዕድገት በማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ላይ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም በምግብ ዋስትና መረጋገጥ በአካባቢ ደኖችና የእርሻ ይዞታዎች ላይ ብርቱ ተጽዕኖ ያሳድራል:: ለምሳሌ እያንዳንዱ ዜጋ በልቶ ማደር ስላለበት ዛፎች በብዛት ተቆርጠው የሰብል ማሣ እንዲበረክት፣ የግጦሽ መሬቱ እንዲመነምን የምግብ ዋስትና እንዲንኮታኮትና ታዳሽ ያልሆኑ የኃይል ምንጮች እንዲነጥፉ ሊያደርግ ይችላል:: ፈጣን የሕዝብ ዕድገት በዚህ ረገድ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቋቋም በቴክኖሎጂ የታገዘ ልማት ማካሄድ ተገቢ ቢሆንም አብዛኛው የአገሪቱ ሀብት ሕፃናትን ለመንከባከብና ለማስተማር መዋል ስላለበት የመዋዕለ ንዋይ እጥረት ለኢንቨስትመንትና ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚረዳ፣ የማኅበረሰብና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ተግባራት በስፋት እንዳይከናወኑ ስለሚያደርግ በርካታ የሕዝብ ቁጥር ያላት አገር በተለይም አብዛኛው ተገልጋይ (dependent) ከሆነ የተፈጥሮ ሀብት ከማሟጠጥ፣ አካባቢ ከመራቆት፣ የምግብ ዋስትና መረጋገጥ በጥያቄ ምልክት ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል በማለት ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር ሊያስከትል የሚችለውን ተያያዥ ችግር ዶ/ር እሸቱ በስጋት ያዩታል::

የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም የአካባቢ መራቆትን ለመከላከልና የምግብ ዋስትናን በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ ስከን ያለ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ ያስፈልጋል የሚሉት ዶ/ር እሸቱ ይህ ማለት በአንድ አገር ውስጥ በየዓመቱ በወሊድ ምክንያት የሚጨምረው የሕዝብ ብዛት ከኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ጋር የተመጣጠነ በተለይም ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱን የሚያግዝ ከሆነ የተፈጥሮ ሀብት ከመመናመን ይልቅ ይበልጥ ሊለሙ፣ የአካባቢ ሁኔታ ከመራቆት ይልቅ ይበልጥ በደን ሊሸፈኑና፣ የምግብ ዋስትናን ሊረጋገጥ ይችላል::

የሕዝብ ብዛት የተፈጥሮ ሀብት ያራቁታል የሚለውን ሐሳብ በተቃራኒው የሚያዩት አሉ:: ከእነዚህ አንዱ ዶ/ር ወልዳይ አምሖ ናቸው:: የሚወለደው ሰው ሁሉ ሆድ ብቻ ይዞ አይመጣም፤ የሚሠሩ እጆችና የሚያስብ አእምሮ ጨምሮ ይመጣል የሚለውን የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሐሳብ ይጋራሉ:: ስለዚህ ሕዝብ ቁጥሩ ቢጨምርም የተሻለ አሠራርና ፈጠራ ሊያመጣም እንደሚችል መረዳት ይገባል የሚል ሐሳብ አላቸው:: የሰው ሀብት ልማት ላይ እንዲሁም ምጣኔ ሀብት ማሳደግ ላይ ትኩረት ከተደረገ ሕዝብ ብዛት በራሱ መንገድ ቁጥጥር ስለሚደረግበት ስጋት ሊሆን አይችልም በማለት ያስረዳሉ::

ሕዝብ ሲበዛ መሠረተ ልማት ከማሟላት አኳያ ችግር በመፍጠር ውጫዊና ውስጣዊ ስደት እንዲባባስ በማድረግ ሥራ አጥነትን በማስፋፋት እንዲሁም በምጣኔ ሀብቱ ላይ የጥገኞችን ቁጥር ያበዛዋል:: ከፖለቲካ አኳያም አለመረጋጋትና ሁከት ሊቀሰቅስ ይችላል:: ስለዚህ ፈጣን የሕዝብ ዕድገት ከፈጣን ምጣኔ ሀብት ዕድገት ጋር ተዋሕዶ ካልሄደ አደጋው የከፋ እንደሚሆንና በአገር ላይ ከፍተኛ የሆነ ስጋት ሊፈጥር እንደሚችል የዘርፉ ምሁራን ይጠቁሙና፤ ይህንን ለማስታረቅ በጠንካራ የሥነ ሕዝብና የኢኮኖሚ ፖሊስ የታገዘ የተቀናጀ አሠራር በአገር ደረጃ ሊሠራ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ::

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የወሊድ መጠንን በመቀነስ በተለይ ወጣት ሴቶችን በትምህርት በማብቃት የወሊድ ቁጥርን ለመቀነስ ያስችላል:: ወጣት ሴቶች እየተማሩ በሄዱ ቁጥር ካልተማሩት በተሻለ የቤተሰብ ምጣኔን እንደሚገነዘቡ ይታወቃል:: በተጨማሪም የትምህርት ተደራሽነትንና ጥራትን፣ ግብርናውን የማዘመን አሠራርን መሠረተ ልማት ዝርጋታውን፣ አካባቢ ጥበቃን፣ ጾታዊ እኩልነትን አካቶ ቤተሰብ ምጣኔን ላይ በመሥራት ይህንንም በጠንካራ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ በመደገፍ ፈጣን የሕዝብ ዕድገት ሊያመጣ የሚችለውን የወሊድ መጠን መቀነስ እንደሚቻል የዓለም ባንክ በ2011 ያወጣው ጥናት ይጠቁማል::

የአንድ አገር ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚለካው በአገሪቱ ሕዝቦች ላይ በሚያመጣው የአኗኗር ሁኔታ (Quality of Life) ለውጥ መሆን

ወደሚቀጥለው ገጽ ▶

▶እንዳለበት መታወቅ ይኖርበታል:: ኢኮኖሚያዊ ዕድገት (Economic Growth) በሕዝብ አኗኗር ሁኔታ ላይ ሊከሰት ይችላል:: ለምሳሌ አንድ የዓለም አቀፍ ኩባንያ (Multinational Corporation) በአንድ አገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ካካሄደ በአገሪቱ ውስጥ የሚመረተውን ምርትና የሚሰጡትን አገልግሎቶች (Goods and services produced in a country during the year) በከፍተኛ መጠን ሊያሳድግ እንደሚችል የሥነ ሕዝብ ምሑሩ ዶ/ር እሸቱ ያስገነዝባሉ:: ይህም እንደ ኢኮኖሚ ዕድገት መለኪያ የሚወሰደውን (Per capita income) ሊያሳድገው ይችላል:: ነገር ግን ከምርቱ ሂደቱ የተገኘው ትርፍና ኢንቨስትመንት የዋለው ዋናው ገንዘብ ወደ መጣበት አገር እየተመለሰ የሚሄድ ከሆነ፤ አገሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት (Socio-economic transformation) በማሳየት ረገድ ቀርፋፋ ልትሆን እንደምትችልና የአንድ አገር የሕዝብ ዕድገት ምጣኔና የምጣኔ ሀብት እድገት የተመጣጠነ መሆን እንደሚኖርበት ያስረዳሉ::

የተመጣጠነ የምጣኔ ሀብት የሕዝብ ዕድገት ማለት በአገሪቱ ውስጥ የሚኖረው ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በሕዝቦች አኗኗር ላይ መሠረታዊ ለውጥ በሚያመጣ ሁኔታ የተቃኘ ሲሆን ነው:: ይህም ማለት አንድ ሕፃን ሲወለድ በቅድሚያ የምግብና የጤንነት አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ማግኘት ይኖርበታል:: ከፍ እያለ ሲሄድም የትምህርት አገልግሎት ይፈልጋል:: ቀጥሎም ለራሱና ለሚመሠርተው ሕዝብ ቀለብና ተዛማጅ ወጪዎች መሸፈኛ በቂ ክፍያ የሚያገኝበት ሥራ ያስፈልገዋል:: ከዚያም የመኖሪያ ቤትና ወደ ሥራ ሄዶ የሚመላለስበት የትርንስፖርት አገልግሎትና መንገድ ይፈልጋል:: የተሟላ ኑሮ ለመኖር ደግሞ ሌሎች ተዛማች አግልግሎቶች በበቂ ሁኔታ መቅረብ ይኖርባቸዋል:: ይህንን ሁኔታ የተጣጣመ ለማድረግ ለ1% ሕዝብ ዕድገት 3% የኢኮኖሚ እድገት እንደሚያስፈልግ በዚህ ዘርፍ የተሰሩ ጥናቶች ያስረዳሉ::

ይህም ማለት ለምሳሌ አንድ አገር የሕዝብ ምጣኔ በ2.5% በየዓመቱ ቢያድግ ይህቺ አገር መሠረታዊ የሕዝቦችዋን ፍላጎት ለመሟላት ቢያንስ ቢያንስ ኢኮኖሚያዊ በ7.5% በየዓመቱ ማደግና የዚህ ዕድገት ተጠቃሚዎችም ሕዝቦቿ መሆን እንዳለባቸው ይነገራል:: በዚህ ረገድ የተሸለ ማኅበረ ኢኮኖሚ ዕድገትና የተሻሻለ የአኗኗር ሂደት ለማምጣት በቅድሚያ የሕዝብ እድገት ምጣኔን መቀነስ ዋነኛ አማራጭ ተደርጎ መወሰዱን የሚናገሩት ዶ/ር እሸቱ እንደ ጃፓን ያሉ አገራት የተሻሻለ ዕድገት ማስመዝገብ የቻሉት የሕዝብ እድገት መጠናቸውን ወደ 1 ፐርሰንት በማውረድና ኢኮኖሚያቸውን ደግሞ 10 ፐርሰንት በላይ በማድረስ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል:: ይህ ሁኔታ ደግሞ ጃፓን የራሷን ኢኮኖሚ በሰፊው በአገሪቷ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ መቻሏንና የኢንቨስትመንቱ ተጠቃሚ እንድትሆን አድርጓታል ይላሉ::

ልማትን ለማካሄድ በቅድሚያ የሚቆጠብ ኢኮኖሚያዊ የአመራረት ሥርዓት ሊኖርና የሚቆጠበ ገንዘብም ተመልሶ በኢንቨስትመንት መልክ በሰፊው ወደ ሥራ የሚገባበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል:: በአንዳንድ አገሮች በውጪ ዕርዳታ በብድርና በውጪ ካፒታል ፍሰቶች በመከናወን ላይ የሚገኙት የልማት እንቅስቃሴዎች ለኢኮኖሚው ማደግ የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ቀላል ባይሆንም ብድሩ ሊከፈልና ወደ አገር ውስጥ የገባው የካፒታል መጠን ተመልሶ ወደ መጣበት አገር ሲመለስ የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻልና መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ረዘም ያለ ጊዜ መውሰዱ የግዴታ ይሆናል::

ለዚህም ነው በአንዳንድ አገሮች የሚታየው የኢኮኖሚ ዕድገት ሥር ነቀል የሆነ የኑሮ ሁኔታ ለውጥ በሕዝቡ ዘንድ ሳያሳይ የሚቀረውና ኅብረተሰቡ ከዕድገቱ ተጠቃሚ የማንሆነው የሚል ጥያቄ እንዲያቀርቡ የሚያደርገው:: ስለዚህም ፈጣን የሕዝብ ዕድገት መጠንን መቀነስ አገራት በራሳቸው ኢኮኖሚ እንደተማመኑ መሠረታዊ የኑሮ ለውጥ (Quality of Life) እንዲያመጡና አገራዊ ሀብት በቅድሚያ ለቁጠባ በቀጣይነትም ለሰፊ ኢንቨስትመንት እንዲመጣ ያደርጋል:: ይህም የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥና የአካባቢ ልማት እንዲፋጠን የሚረዳ በመሆኑ አገራቱ የሕዝቡ ዕድገት መጠን ከማኅበረሰባዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ ብርቱ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ዶ/ር እሸቱ ይመክራሉ::

## የውልደትና የሞት ምጣኔ

የሕዝብ ብዛትን የሚወስኑ ሦስት ነገሮች አሉ:: ውልደት፣ሞትና ስደት ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ በኢትዮጵያ ለሕዝብ ብዛት መጨመር የሚጠቀሱት የውልደትና የሞት ምጣኔ ሲሆኑ፤ የስደት ምጣኔ ብዙም ግምት ውስጥ የማይገባ መሆኑን ከበደ ተስፋዬ “Theoretical consideration of Demographic variable in development programs (1994)” በተሰኘ ጥናታቸው ይጠቅሳሉ:: አያይዘውም የውልደት ምጣኔው ከ1970-1990 ከፍተኛ ሲሆን፤ ከዚያ በኋላ ባሉ ዓመታት ግን መቀነሱን ይገልጻሉ:: የ2000 የኢትዮጵያ የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት መረጃ እንደሚያሳየው የውልደት ምጣኔው አንዲት ሴት ስድስት ልጆች ትወልድ ነበር:: ባለፈው ዐሥር ዓመት ምጣኔው ወደ ግማሽ ልጅ መቀነስ ተችሏል:: ይህም ቢሆን አሁንም ከፍተኛው የወሊድ ምጣኔ እንደሆነ ከበደ ተስፋዬ ከላይ በተጠቀሰው ጥናታቸው ያስረዳሉ:: በቅርቡ የማዕከላዊ እስታቲክስ ኤጀንሲ የ2008 ዓ.ም. የሥነ ሕዝብ ጤና ጥናት ውጤትን ይፋ አድርጓል:: በጥናቱ ከተካተቱት ዋነኛው የሥነ ሕዝብና የጤና ጥናት ውጤቶች መካከል በፈረንጆች 2000 ላይ 5.5 ልጅ በአማካይ የነበረው የአንዲት ኢትዮጵያዊ እናት የውልደት መጠን አሁን በጥናቱ ወደ 4.6 ልጅ በአማካይ መውረዱ ታውቋል:: ይህም የሆነበት ምክንያት በእናቶች ጤናና በቤተሰብ ምጣኔ ላይ በተሠራው ውጤታማ ሥራ መሆኑ ተጠቅሷል::

የሕዝብ ብዛት በራሱ ሀብት መሆኑን የሚጠቅሱት አካላት ሰፊ የገበያ አማራጭና ገበያ የመሳብ እምቅ ሀብት መሆኑንም ጨምረው ያስረዳሉ:: አገሪቱ ከ30 ዓመታት በታች በርካታ ሕዝብ ስለሚኖሩባት ወጣቱም ለልማቱ ጠቃሚ ስለሚሆን የሕዝብ ብዛቱ በራሱ ስጋት እንደማይሆን ይሁን እንጂ ቁጥጥር ሊደረግበት እንደሚገባ ይጠቁማሉ:: የሕዝብ ብዛትንና የምጣኔ ሀብት ዕድገት እንዲሁም ከተፈጥሮ ሀብት ጋር ያለውን ዝምድና በማጣጣም የሕዝብ ብዛት ስጋት ከመሆኑ አስቀድሞ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም እንደሚቻል ይከራከራሉ::

የኢትዮጵያ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር ዶ/ር ወልዳይ አምኃ የሕዝብ ብዛት ሥጋትም ነው፤ ሥጋትም አይደለም የሚል መከራከሪያ አላቸው:: የሕዝብ ብዛት ስጋት ቢሆን ኖሮ ቻይና ትጠፋ ነበር፤ ነገር ግን ሕዝቧን ከሞላ ጎደል ለመመገብ፤ የሥራ ዕድልም ለማስፋፋትና ወጣቶቿን በሥራ ለማሳተፍ ችላለች:: ስለዚህ ሕዝብ ኃይል ነው:: ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ጠንካራ ኢኮኖሚ እየገነባችና እየፈጠረች ያለች አገር ናት:: ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ ኢኮኖሚው በሚፈለገው ደረጃ ባለመድረሱ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲው ላይ ትኩረት ተደርጎ ሊሠራ እንደሚገባ ዶ/ር ወልዳይ ያስረዳሉ:: ይህ ካልሆነ ግን ሥራ አጥነቱ በተስፋፋበትና በተለይ በከተሞች በምግብ ራስን መቻል ባልተቻለበት ሁኔታ ሕዝቡም አምራች ኃይል ሳይሆን ቁጥሩ ብቻ ካደገ አገሪቱ አስቸጋሪ ፈተና ውስጥ እንደምትወድቅ ዶ/ር ወልዳይ ያስረዳሉ::

በኢትዮጵያ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው ሽግግር አዝጋሚ ነው:: ዶ/ር ወልዳይም በዚህ ይስማማሉ:: ወደ ኢንዱስትሪ በሚደረገው ሽግግር አገሪቱ ተኝታ ነበር:: አሁን ጅምሮች አሉ:: ለውጡ በአንድ ጊዜ የሚመጣ አይደለም:: የግል ባለሀብቱ ወደ ማንፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው በሚፈለገው መጠን ሊገባ አልቻለም:: መንግሥት ይህንን ዘርፍ በተለያዩ ማበረታቻዎች በማገዝ ድጋፍ በማድረግ አብሮ መሥራት አለበት:: የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ማመን ያስፈልጋል:: መተማመን ሲኖሮ ነው ውጤታማ መሆን ብሎም በፍጥነት እያደገ ለመጣው ወጣት ኃይል የሥራ ዕድል መፍጠር የሚቻለው በማለት ዶ/ር ወልዳይ በፍጥነት እያደገ ላለው የሕዝብ ቁጥር ኢንዱስትሪው የሚከፍተውን የሥራ ዕድል ይጠቁማሉ::

ባለፈው ዓመት በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች የታየው የሕዝብ እምቢተኝነት በተለይም የወጣቶች ተቃውሞ መንግሥትንም፣ አገርንም፣ ሕዝብንም ብዙ ዋጋ አስከፍሏል:: መንግሥት ችግሮችን በማፈን አድበስብሶ የመሄድ አቅጣጫ ሲከተል መቆየቱ ለተባባሰ እምቢተኛነቱ በር ከፋች ሆኗል:: ችግሮችን ቀድሞ በማየትና መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ የማዳፈን እርምጃ የሚከተለው ገዢው መንግሥት እንደ ፈሊጥ የያዘው “ተሐድሶና ጥልቅ ተሐድሶ” የሚል ትችት በተደጋጋሚ ይነሣበታል:: ለኢኮኖሚው ዕድገትና ሁሉን ዐቀፍ አካታች ለሆነ ልማት ፖለቲካዊ መግባባቶች ወሳኝ ድርሻ እንዳላቸው ዶ/ር ወልዳይ አስታውሰው ባለፈው ዓመት የተከሰተውንም ችግር መመርመር የሚያስፈልገው ከምንጩ መሆን እንዳለበት ይናገራሉ::

የኢኮኖሚ ዕድገቱ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል አካቷል? በየጊዜው ቁጥሩ እየጨመረ ላለው ለወጣቱ የሥራ ዕድል ለመፍጠር አስችሏል? ኢንቨስትመንትን በበቂ ሁኔታ ለመሳብ ተችሏል? የሚሉት መሠረታዊ ጉዳዮች መልስ ሊያገኙ እንደሚገባም ጠቁመዋል:: ስለዚህ ያለፈው ችግር መንግሥትን በፖለቲካዊም ሆነ በኢኮኖሚያዊ አካሄዱ ላይ ቆም ብሎ እንዲያስብ ሊያደርገው እንደሚችል ዶ/ር ወልዳይ አምኃ አስረድተዋል::

በኢትዮጵያ ፈጣን የሕዝብ ዕድገት በኢኮኖሚ ዕድገቱ ላይ የራሱ የሆነ ጫና መፍጠሩ ቢታወቅም ለኢኮኖሚ ዕድገት መቀጨጭ ብቸኛ ምክንያት አይደለም:: ሌሎች ምክንያቶች ማለትም የማይክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታው፣ የተቋማት ተጠያቂነት እና ግልጽነት፣ የቴክኖሎጂ ፖሊስና የአቅም ግንባታ መጠናከር ግምት ውስጥ መግባት እንደሚኖርባቸው ካሣሁን ዓለሙ “Impact of population Growth on the Ethiopian economic performance (2014፣ 44)” በተሰኘው ጥናታቸው ገልጸውታል::



ጌታቸው በቀለ



# የጫት ኢኮኖሚ

ኒውዮርክ ታይምስ (New York Times) ጋዜጣ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተስፋፋ የመጣውን ጫት የመቃም ልማድ በሰፊው ዘግቦታል፤ "በኢትዮጵያ ውስጥ ጫት መቃም ልምድ መስፋፋቱ አሳሳቢ ሁኗል:: ከመላው ኢትዮጵያ ወጣቶች ግማሽ ያህሉ ጫት ይቅማሉ፤ ችግሩም ወረርሽኝ ሆኗል" ሲል ምንጭ ጠቅሶ ዘግቧል:: የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ሐምሌ 28 ቀን 2017 ዓ.ም. "አፍሪካ በጋዜጦች" በሚለው ዝግጅቱ የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣን ጠቅሶ አገሪቱ በጫት የምታገኘው ገቢ ከፍተኛ መሆኑን እንደሚከተለው ገልጾታል፤ "1.2 ሚሊዮን ኤከር የሚሆን መሬት ለጫት ተክል ተመድቧል:: ከሃያ ዓመታት በፊት ከነበረው ወደ ሦስት እጥፍ ይጠጋል:: ጫት በእያንዳንዱ ኤከር የሚያስገኘው ገቢ ቡና ካካተቱ ሌሎች ምርቶች ከሚያስገኙት ልቆ እንደሄደ የአፍሪካ ጥናቶች ተመራማሪ ገሠሠ ደሴ መናገራቸውን" አብራርቷል:: በአገራችንም በቅርቡ የተጠኑ ጥናቶችም ሆኑ የሚወጡ ዘገባዎችም ይህንኑ አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው::

የእነዚህ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ዘገባ አንድ ነገር ይጠቁመናል:: የጫት ተክል ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዋልታ ቢሆንም እንኳ፤ ጫት የመቃም ልማድ ከመስፋፋቱ የተነሣ አገሪቷን ወደ ማትወጣው አዘቅት ውስጥ እየከተታት መሆኑን ነው:: በአንጻሩ ደግሞ በተባበሩት መንግሥታት የዓለም ጤና ድርጅት በ1980 ባደረገው ጥናት ጫትን ከአልኮልና ከትንባሆ ያነሰ ንጥረ ነገር የያዘ ቢሆንም፤ በአደገኛ ዕፅነት የተመዘገበ መሆኑን ያስረዳል:: ይህንንም ተከትሎ በርካታ አገራት ጫት ወደ አገራቸው እንዳይገባ ደንግገዋል:: ይሁን እንጂ በአገራችን የጫት ተዘውታሪነት ከዕለት ወደ ዕለት እያደገ መጥቶ በለጋ ዕድሜ ያሉ ሕፃናት ሳይቀር በጫት ሱስ መያዝ በርካቶችን እያሳሰበ፣ እያወያየ የሚገኝ ርእሰ ጉዳይ ሆኗል:: በተለይ ከምሳ ሰዓት ጀምሮ በአገራችን ከተሞች በጫት መሸጫ ሱቆች ተኮልኩሎ፣ ጫት ገዝቶ በስስ ላስቲክ ሸክፎ ይዞ ሲሔድ የሚታየው ወጣት "አገሪቱ ወዴት እየሔደች ነው?" ያስብላል:: ዛሬ ራሱን ለሱስ ለማስገዛት የሚጣደፈው ወጣት የነገ አገር ተረካቢ መሆኑንም የዘነጋው ይመስላል:: ይህንን መሠረት በማድረግ ውይይት መጽሔት የተለያዩ ጥናቶችን በመመልከት፣ ጫት ሻጮችን፣ ቃሚዎችን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችንና ባለሙያዎችን በማነጋገር ይህን ዘገባ አዘጋጅታለች::

## የጫት ተክል ታሪካዊ ቅኝት በኢትዮጵያ

በዘመናችን ለሰው ልጆች ከመጠን በላይ አነቃቂ ከሆኑት በርካታ ዕፀዋቶች አንዱ የኾነውን ጫት መዝገበ ቃላቱ እንደሚከተለው ይፈታዋል፤ "ለጋውን፣ ቀንበጡን…የሚያኝኩት…" ነው:: (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962፤ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 629):: ጫት በሣይንሳዊ ስሙ ካታ ኤዱሊስ (Catha edulis) በመባል ይታወቃል::

ጫት የየት አገር ብቃይ እንደሆነ በርካታ ጸሐፊዎች የየራሳቸውን የጥናትና ምርምር ውጤቶቻቸውን አስነብበዋል:: ከተመራማሪዎቹ አንዳንዶቹ እርስ በርስ የሚቃረኑ ሐሳቦችን ቢያቀርቡም አብዛኛዎቹ ጸሐፍት ግን የጫት መገኛ አገር አቢሲኒያ (ኢትዮጵያ) እንደሆነች ይስማማሉ:: (Al-habeshi and Skaug፣ 2005):: እንግሊዛዊው ጸሐፊና ተርጓሚ ሰር ሪቻርድ በርተን (Sir Richard Burton) በ1856 በጻፈው መጽሐፍ ጫት ወደ የመንና ሌሎቹ አገራት የሔደው ከኢትዮጵያ እንደሆነ ያስረዳል:: (Burton፣ 1856):: በ14ኛው መ/ክ/ዘ በዐረብኛ የተጻፉ መረጃዎች፡- የምሥራቁ የአገራችን ክፍል በሆነው በሐረርጌ ደጋማ አካባቢዎች ጫት በብዛት ይመረት እንደነበርና ለየመናውያን ከ6ኛው መ/ክ/ዘ ጀምሮ መግባት መነሻ ይኸው ሐረር ነው የሚሉ የጽሑፍ ማስረጃዎች አሉ (ወልደ አማኑኤል፣ 2007):: ተሰማ ሰብስቤም ጫት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው በኢትዮጵያ መሆኑን "በርጫ (ጫት)" በሚለው መጽሐፉ እንደሚከተለው አስፍሮታል:: "የቡና መገኛ የሆነችው አገራችን ኢትዮጵያ እንደ ቡናው መገኛነት ኩራት ብዙም ባይዘፈንላትም የጫት መገኛ ናት":: (2004፣ 79)::

ጫት በኢትዮጵያ በቀደሙት ዘመን እንደ አሁኑ አይብዛ እንጂ ይቃም እንደነበር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም "የሕይወቴ ታሪክ" በሚለው መጽሐፋቸው ገልጸዋል:: ጫት በነገሥታቱ ዘንድ ባለመለመዱ ልጅ ኢያሱ በመቃሙ ችግር እንደደረሰበት ሲያስረዱ፤ "ጫት ያስቀባጥራል፣ ልብ ይነሣል ሲሉ እሰማ ነበር፤ ልጅ ኢያሱም ጫት ይበላሉ በስተኋላም በጣም ማብዛት ጀምረው ነበር…" በዚህ ምክንያት በወቅቱ ከቤተመንግሥቱ እንደተገለሉና ከሥልጣን ለመውረዳቸውም እንደ አንድ ምክንያት መቅረቡን ይዘረዝራሉ::

ጫት በዓለም አቀፍም ሆነ በኢትዮጵያ በርካታ መጠሪያ ስሞች አሉት:: በእንግሊዘኛ ተናጋሪ አገራት khat፣ በየመን qat and gat፣ በሶማሊያ qaat and jaad፣ በኢትዮጵያ chat (ጫት) ተብሎ ይታወቃል:: ከእነዚህም በተጨማሪ የአቢሲኒያ ሻይ (Abyssinian Tea)፣ የዐረቦች ሻይ (Arabian Tea) ይባላል:: በማለት ጫት ከኢትዮጵያ ተነሥቶ በአካባቢው ወዳሉት አገራት የመን፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ማላዊ፣ ታንዛኒያ፣ የዐረብ ባሕረ ሰላጤ አገራት፣ ደቡብ አፍሪካና ሌሎችም አገሮች በስፋት መድረሱንና መብቀሉን ያስረዳል:: (Al-Mugahed Leen፣ 2008)::

ጫት በሚቃምበት ወቅት ውስጣዊና ውጪያዊ ስሜቶችን ሊያነቃቁ የሚችሉ ንጥረ ነገሮች አሉት:: እነዚህም፡- Cathinone, Cathine እና norephed-rine የሚባሉ ንጥረ ነገሮች (ቅመሞች) የያዘ ነው:: ትኩስ ቅጠሉን በቀላሉ ማግኘት በሚቻልባቸው አገራት ጫት በቀላሉ እየታኘከ በውኃና በሌሎች ጣፋጭ የፈሳሽ ዓይነቶች የሚወራረድ ሲሆን፤ ትኩስ ቅጠሉ በማይገኝባቸው አገራት እንደ ሲጃራ ተጠቅልሎ አሊያም ፒፓ ላይ ተደርጎ ይጨሳል:: በዓለም አቀፍ ደረጃ በጫት ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር የሚያደርጉ አገራት እንዳሉ ሁሉ፤ በተቃራኒው በከፍተኛ ሁኔታ የሚሸጥባቸው ደግሞ እንደ ጅቡቲ፣ ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ… ያሉ አገራት መሆናቸውን ይኸው ጥናት ያስረዳል::

## የጫት ዝርያ ዓይነቶች

የጫት ዝርያ ዓይነቶች የሚመረቱባቸው አካባቢያዊ ሁኔታዎች መለያየት ማለትም የቦታው አቀማመጥ፣ የአየር ጠባዩ፣ የአፈሩ ዓይነት፣ የሚደረግለት እንክብካቤ ወዘተ. መሠረት በማድረግ ቀላል የማይባሉ የይዘት ልዩነቶች እንደሚፈጥሩ ባለሙያዎች ያስረዳሉ:: የጫት ዓይነቶችም በኅብረተሰቡ ዘንድ በስፋት የሚታወቅበት ጫቱ የመጣበትን ቦታ፣ እንደሚበቅልበት ከተማ ስያሜ የተለያዩ ናቸው:: ወንዶ፣ በለጬ (የማብለጭለጭ ጠባይ ያለው)፣ አቦ ሚስማር (ቂጡ ላይ ሚስማር የሚመስል ቅርጽ ያለው)፣ ገለምሶ (ማታ ማታ ለቅሶ ይሉታል)፣ አውዳይ፣ የባሕር ዳር እና የጉራጌ ጫት ይባላሉ:: የጫት መጠሪያው ይኼ ብቻ አይደለም:: በአገሪቱ በተለያየ አቅጣጫ የየራሱ የሆነ ስያሜዎች አሉት (ዝኒ ከማሁ፣ 2004፣ 81)::

ከላይ የተገለጹት የጫት ዓይነቶች በዋጋቸውም ይለያያሉ:: አወዳይ እና ገለምሶ የተባሉት ጫቶች ከሐረር አካባቢ የሚበቅሉ ናቸው:: አወዳይ በጫት የጥራት ደረጃ (በቃሚዎች የወጣ እንደሆነ ልብ ይሏል) ቀዳሚ የተሰኘ ነው:: ዋጋውም ከሌሎች የጫት ዓይነቶች በእጅጉ ይወደዳል:: ይህንን ጫት የሚቅሙት ጥሩ የገንዘብ አቅም ያላቸው ሰዎች እንጂ በሌሎች አይደፈርም:: ይህ ጫት አገራችንን ወደተለያዩ አገራት በከፍተኛ መጠን

ወደሚቀጥለው ገጽ ▶

ከምትልከው የጫት ዓይነት ውስጥ ዋነኛው እንደሆነም ይነገራል:: ገለምሶ፣ ወንዶ እና በለጬ በተቀራራቢ የዋጋ ደረጃ የሚሸጡ የጫት ዓይነቶች ናቸው:: ገለምሶ ከተቃመ በኂላ የሚያመጣው የስሜት ለውጥ (ምርቃና) ኃይለኛ እንደሆነ ሲነገር ወንዶና በለጬ ሰውነት ውስጥ ሙቀት ከመስጠት ባሻገር ብዙም የሚያመጡት የስሜት ለውጥ የለም:: የጉራጌ ጫት የሚባሉት ናቸው:: እነዚህ በተናጠል እንደሚበቅሉበት ሥፍራ የራሳቸው ስያሜ አላቸው:: "እንድብር፣ ወለኔ፣ ወልቅጤ" ይባላሉ፤ በዋጋም ደረጃ ብዙ ገንዘብ አይጠይቁም::

## የመቃም ጦርነቶች ከትናንት-ዛሬ

ጫት በየቀኑ ካላገኘ የማይንቀሳቀስ ቃሚ አለ፤ ለሥራ ማነቃቂያ ብሎ ጫት ቤት ሔዶ አልያም ቤቱ ወስዶ የሚቅም አለ:: የዕረፍት ጊዜውን ቅዳሜና እሑድ ጠብቆ ከጓደኞቹ ጋር ሰብሰብ ብሎ የሆድ የሆዱን ለመጫወት የሚቅም አለ፤ በተቃራኒው ደግሞ 24 ሰዓት ከአፉ ጫት ሳትወጣ ኦክስጅን የሆነችለት ቃሚም አለ:: ጫት የዕድሜ፣ የጾታ፣ የትምህርት ደረጃ የኢኮኖሚና የአስተዳደግ ባሕል ልዩነት ሳይገታው ተዘውታሪነቱ ይበልጡኑ እያደገ ነው:: ቀደም ባሉት ጊዜያት ጫት ሰው እያየ ፊት ለፊት ይዞ መንቀሳቀስ እንደ ነውር የሚቆጠርበት ሁኔታ ነበር:: በአሁኑ ወቅት ግን፤ በአብዛኛው ቃሚ ከመንደር አንሥቶ እስከ አደባባይ፣ በታክሲ ውስጥ፤ በዩኒቨርስቲዎች፣ በመኖሪያ ቤት፣ በማስቃሚያ ቤቶች፣ በመንገድ ላይ፣ በገበያ ቦታዎች፣ በቢሮዎች ሳይቀር ይቃማል:: ከዚህም በተጨማሪ አዳዲስ የሆኑ የጫት መቃሚያ የግለሰቦች መኖሪያ ቤቶችም እየተፈጠሩ ነው::

በዚህ ዘመን እየተመለከትን ያለነው ወጣቱ የገዛውን ጫት በስስ ላስቲክ ይዞ ሲጓዝ አይሸማቀቅም፤ እንደውም እንደ ዘመናዊነት እየታየ ነው:: በርካታ ሠራተኞች ከጫት የተነሣ ይጠርም ይብዛም የሥራ ጊዜያቸውን ያባክናሉ:: ጫት ለሠላሳ ዓመት ቅሜያለሁ የሚለው መስፍን አበበ ጫት ቤት ገብተህ ስታይ ጫት ይቃማል ሳይሆን እንደ ምግብ ይበላል ማለት ይቻላል ይላል:: "በጫት ቤቶች ውስጥ ዶክተሩ፣ መሐንዲስ፣ አስተማሪው፣ ባለሥልጣኑ፣ ዘፋኙ፣ ወያላው፣ የታክሲ ሹፌሩ፣ የቤት እመቤቶች ሳይቀሩ በየዕለቱ ከትመው ይበላሉ" ሲልም ያክላል:: ይህ ልማድ አሁን ባለበት የመስፋፋት ፍጥነት ሲታይ ችግሩን በእንጭጩ እንዳይፈታ አሳሳቢ አድርጎታል ይላሉ ባለሙያዎቹ:: አንዳንድ ወላጆችም በልጆቻቸው በጫት ሱሰኝነት መጠመድ ከማዘናቸውም በላይ፤ በአገሪቱ የጫት ቃሚ መስፋፋት ተጠያቂው መንግሥት ነው በማለት ይተቻሉ:: "ከኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር ለያዘው ወጣት መንግሥት በቂ የሥራ ዕድል አልፈጠረላቸውም፤ በቂ የሥራ ቦታዎች ባለመኖራቸው ለጊዜ ማሳለፊያ ጫት ይቅማሉ" በማለት መፍትሔ እንዲጣ ያማርራሉ::

የሚቃመው ጫት በከፍተኛ ደረጃ የስሜት ለውጥን ሲያስከትል "ምርቃና" ይባላል:: በምርቃና ወቅት በቃሚዎቹ ዘንድ የተለያዩ ባሕሪና ስሜቶች ይንጸባረቃሉ:: አንዳንዱ ያለመታከት ያወራል:: ሌላው ባልተጨበጠ ተስፋ በደስታ ይቦርቃል:: ገሚሱ በሌለና በሚያስጨንቅ ሐሳብ ውስጥ ተዘፍቆ ይፈዛል:: በጫት ቤት አግኝተናቸው አስተያየት የሰጡን ወጣቶች "ምርቃና ከመጣ የተወሰነ አልኮል ነክ መጠጥ ተጎንጭቶ ስሜትን ማርገብ የግድ ነው:: ያለ በለዚያ ሌሊት ዐይንህ እንደፈጠጠ ጀንበር ስትወጣ ታያለህ" ሲሉ ሌሎች ደግሞ "እንዳለማመድህ ነው ጫት ቅመህ መጠጥ የማታዘወትር ከሆነ እንቅልፍ አይነሣህም::" ይላሉ::

በጫት ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ ከባለፉት ሁለት ሥርዓቶች ይልቅ ከኢሕአዴግ ሥልጣን መያዝ ጋር ተያይዞ የጫት ሥርጭት መጨመሩን ተሰማ ሰብስቤ ጥናቶችን መሠረት አድርጎ ሲያቀርብ፡- የሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ በአገር ውስጥም በውጭም የመንቀሳቀስ፣ ተዘግተው የነበሩ ኬላዎች መከፈት፣ የጫት ሥርጭትን በሓላፊነት ለመከታተል የወሰደ አካል አለመኖሩ፣ በዓለም ላይ እየጨመረ የመጣው የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ:: (ዝኒ ከማሁ፣ 2004፣ 79):: በእነዚህ ዓመታት የመቃም ባሕል በአገራችን በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ መጥቷል:: ለዚህም ምክንያት ያለውን ሚኪያስ ሰብስቤ በመጽሐፉ "በአንዳንድ አካባቢዎች ለእህል ሰብልና ለቡና ተክል ይውሉ የነበሩ ማሳዎች በጫት ተክል እየተተኩ በመሔድ ላይ ይገኛሉ:: ጫት በሚበቅልባቸው የአገሪቱ ክፍሎችና የጫቱ ንግድ በሚሧሧርባቸው ክፍሎች የሚገኙ የፖለቲካና የአስተዳደር ሹማምንት ከጫት ከፍተኛ ቀረጥ ይሰበስባሉ:: ገበሬውም የምግብ እህል ከማምረት ይልቅ በማንኛውም ጊዜ በጥሩ ዋጋ የሚሸጥለት የጫት ምርት መሆኑን ስለተገነዘበ በሰፈረበት መሬት ላይ ጫት ለመትከል ለመንከባከብና ለማምረት ቅድሚያ ይሰጣል::" (ሚኪያስ ሰብስቤ፣ ማኅበራዊ ጠንቆች እና ያንዣበቡ አደጋዎች፣ 1995፣ 98)::

## ጫት- "ሕጋዊና ሕጋዊ ያልሆነ ተክል" ጠቀሜታው ለማነው?

በብዙ የዓለም አገራት ጫት "ሕጋዊና ሕጋዊ ያልሆነ ተክል" ተደርጎ ይታያል:: ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካና በዐረብ አገራት ሕጋዊ ተክል ነው:: ይኽ ተክል ወደ አገራቸው እንዳይገባ እገዳ በጣሉት የምዕራባውያን አገራት ጫት ሕጋዊ ያልሆነ ተክል ነው:: ሕጋዊ ባይሆንም የሕጋዊነትን ያህል በየመንደሩ ኀብረተሰቡ በስፋት አውቆታል፤ እየተጠቀመም ነው:: አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ጫትን በየቀኑ በዓለማችን ከአንድ መቶ ሚሊዮን በላይ ሰው ይቅማል ተብሎ ይገመታል:: እነዚህ ቃሚዎች በብዛት የሚገኙባቸውን አገራት ወልደ አማኑኤል ገድሶ በመጽሐፉ እንደሚከተለው ዘርዝሮታል:: " የመን፣ ሶማሊያ፣ ኬንያና ኢትዮጵያ የሚኖሩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ በሌሎች የዓለም ክፍሎች በአፍሪካ ቀንድ፣ የደቡብ ምሥራቅ እስያ፣ የመካከለኛ ምሥራቅና ተጎራባች የዐረብ ባሕረ ሰላጤ አገራት ተወላጆች ናቸው::" (ወጣቱና ጫት፣ 2007፣ 23)::

ጫት በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋነኛ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ ምርት ነው:: በየዓመቱ ከመቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ታገኛለች ከምትባለው ኢትዮጵያ ጀምሮ በሌሎችም አገራት ጫትን እንዳይቅሙ የሚያበረታቱ ቀጥተኛ ያልሆኑ ተግሳጾች ቢኖሩም "አዛውንቶችና በተለይም ደግሞ ወጣቶች" በተለያዩ ምክንያቶች ከማዘውተር አልተቆጠቡም:: (ወጣቱና ጫት፣ ገጽ 28):: አዲስ አድማስ ጋዜጣም ዘኢኮኖሚስት መጽሔት ያወጣውን መረጃ በመጥቀስ ጫት ከቡና ቀጥሎ በውጪ ንግድ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ ምርት እንደሆነ ዘግቧል:: "በኢትዮጵያ ከ15 ዓመታት በፊት በጥቂት ቆላማ አካባቢዎች ብቻ ተወስኖ የነበረው የጫት ምርት በአሁኑ ጊዜ በመላ አገሪቱ መስፋፋቱንና ከግማሽ ሚሊየን ሄክታር በላይ መሬት መሸፈኑን መጽሔቱ አመልክቷል::" (ቅዳሜ ጥር 13 ቀን 2009 ዓ.ም.)::

ኒውዮርክ ታይምስም ጫት ለመንግሥት ከፍተኛ ገቢ የሚያስገባ በመሆኑ ከሃያ ዓመታት በፊት ከነበረው መሬት አሁን ወደ ሦስት እጥፍ የሚጠጋ ለጫት ተክል መመደቡን ገልጿል:: ቡና አምራች የነበሩት አካባቢዎችም በጫት ዋጋ በየጊዜው ማሻቀብና በአመራረቱ ቀላልነት እየተሳቡ ከቡና ምርት በመውጣት ወደ ጫት አምራችነት እየገቡ መሆኑንም አስቀምጧል:: ገበሬውም የምግብ እህል ከማምረት ይልቅ በማንኛውም ጊዜ በጥሩ ዋጋ የሚሸጥለት የጫት ምርት መሆኑን ስለተገነዘበ በያዘው መሬት ላይ ጫት ለመትከል፣ ለመንከባከብና ለማምረት ቅድሚያ ይሰጣል ይላል::

ዘኢኮኖሚስት እንደዘገበው የአገሪቱን የውጭ ገበያን በሁለተኛነት ተቆጣጥሯል የተባለው ጫት በአገር ውስጥም ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ምርት መሆኑን በአገሪቱ የተለያዩ ከተሞች የጫት መሸጫ አነስተኛ ኪዮስኮች እንደ አሸን እንዲበራከቱ ምክንያት ሆኗል ይላል:: ዋጋውም ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ መጠን እያደገ መሆኑንና ወጣት ተማሪዎችም ተጠቃሚነታቸው እየጨመረ መሆኑ ለአገሪቱ አሳሳቢ መሆኑን ሪፖርቱ ያትታል:: እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጫት ትውልድ ገዳይ መሆኑ እየታወቀ ትውልዱን ከዚህ ሱሰኝነት ለማውጣት በመንግሥት በኩል ምንም ጥረት አለመደረጉን በርካታ ሰዎችን ያሳዘነ ጉዳ ሆኗል:: "እውን ለትውልዱ የሚያስብ መንግሥትስ አለን?" እንዲሉ አድርጓቸዋል::

ጫት በሚመረትበትና በሚነገድበት ክልል የክልሉ ባለሥልጣናት ከሚገኘው ቀረጥ ተጠቃሚ ስለሆኑ ሁኔታውን እንደጤናማ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አድርገው የወሰዱት ይመስላል:: የፌደራል መንግሥትም ጫት የሚበቅልባቸው ክልሎች ከሚያገኙት ጥቅም በተጨማሪ ተጠቃሚ ነው:: ይህንንም ሚኪያስ ሰብስቤ በመጽሐፉ እንዳሰፈረው ለምሳሌ፡- ከድሬደዋ ወደ ጅቡቲ በአውሮፕላን በባቡርና በመኪና በየዕለቱ ከሚጋዘው የጫት ምርት መንግሥት ቀረጥ እና የውጭ ምንዛሪ ያገኛል:: ከምሥራቅ ሐረርጌ ወደ ሶማሊያ የሚጋዘው ከፍተኛ ጫት እንደዚሁም መጠኑ አነስተኛ ቢሆንም ወደ ሌሎች አገሮች ከሚጋዘው ጫት የማይናቅ ገቢ ይሰበስባል:: በመሆኑም የማዕከላዊው መንግሥት አካላት የዚህን ዕፅ ጎጂነት በይፋ በማጋለጥ ለሕዝቡ ትምህርት ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለመግታት የወሰዱት የጎላ እርምጃ የለም በማለት ቅሬታውን ይገልጻል:: (ዝኒ ከማሁ፣ 98-99)::

በጫት ንግድ አገሪቱ ከምታገኘው ገቢ በተጨማሪ ለአፈር ጥበቃ ጥቅም እንዳለው በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ያስረዳሉ:: በ2005 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ "ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በአፈር ጥበቃ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ" ለመመርመር በተደረገ የማስተሬት ዲግሪ ጥናት የጫት ተክል በመልካም ጎኑ መታየት እንዳለበት ያስረዳል:: "ጫት ለአፈር ጥበቃ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል:: አፈርን ቆንጥጦ ይይዛል፤ መሸርሸርን ይከላከላል:: በተንሸ መሬት ላይ የተሻለ ገቢ ስለሚያስገኝ ገበሬው መሬቱን ይንከባከባል" ይላል::

ጫት የሚቅሙ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ጫት ጥቅም አለው በማለት ይከራከራሉ:: ሠራተኞች በሥራችን ምርታማ እንድንሆን፣ ተማሪዎችም በትምህርታችን ውጤታማ እንድንሆን አድርጎናል፤ ያደርገናልም ይላሉ:: ጫት ጥቅሙ ተግተን እንድንሠራ ያደርገናል የሚለው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ዲግሪውን እየሠራ የሚገኘው እስጢፋኖስ ተሰማ "ጫት ስቅም በደንብ አጠናለሁ:: ለመሥራትም ያበረታታኛል" በማለት በመቃሙ እንደተጠቀመ ይናገራል:: ጫት መቃም ከጀመርኩ አንድ ዓመት ይሆነኛል የሚለው ዓለማየሁ መኮንን "እስከ ዛሬ አለመቃሜ ይቆጨኛል:: ስቅም ደስታ ይሰጠኛል፣ የበለጠ ጉልበት አገኛለሁ ዋናው በሱስ አለመጠመድ ነው" በማለት በመቃሙ እንደተጠቀመ ያስረዳል:: ጫት ለረጅም ዓመት በመቃም ላይ የሚገኝ አንድ በኅልማሳነት ዕድሜ ክልል የሚገኝ ሰው በጫት ተጠቃሚው መንግሥት እንጂ ትውልዱ አለመሆኑን እንዲህ ነበር የገለጸው "ጫት ተጠቃሚው መንግሥት ነው:: አንደኛ በገቢ ሁለተኛ እኔን ጨምሮ ብዙ ጀዝባና ፈሪ ትውልድ ክምችት ይኖራል:: ስለዚህ ሁሉም ስለ መንግሥት፣ ስለ ፖለቲካ ማሰብ አይፈልግም:: ሁሉም የሚያስበው ሱሱን የሚያሟላበትን ትንሽ ብር ብቻ ነው፤ እሷን ካገኘ ምንም አይፈልግም"::

በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎችም ጫት ትውልዱን እየጎዳው እንደሆነ ይናገራሉ:: ዶክተር የራስወርቅ አድማሴ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶሲዮሎጂ መምህር በጫት ላይ ሰፊ ጥናት ያካሄዱ ምሁር ናቸው:: እርሳቸው እንደሚናገሩት "ኢትዮጵያ በጫት ምርት አገኘች ተብሎ ትውልድ እንዲጠፋ መተው ትልቅ ዋጋ ያስከፍለናል" የሚሉት ዶክተር የራስወርቅ በጫት ንግድ ሀብታም ሆኑ የሚባሉ ሰዎች ልጆች በጫት ሳቢያ አእምሮአቸው ተናግቶ በአእምሮ ሕክምና ተቋማት ውስጥ ገብተዋል ሲሉ ተናግረዋል:: በጫት ለሚገኝ የአጭር ጊዜ ትርፍ አገኘሁ ተብሎ የትውልድ መጻኢ ዕድልን መሠዋት ተገቢ አይደለም የሚሉት አጥኚው ይህ ሁኔታ አደገኛ ከሚባልበት ደረጃ ሁሉ አልፏል ባይ ናቸው::

ታዲያ ይህ ሁሉ ኅብረተሰብ ክትልቅ እስከ ትንሽ፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ እየቃመው ያለ ጫት የሚያስከትለው መዘዝስ ይኖር ይሆን? የሚለውን መፈተሽ ግድ ይላል::

## ጫትና መዘዙ

ዛሬ በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ክፍሎች ጫት መቃም እንግዳ ነገር አይደለም:: እንደውም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እየጨመረ እንደመጣ ሚኪያስ ሰብስቤ "ማኅበራዊ ጠንቆች፤ ያንገፀበፁ አደጋዎች" በሚለው መጽሐፉ "በምሥራቅ አፍሪካ የጫት እርሻ እየተስፋፋ ገበሬውና ከተሜው የዚህ ዕፅ ሱሰኛ የመሆን መጠን እየጨመረ በመሔድ ላይ ይገኛል" ይላል:: (ዝኒ ከማሁ፣ 99):: የተጠቃሚው መብዛት የሚያስከትላቸው መዘዞች በርካታ እንደሆኑ የሕክምና ባለሙያዎች ያስረዳሉ:: የሚያስከትሉትንም ጉዳቶች ጠቅለል አድርገን እንመለከታቸው፡-

## የጤና ችግር ያመጣል

ጫት የሚያስከትላቸው የጤና ችግሮች በርካታ ናቸው ይላሉ ተመራማሪዎች:: Glenic Cox እና Hagen Rampes የተባሉ ሳይካትሪስቶች Adverse effects of khat በሚለው ጥናታዊ ጽሑፋቸው "ጫት መቃም የሚጀመረው በቀና አስተሳሰብ ነው:: ከዚያም ቀስ በቀስ በሱስ መጠመድ ይመጣል:: ሱሰኝነት ስሜታዊ መሆን፣ አለመረጋጋትን ያስከትላል ይህም በጤና ላይ የሚያስከትለው ቀውስ" ቀላል አለመሆኑን አስረድተዋል:: ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም "የሕይወቴ ታሪክ" በሚለው መጽሐፋቸው "የጫት ስካር ለአንዳፍታ ይቀሰቅሳል፤ ጥቂት ቆይቶ ያፈዛል" በማለት ሱሱን በቀላሉ የሚላቀቁት አለመሆኑን በመጽሐፋቸው ጠቅሰውታል::

የሕክምና ባለሙያዎች ጫት በጤና ላይ የሚያደርሰው ቀውስ እንዳለ ያስረዳሉ:: ጫት በሚቅሙ ሰዎች ላይ የሚመጣው ምልክት የልብ ምት መጨመር፣ የአፍ ውስጥ እብጠት፣ የጥርስ መበስበስ፣ የምግብ መውረጃ ቱቦ ቁስለት፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍላጎት መቀነስ፣ የደም ግፊት፣ ያልተለመደ የአፍ ውስጥ ድርቀት፣ የአተነፋፈስና የልብ ምት መጨመር፣ ከፍተኛ የሆነ የራስ ምታት፣ እንቅልፍ ማጣት ተጠቃሾች ናቸው:: በተጨማሪም የማመዛዘን የማስተዋልና የማገናዘብ ችሎታን ይቀንሳል፤ የስሜት መረበሽና አለመረጋጋትን፣ በሆነ ባልሆነ መጨነቅና ራስን መጸየፍ ቀስ በቀስ የመሥራት አቅም መቀነስ፣ የእንቅልፍ ጊዜ መዛባት ብሎም መፍዘዝን ያስከትላል:: በጉዳት ረገድም አካላዊ እስከ አዕምሮአዊ ድረስ ችግሮችን ያስከትላል (The health impacts of khat, pp. 4፤ ጫት 2004፣ 86-87)::

## ኢኮኖሚያዊ ችግር ያስከትላል

በጫት ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ከሚያገኙት የሚያጡት፣ ከሚያለሙት የሚያጠፉት የበለጠ መሆኑን የባለሙያ ጥናት አያስፈልገውም:: ቃሚዎቹ በኢኮኖሚ ራሳቸውን ከመጉዳታቸውም በላይ ቤተሰቦቻቸውን፣ ማኅበረሰቡንና አገርንም ሊጎዱ ይችላሉ:: በየዕለቱ በየሚዲያው የምንሰማቸው በተሽከርካሪ አደጋዎች የሰው ሕይወት ማለፍ በአብዛኛው ከጫት ተጠቃሚዎች አሽከርካሪዎች ጋር የተያያዙ ናቸው:: ይህም በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ቀውስ ቀላል አይደለም::

## የማኅበራዊ ሕይወት ጠንቅ

ጫት ለማኅበራዊ ሕይወት መናጋት ዓይነተኛውን ቦታ ይይዛል:: ጫት ሲገኝ በምርቃና፣ ሲጠፋ በድንዛዜ በመያዛቸው በሱሱ ምክንያት ሰዎች ከትዳራቸው እንዲሁም ከማኅበራዊ ሕይወታቸው የተገለሉ በርካታ ናቸው:: ጫት በጋብቻ ሕይወት፣ በማኅበራዊ ዕሴት፣ በሥራ ተነሳሽነት፣ በምግባረ ቢስነት በሀገር ዕድገት ላይ እያሳደረ ያለው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም::

ጫት ተማሪዎችን ከትምህርት፣ ሠራተኞችን ከሥራ ገበታቸው እየወጡ አላግባብ ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ በሥራዎቻቸውም ላይ ተጽዕኖ እያደረገ ይገኛል:: ወጣቱ ለጫት መቃም እንደተቀመጠ ውድ ጊዜያቶቹ ያመልጣሉ:: አፍላ የወጣትነት ጉልበቱና ብሩህ አዕምሮው በዚሁ ጫትና ተከታይ ሱሶች ሳቢያ ተተብትቦና ደንዝዞ ይኖራል:: "The Socio economic effect of khat" በሚል ርዕስ ጥናት ያደረገው አማኑኤል ጫት ትውልዱን እንዳይሠራ እንዳደረገው ሲያብራራ "ከሌላው ኅብረተሰብ የተሻለ ንቃተ ኅሊና አላቸው የሚባሉ፣ ወደፊት ተስፋ የሚጣልባቸው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ማየት ይቻላል:: እነዚህ ወጣቶች ከሰዓት በኋላ በካምፓስ ውስጥ ማግኘት ዘበት ነው:: አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጫት ቤት ያሳልፋሉ" ይላል::

## ወደፊት

ለውይይት መጽሔት አስተያየታቸውን የሰጡ አንድ እናት፤ ልጃቸው በጫት ሱስ የተጠመደ በመሆኑ ከቤታቸው ዕቃ እያወጣ በመሸጥ እንደተቸገሩ ይናገራሉ:: ለዚህም ጥፋተኛ አድርገው የሚከሱት መንግሥትን ነው:: መንግሥት የሥራ ዕድል ባለመፍጠሩ ልጆቻቸው የጫት ሱሰኛ እንደሆኑ ሐዘን በተቀላቀለው ስሜት ቅሬታቸውን ይናገራሉ:: "ጫት በአገሪቱ ኢኮኖሚና በጤና ላይ የሚያስከትለው ችግር በቀላሉ መታየት የለበትም:: መንግሥትም አስፈላጊውን ቁጥጥር ማድረግ አለበት:: ዛሬ በየመንደሩ፣ በየሥርቻው ሁሉ ጫት ቤት ተስፋፍቷል:: ስንት ቦታ ይደርሳሉ የተባሉ ወጣቶች እየመከኑ ተሰነካክለው የቀሩትን ቤት ይቁጠራቸው:: አንዳንዴም መንግሥት ሆን ብሎ የሚያደርገው ይመስለኛል" ይላሉ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶሲዮሎጂ መምህር ሆኑት ዶ/ር የራስወር አድማሴ ጫት ቃሚው እየበዛ መምጣቱን አስመልክተው ያቀረቡትን ጥናት ማኅበራዊ ጥናት መድረክ "The Khat Conundrum in Ethiopia: Socio economic Impact and Policy Directions" በሚል ርእስ አሳትሞታል::

ይሁን እንጂ የግለሰቦች ጫት የመቃም፣ የማምረት የመሸጥ መብት መከበር ያለበት ቢሆንም ግን መቼ፣ ለማን መሸጥ እንዳለበት መንግሥት በኃላፊነት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመወያየት በሥራ ጊዜና በጤና ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ከወዲሁ መፍትሔ መፈለግ አለበት:: "ጫትን መንግሥት በምርቃና ትውልዱን ወደማይሆን ሕይወት ውስጥ ለማስገባት ወይስ ለሀብት ማግኛ ነው እየተጠቀመበት ያለው? ይህ መፈተሽ አለበት" አለበለዚያ የጫት ቃሚው መብዛት ለአገሪቱ ዕድገት ሳይሆን ውድቀት እንደሚያስከትል ለመናገር ነቢይ መሆንን አይጠይቅም::



ታዬ ንጉሤ (ዶ/ር)

# ማኪቬሊያዊ ፖለቲካ እና መዘዙ

በቅርቡ ከአንድ የቅርብ ጓደኛዬ ጋር ስለ ፖለቲካ ስንጨዋወት ቀጥሎ የተመለከተውን ወግ አወጋኝ:: በአንድ ወቅት በምሥራቅ ኢትዮጵያ የሆነ አካባቢ ነው፤ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ከሕዝቡ ጋር ስብሰባ ሲያካሂዱ ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ አዛውንት አስተያየት ለመስጠት ብድግ ይሉና ፊታቸውን ወደ ተሰብሳቢው በመዞር በጣታቸው ወደ ዐይናቸው እያመለከቱ በኦሮምኛ "kuni maali?" ("ይህ ምንድን ነው?") ብለው ይጠይቃሉ:: ተሰብሳቢውም "Hay! ija dhaa" (ዐይን ነዋ) ብለው ይመልሳሉ:: አዛውንቱም መልሰው "abeden, ija mitii; hudu dhaa" (በፍጹም ዐይን አይደለም "ቂጥ" እንጂ) ብለው ሲሉ የስብሰባው አዳራሽ በሳቅ ተናጋ:: ቀጥለውም ይኸውላችሁ የኢሕአዴግ ፖለቲካም እንዲህ ዐይን ያወጣ ክህደት ነው ብለው የምሳሌያቸውን ጭብጥ አስረዱ::

እንዲሁም በቅርቡ አንድ ሰው ሲያወጋኝ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በቅርቡ የተከሰተውን ሕዝባዊ አመጽ ተከትሎ፣ በመንግሥት ተቋሞች ውስጥ ለሚገኙ የአመራር አካላት በተሰጠው "የጥልቅ ተሐድሶ" ሥልጠና ላይ የነበረው አንዱ አጀንዳ በዚህ የኢሕአዴግ የአገዛዝ ሥርዐት ውስጥ "ዕውን የሕወሓት የበላይነት አለን?" የሚል ነበር:: እኔም መልሼ ታዲያ የሥልጠናው ተሳታፊዎች በአጀንዳው ላይ የነበራቸው ምላሽ እንዴት ነበር? ብዬ ጠየቅሁት:: እሱም የስብሰባውን ግልጽነት እያደነቀ አንዳንድ ተሳታፊዎች በመከላከያና የደኅንነት ቁልፍ የሆኑ መንግሥታዊ ተቋማት አመራር ያሉትን ሰዎች በመጥቀስ በርግጥም የሕወሓት የበላይነት እንዳለ አስተያየት ሰነዘሩ አለ:: ነገር ግን አለ፣ መድረኩን ከሚመሩት የሕወሓት አባላት በተለይም አንዱ በዕድሜ ወጣት የሆነ እጅግ ተናጋሪ ካድሬ (በእሱ አባባል "ትንሹ መለስ") የተለያዩ የመከላከያ ሐሳቦችን እየጠቀሰ የሕወሓት የበላይነት እንደሌለ አስረዳ:: እኛም ተቀበልነው አለኝ:: ይህን ሲለኝ ወዲያው በጭንቅላቴ ውስጥ የመጣብኝ በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኩት የአዛውንቱ ምሳሌያዊ አነጋገር ነበር::

አንዳንድ ሰዎች "ፖለቲካ የመዋሸት ስልት ነው" ብለው ሲናገሩ እሰማለሁ:: እንዲያውም ማኪቬሊ የተባለው ጣሊያናዊ ፈላስፋ "ዘ ፕሪንስ" በሚለው ዝነኛ መጽሐፉ ውስጥ እንደሚያትተው፣ አንድ ውጤታማ ገዢ "የቀበሮና የአንበሳ" ባሕሪያትን አጣምሮ ሊይዝ ይገባል ይላል:: የቀበሮው ባሕሪ የሚወክለው ማጭበርበርና ማስመሰልን ሲሆን፤ የአንበሳው ባሕሪ የሚወክለው ደግሞ የኃይለኝነትንና በጉልበት የማንበርከክ ሥልትን ነው:: ማኪቬሊ ለገዢዎች የሥልጣን ጊዜን እንዴት ማስረዘም እንደሚችሉ ሲመክር፡ እየቀጠፉ፣ እያጭበረበሩና በኃይል እየደቆሱ መግዛት እንደሚገባቸው አበክሮ ያስገነዝባል:: ባጭሩ ማኪቬሊያዊ ፖለቲካ አስመሳይነት፣ ማጭበርበርና ኃይልን ያማከለ የፖለቲካ ስልት ነው::

ባለፉት ሦስት ዐሥርት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በሥልጣን ላይ የቆየው የኢሕአዴግ ሥርዓት በጥሞና ሲመረመር ማኪቬሊያዊ የአገዛዝ ማኑዋልን ታማኝነት እየተረጎመ የሚገኝ ይመስላል:: እንደሚመስለኝ ይህም የሆነበት የራሱ ታሪክ አለው:: ሲጀምር የኢሕአዴግ አስኳል የሆነው ሕወሓት ኢትዮጵያ የሚል የፖለቲካ አጀንዳ አልነበረውም:: ኢትዮጵያ የሚለው በፖለቲካ አጀንዳነት የመጣው በትግሉ የመጨረሻ ደቂቃዎች ላይ ኢትዮጵያን የሚያህል አገር የማስተዳደር ኃላፊነት ሳያስበው በእጁ ላይ በመውደቁ ነበር:: ኢሕአዴግ የሚለውም ድርጅት የወቅቱን የፖለቲካ ጥያቄ ለመመለስ በጥድፊያ የተዋቀረ የቶሎ ቶሎ የይድረስ ቤት ነው::

የኢሕአዴግ ማኪቬሊያዊ ፖለቲካ ሥረ መሠረቱም ኢትዮጵያን በተለያዩ "ዘውጎች" ከፋፍሎ በመግዛት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ይገኛል:: ለዚህም የመከራከሪያ ነጥቡ ኢትዮጵያ ስትመሠረት "ሉዓላዊ" በሆኑ ዘውጎች በኃይል ወደአንድነት እንዲመጡ ተገደው ነው የሚል ነው:: ሰሞኑን ታትሞ በገበያ ላይ የዋለው የደራሲ ሀብታሙ አለባቸው "ታላቁ ተቃርኖ" የሚል መጽሐፍ ይህን የመከራከሪያ ነጥብ ትንሽ ወሰብሰብ አድርጎ የአካዳሚ ገጽታ አልብሶት ብቅ ብሏል:: በርግጥ መጽሐፉን ላየው ራሱ በተቃርኖ ሐሳቦች የተሞላና የተመሠረተበትም ኀልዮት የተፋለሰ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ይወጣል:: ለምሳሌ መጽሐፉ በመጀመሪያ ገጾቹ የሥራውን አግባብነት ሲያስረዳ፣ ይህን ሥራ ለየት የሚያደርገው አወቃቀሩ ቀደም ሲል በሶሲዮሎጂ የትምህርት መስክ ከፍተኛ ተጽዕኖ የነበረውን የ"ስትራክቸራል ፈንክሽናሊዝም" አተያይ ላይ እንደተመሠረተ ይገልጻል:: እዚህ ላይ የመጽሐፉን ዐቢይ ተቃርኖ ልብ ልንል ይገባል:: መሠረቱን በዚህ የምዕራባውያን ሥነ ዕውቀት በሆነው "ስትራክቸራል ፈክሽናሊዝም" ላይ ጥሎ ሲያበቃ፣ በመጽሐፉ የውስጥ ገጾች ላይ ግን የምዕራባውያንን ሥነ ዕውቀት በአጠቃላይ በሌሎች ሕዝቦች ላይ የፈጸመውን የእእምሮ በደል ሲኮንን ይታያል::

በነገራችን ላይ ይህ "የስትራክቸራል ፈንክሽናሊዝም" ዕይታ በአሁኑ ወቅት በሶሲዮሎጂ የትምህርት መስክ ተቀባይነት አጥቶ ወደ ቅርጫት ከተወረወረ ሰንበትበት ብሏል:: ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፉ ወደ ዝርዝር ሐሳቦች ሲገባ የተለያዩ ሶሲዮሎጂካል ጽንሰ ሐሳቦችን እያነሳ ለመከራከር ይሞክራል:: ሆኖም ግን ክርክሩ በመንገደኛ ሶሲዮሎጂካል ዕውቀት (common-sense sociological knowledge) ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የመጽሐፉን ጭብጥ የበልጥ አጨቅይቶት ይታያል:: በሌላ በኩል የመጽሐፉ ዐቢይ ግድፈት የኢትዮጵያን ታሪክ በተቃርኖ ክስተቶች መሞላቱ በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ተለይቶ የወረደ ልዩ እርግማን አድርጎ መመልከቱ ነው:: ለመሆኑ የየትኛው አገር ታሪክ ነው ከተቃርኖ ክስተቶች ነጻ የሆነው? ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ጫፍ ብታስስ አንድም አገር ከዚህ የተቃርኖ ክስተቶች የጸዳ ሆኖ አይገኝም:: ይህ ተቃርኖ ከሌለው አገሩ ታሪክ የለውም ማለት ነው!!

ወደፊት ሀያሲዎች በዚህ መጽሐፍ ላይ ያለውን ዝርዝር ፍልሰት በስፋት እንደሚዳስሱት ተስፋ አደርጋለሁ:: አሁን ወደ ዋናው ነጥብ እንመለስ - ኢሕአዴግ ማኪቬሊያዊ ፖለቲካን በኢትዮጵያ ውስጥ ሲተገብር በዋነኛነት የተጠቀመበት ስልት "የፍርሃትና የጥርጣሬ ባሕል" (Culture of Fear and Suspicion) በኅብረተሰቡ ውስጥ በስፋት እንዲሰፍን በማድረግ ነው፤ ግምገማን ልብ ይሏል:: በርግጥ በዚህች አጭር ጽሑፍ ውስጥ የሥርዓቱን ማኪያቬሌያዊ ድርጊቶች በዝርዝር ማቅረብ አስቸጋሪ በመሆኑ አንኳር በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለማተኮር ይሞክራል::

"ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል" የሚል አንድ የቆየ አባባል አለ:: የዚህን አባባል ትክክለኛነት የምንረዳው የዚህ ሥርዓት ዋና ቀኖና በሆነው "የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት" የሚለውን ዲስኩር በጽሞና ስናይ ነው:: ከዚህ ቀደም በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ላይ በጻፍኳቸው መጣጥፎች የዚህን አባባል ተቃርኖ ለማሳየት ሞክሬያለሁ:: ያውም እነኚህ ሦስት ቃላት፣ ማለትም "ብሔር፣ ብሔረሰብ እና ሕዝብ" የሚባሉት በትክክለኛ ትርጓሜቸው ሲታዩ ሦስት የተለያዩ የሕዝብ ስብስቦችን እንደሚያመለክትና በምንም ዓይነት እኩል ያልሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች ሆኖ እያለ፤ ይህን እኩልነት ብሎ በተደጋጋሚ ሲለፈፍ፣ አሁን አሁን ለሕዝቡም ቢሆን እውነት እየሆነ የመጣ ይመስላል:: በተግባር ደግሞ ያለው እውነታ እጅግ ወሰብሰብ ያለና ይህን የእኩልነት ዲስኩር በምንም ዓይነት አመላካች እንዳልሆነ የለት▶

> ***የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየን፣ ቀደም ሲል ለይስሙላም ቢሆን የነበረው የብዙሃን ፓርቲ ሥርዓት ቀስ በቀስ ደብዛው ጠፍቶ በአንድ ጠቅላይና "አውራ" ፓርቲ መዳፍ ሥር ወድቆ መገኘቱን ነው***

ተዕለት ሕይወታችን ይመሰክራል::

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የእኩልነት ዜማ እንኳን በአገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ የተለያዩ ሕዝቦች ቀርቶ ራሱ ኢሕአዴግ ብሎ ባዋቀራቸው አራት የጎሣ ፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ እንኳን እንደማይሠራ ሁሉም የሚያውቀው ያደባባይ ምስጢር ነው:: በእውነቱ ከሆነ ኢሕአዴግ የሚለውን የለበጣ ስያሜ ሲፋቅ የምናገኘው ሕወሓትን ነው:: በተግባርም እንደሚታየው የተቀሩት ድርጅቶች ሌሎችን ክልሎች የሚያስተዳድሩ "የሕወሓት እንደራሴዎች" እንጂ የራሳቸው ህልውና ያላቸው ነጻ ድርጅቶች በፍጹም አይደሉም:: ድርጅቱ ከአንድ ወጥ የፖለቲካ ፓርቲነት ይልቅ የተለያዩ የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ ሆኖ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ የሚያስረዳን አንድነትና እኩልነትን የማይሻ የትምክህት እና የጠባብነት ወይም የጎሠኝነት ስሜት ተጠቂ መሆኑን ነው:: የሚገርመው ግን ይህን የትምክህትና የጥበት ባሕሪ በሌሎች ላይ ተለጥፎ ሲታይ ነው::

ይህ ሥርዓት እንደ ዋነኛ ድል ከሚቆጥራቸው ክንውኖች አንዱ የዴሞክራሲን ሥርዓት ለሕዝቡ ማጎናጸፉን ነው:: ሁላችንም እንደምንረዳው የዴሞክራሲ ጽንሰ ሐሳብ እጅግ ሰፋ ያለና የተወሳሰበ የፖለቲካ እሳቦት ነው:: ይህም ሆኖ የጽንሰ ሐሳቡ ዋነኛ መለኪያዎች ሆነው ከሚወሰዱት መካከል አንድን መንግሥት የሚያዋቅሩት ሦስቱ አካላት፤ ማለትም የሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈጻሚውና ሕግ ተርጓሚው መለያየትና እርስ በርሳቸው መጠባበቅ እንደሆነ ይታወቃል:: አሁን ባለው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ግን በፍጹም አንዱን የመንግሥት አካል ከአንዱ መለየት የማይቻልና ሁሉም የአንድ ሳንቲም የተለያዩ ገጽታዎች ነው የሚመስሉት:: ይህ ጉዳይ አሁን አሁን በመርሕ ደረጃ እንኳን መቀመጡ ተረስቶ ገለልተኛ የመንግሥት ተቋማት ናቸው ተብሎ ከተደነገጉት እንደ ፖሊስና የፍርድ ቤት ተቋማት ደጃፎችና ግንቦች ላይ የገዥው ፓርቲ መፍክሮች ተንጠልጥለው ማየት የተለመደ ሆኗል:: እዚህ ላይ እንግዲህ የዴሞክራሲ ዋና መሠረቱ ተናደ ማለት ነው::

ሌላው ከዚህ የዴሞክራሲ ጽንሰ ሐሳብ ጋር የሚያያዘው፣ በተወሰኑ ዓመታት ልዩነት የሚካሔደው ነጻና ገለልተኛ ምርጫ ነው:: በዚህ ረገድም ቢሆን የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየን፣ ቀደም ሲል ለይስሙላም ቢሆን የነበረው የብዙሃን ፓርቲ ሥርዓት ቀስ በቀስ ደብዛው ጠፍቶ በአንድ ጠቅላይና "አውራ" ፓርቲ መዳፍ ሥር ወድቆ መገኘቱን ነው:: ይህንንም ተከትሎ በየአምስት ዓመቱ የሚካሔደው ምርጫ ገዢው ፓርቲ መቶ በመቶ "እያሸነፈበት" በአሁኑ ሰዓት ትርጉም አልባ እየሆነ መጥቷል:: እዚህም ላይ ዴሞክራሲ ባዶ ፕሮፖጋንዳ ሆኖ ቀረ ማለት ነው::

ሦስተኛው የዴሞክራሲ ገጽታ ሰዎች ሐሳባቸውን በነጻ የሚገልጹበት የሚደያ ሥርጭት ነው:: ይህንን በሚመለከት ራሱ ገበያው የሚነግረን ብዙ ነገር አለ:: ዛሬ በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ እጅግ በተቀራረበ ርቀት ላይ እንደ አሸን ፈልቶ የሚያገኙት ሥጋ ቤት፣ ጫት ቤት፣ መጠጥ ቤትና ፖሊስ ጣቢያዎች ሲሆን (በነገራችን ላይ የፖሊስ ጣቢያዎች ብዛት ከሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች ቁጥር ጋር በፍጹም የሚወዳደር አይደለም፤ ያውም እንደ አዲስ አበባ ባለ ንጽሕናዋ የተጓደለ ከተማ) መጽሔትና ጋዜጣ ለመግዛት ግን ስንት ሚሊዮን ሕዝብ በሚኖርባት ከተማ ውስጥ የሚያገኙት ከሦስትና ከአራት አማካይ ቦታዎች የዘለለ አይሆንም:: ለዚያውም የሚያገኙት የቁንጅና፣ የስፖርትና የሜድካል ጋዜጣና መጽሔቶችን ነው:: ይህ አፍራሽ አዝማሚያ ምን ያህል በሕዝቡ የንባብ ባሕል ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ መገመትም አያዳግትም::

ከዚህ የዴሞክራሲ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ሥርዓቱ ሌላው "ዐቢይ ድል" ነው የሚለው ራስን በራስ የማስተዳደር ዕድልን የሚያጎናጽፈውን የፌደራል አወቃቀርን ነው:: በርግጥ ይህ ሥርዓት በዋና ተቃዋሚዎች ከሚወገዝበት አንዱ ምክንያት አገሪቱን በጎሣ በተሸነሸኑ ክልሎች በመከፋፈልና ለእነሱም "ሰፊ የሆነ ራስን በራስ የማስተዳደር እስከ መገንጠል" መብት በመስጠቱ ነው ተብሎ ይታመናል::

ይህም ቢሆን በተግባራዊነቱ ላይ ጥልቅ ጥያቄ ያጭራል:: ምክንያቱም በተለያዩ ክልሎች በተለያየ ጊዜ የሚወጡት ዐዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከአንድ ምንጭ የፈለቁ ሐሳቦች በመሆናቸው ነው:: እውን እውነተኛ የሆነ የራስ በራስ አገዛዝ ባለበት አገር እንዴት ሁሉም ክልሎች በአንድ ዓይነት ቅኝት ሊቃኙ ይችላሉ? እንደ እውነቱ ከሆነ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአንድ ጠቅላይ አገዛዝ ሥር መውደቋ የአደባባይ ምስጢር ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ይህ በጎሣ ላይ የተመሠረት የአስተዳደር ክፍፍል ከመቼውም ጊዜ በተለየ መልኩ የማኅበረሰብ ግጭቶችን እንደ አሸን አፍልቷል:: ብዙ ጊዜ እንደምንሰማው የድንበር የይገባኛል ግጭት የሚከሰተው በሉዓላዊ አገሮች መካከል ነበር:: አሁን ግን "ዕድሜ ለጎሣ ፌደራሊዝም" በኢትዮጵያ ውስጥ እየሆነ ያለው የድንበር የይገባኛል ግጭት በአንድ አገር ውስጥ ባሉ የአስተዳደር ክልሎችና ጎጦች ሆኗል::

በኢኮኖሚው ረገድ በመንግሥት ሚዲያ ከምንሰማው የእጥፍ አኃዝ ዕድገት በተጻራሪ በውኑ የገበያ ዓለም የሚታየው እውነታ መሠረታዊ ሸቀጦች በራሽን ለዜጎች የሚከፋፈሉበት፣ በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ለረኀብ የሚጋለጡበት፣ የዋጋ ንረት በመቶ ፐርሰንቶች የሚወጣበት፣ ከምርታማነት ይልቅ ድለላ፣ ኪራይ ሰብሳቢነት፣ ሙስና በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉና እየተስፋፉ የመጣበት የተንጋደደ (misguided) ኢኮኖሚ ነው::

በማኅበራዊው ዘርፍ ደግሞ የባሕል ዝቅጠት፣ ዋልጌነት፣ ሥራ እጥነት፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ ወንጀለኛነት እና የሱስ ተጠቂነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰበት ሁኔታ ነው::

እንደኔ አተያይ እነኚህና ሌሎች በቦታ ጥበት ምክንያት ያልተጠቀሱ ሺሕ የሚሆኑ የማኪቬሊያዊ የፖለቲካ ድርጊቶች አሁን ይህን ሥርዓት ለገባበት አጣብቂኝ ዋና ምክንያት ይመስሉኛል:: "በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ አሁን የገባበትን ቀውስም ለመፍታት እየወሰደ ያለው የኀይል እርምጃና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ አገሪቱን በከባድ የፖለቲካ ድባብ ሥር እንድትወድቅ አድርጓታል:: የሕዝቡን ቅሬታና ተቃውሞ ወደ ጎን በመተው በራሱ ድርጅታዊ አሠራር መፍትሔው በራስ ላይ የሚካሄድ "ጥልቅ ተሐድሶ" ነው በሚል የሕዝቡን መሠረታዊ ጥያቄ ለማድበስበስ ይሞክራል::

ሲጀመር "የጥልቅ ተሐድሶ" ዲስኩር መሠረታዊውን የፖለቲካ ጥያቄ በማድበስበስ ወደ ተራ አስተዳደራዊ ጉዳይ አውርዶ ያገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም የተደረገ ማኪቬሊያዊ የፖለቲካ ሤራ ነው:: በመጨረሻ ውጤቱንም እንዳየነው ጥቂት "የሕወሓት እንደራሴዎች" ሥልጣን ከመሸጋሸግ ውጪ ሌላ ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳላመጣ በሙሉ ልብ መመስከር ይቻላል:: "አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" እንደሚባለው ብሂል ቀደም ሲል የነበረው የፖለቲካ ችግር ባግባቡ ባለመፈታቱ በቅርቡ አመጹ እዚህም እዚያም መልሶ ብቅ ጥፍት ሲል ይስተዋላል::

እንደ እውነቱ ከሆነ ለአገሪቱም ለዘለቄታው ጠቃሚ የሚሆነው እርምጃ አሁን አገሪቱ የገባችበትን ችግር መንስኤ በጽሞና እና በተረጋጋ መንፈስ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ በመመርመር አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ነበር:: አሁንም ቢሆን ይህን ለማድረግ እውን ቅንነቱና ብልህነቱ ካለ ጊዜው የረፈደ አይመስለኝም::

*ዶ/ር ታዬ ንጉሤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል ባልደረባ ናቸው::*
*በኢሜል አድራሻቸው tayesosa@yahoo.com ላይ ይገኛሉ::*



መስከረም አበራ

# ወይ አዲስ አበባ....!

## ቅድመ-ነገር

ታሪክ የሰው ልጆችን ያለፈ የሕይወት ስንክሳር መርምሮ፣ መጭው ትውልድ ካለፈው ድካምም ብርታትም እንዲማርና የተሻለ ዓለም እንዲፈጥር ማስቻልን ያለመ የጥናት መስክ ነው:: የአገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ አተናተን ዘይቤ ክፉኛ በታሪክ ላይ የተጣበቀ ነው:: ፖለቲካችን ታሪክን የሙጥኝ ማለቱ በራሱ ጥፋት የለውም:: አስቸጋሪ የሚሆነው ታሪካችንን ለወቅታዊ ፖለቲካችን ትንታኔ በምንጠቀምበት ጊዜ ሥነ ልቦናችንን አብረን ማጋመዳችን ነው:: የአገራችን ፖለቲካ ውቃቤ እንዲርቀው ካደረጉ ነገሮች ዋነኛው ታሪክን እና ፖለቲካን በየግል ሥነ ልቦናችን ለንቅጠን፣ የሥነ ልቦናችን ደመነፍስ ያቀበለንን የስሜት ግንፍላት በምክንያታዊነት ላይ አንግሰን መንጎዳችን ይመስለኛል::

ወደስሜታዊነት የሚመራን ፖለቲካዊ ሥነ ልቦናችን ምንጩ ሲመረመር ወይ ዝቅተኝነት የሚያንገላታው የተበድያለሁ እዬዬ ነው ወይ እብሪት የነገሠበት የገዥ ነኝ የበላይነት ስሜት ነው:: የዚህ ፖለቲካዊ ሥነ ልቦና ምንጩ ደግሞ ደመነፍሳዊ ማነብነብን እንደ ሁነኛ የርዕዮተዓለም ትጥቅ ይቆጥር የነበረው የስልሳዎቹ ትውልድ ፖለቲካዊ ሥነ ምኅዳር ነው:: ያ ትውልድ አገሩ ፀንታ ቆማ ዘመን የተሻገረችበትን አገረሰባዊ አዕማድ፣ ፖለቲካዊ መስተጋብር፣ ማኅበራዊ ቁርኝት፣ ኢኮኖሚያዊ ትንቅንቅ ለመመርመር ጊዜ ሳይወስድ በነስታሊን ወጭት የኢትዮጵያን ወጥ ሊወጠውጥ የተነሳ፣ እንደ ቤቱ ሳይሆን እንደ ጎረቤቱ ሊኖር የፋተረ ነበር:: በመሆኑም ኢትዮጵያ ከሶቬት ኅብረት ቀድማና ተለይታ በራሷ የታሪክ ዱካ ከመጓዟ የተነሳ የተሰበዘችበትን ፖለቲካዊ ሰበዝ ልዩ ተፈጥሮ ለመመርመር የማርክስ/ሌኒንን ድርሳን ማነብነቡ ፋታ አልሰጠውም ነበር::

የማነብነብ ቱርፋቱ ዕውቀት የሚያመጣው እርጋታ እና ብስለት አይደለምና ያነብናቢነት ዕውቀት ያቀበለው ዘረኝነት ክፉ እንክርዳድ በአገራችን የፖለቲካ ማሳ ላይ ተዘራ:: አገሪቱ የድሆች እስር ቤት መሆኗ ቀርቶ "የብሔረሰቦች እስር ቤት ነች" ተባለ:: አንድ ብሔር አሳሪ ሌላው ብሔር ታሳሪ ተደርጎ የአጋች ታጋች፣ የበዳይ ተበዳይ ፖለቲካ እንደ ኤርታሌ ድንገት ገንፍሎ ይንተከተክ ያዘ! የኢትዮጵያ ታሪክ ሁሉ የመበደል መበደል ድራማ ብቻ እስኪመስል ድረስ ተበደልኩ ባይ ሙሾ አውራጁ በዛ:: አንድ ብሔረሰብ በነሲብ በዳይ ሌላው ብሔረሰብ በጅምላ ተበዳይ ሆኖ የጎሳ ጥላቻ ሰልፍ፣ የመነጣጠል ጎራ፣ የጥርጣሬ መንፈስ በአገራችን የፖለቲካ አየር ረበበ:: ሁሉም የተሰለፈበት የዝቅተኝነት ወይ የበላይነት ፖለቲካዊ ሥነ ልቦና እንደመራው ብድግ ብሎ ፖለቲካን መተንተን ጀመረ:: ፖለቲካዊ ስድነት በአገሪቱ ነገሠ! የገዛ አገርን ቅኝ ገዥ ማለት ከአዋቂነት ተጻፈ:: የአገርን ትውፊት ማቃለል ዘመናዊነት ሆነ:: የእነገብረሕይወት ባይከዳኝ ምጡቅ ልቦና ለአገራችን ችግር አገርኛ መንስኤ እና መፍትሔ የጠቆመበትን ድርሳን ትራስ አድርጎ ተኝቶ የነሌኒንን የጠብ ዶሴ ማገላበጥ፣ ውጭ ውጭውን ማለት የምጡቅነት መለዮ ሆነ::

> ያ ትውልድ አገሩ ፀንታ ቆማ ዘመን የተሻገረችበትን አገረሰባዊ አዕማድ፣ ፖለቲካዊ መስተጋብር፣ ማኅበራዊ ቁርኝት፣ ኢኮኖሚያዊ ትንቅንቅ ለመመርመር ጊዜ ሳይወስድ በነስታሊን ወጭት የኢትዮጵያን ወጥ ሊወጠውጥ የተነሳ፣ እንደ ቤቱ ሳይሆን እንደ ጎረቤቱ ሊኖር የፋተረ ነበር

ይህ የማነብነብ ደመነፍስ በጠመንጃ ታግዞ ሥልጣን ላይ ለመውጣት በሚፋትርበት ወቅት ያዋጋ ያጋድል የነበረው ደመ-ጠጭ ዛር በስተመጨረሻ ለሕወሓት ቆሞለት ሥልጣን ላይ ሰየመው:: ሕወሓት ከላይ ከተነሱት ሁለት ፖለቲካዊ ሥነ ልቦናዎች በተበድያለሁ መስመር የተሰለፈ ነበረና የሕወሓት ሥልጣን ላይ መውጣት ለተበድያለሁ ፖለቲከኞች ጥሩ የማላዘኛ መድረክ ፈጠረ:: የተበድየ ፖለቲካው ሰልፍ ፊታውራሪዎቹ ኦነግና ሕወሓት ፍቅራቸው ገመሬ እንዳየው ዝንጀሮ ድራሹ እስኪጠፋ ድረስ ሻዕብያን ሙሾ አውራጅ አድርገው በተበድየው ሙዚቃ ደረት ሲደቁ ባጁ! በአንጻሩ የበዳይነት ጦስ የወደቀበት የአማራ ሕዝብ የሚወረወርበትን የወቀሳ ፍላጻ ለመመከት የሚያስችል መድረክ እንኳን ተነፈገው:: በሌለበት የፖለቲካ ችሎት ወንጀለኝነቱ ተረጋግጦ የመገለል ክፉ ፍርድ ተፈረደበት:: በአገሩ ሁነኛ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ላይ እንዳይሳተፍ በግልፅም በስውርም እግድ ተጣለበት:: ሽግግር ቻርተር በማርቀቅ ቢሉ ቻርተሩን ሕገ መንግሥት በማድረጉ ሂደት ይህ ነው የሚባልውክልና ተነፈገው:: ያለፈው የአገሪቱ ክፉ ክስተት ሁሉ ተጠያቂ ተደረገ:: ታሪክም አማራውን ጭራቅ አድርጎ ለማሳየት ያስችላል ተብሎ ከተገመተበት ዘመን ይቆጠር ጀመር:: የሉሲ አገር ኢትዮጵያም የመቶ ዓመት ብላቴና ተደርጋ አረፈችው!

የሰው ልጆች ያለፈ ሁለንተናዊ የሕይወት ልምድ ታሪክ መባል ያለበት መቼ ነው የሚለው ነገር የሚያከራክረው ከቅርቡ ወደ ሩቁ ሲቆጠር ነው:: ታሪክ እንደ ጥናት መስክ የሩቁን ለማጥናት ይጓጓል እንጅ የቅርቡን በአያሌው የሚወስነውን የሩቁን ታሪክ ጥሎ የቅርቡን አንጠልጥሎ አይደናበርም:: የአገራችንን ፖለቲካ ቅጥ አምባር ያሳጣው ይኼው ብዙውን ጥሎ ጥቂቱን አንጠልጥሎ የመንጎዱ የእብድ እሩጫ ነው:: በደንባራ በቅሎ ቃጭል ሲጨመር ደግሞ በዚህ ላይ ስነልቦናችን ታክሎበት መመለሻችንን

በሚያስናፍቅ የቁልቁሊት ሩጫ ውስጥ ዶሎናል፤ ላለመደማመጥ አማምሎናል፤ ምክንያታዊነትን ለዘረኝነት አሰውቶ ፖለቲካችንን የሥነ ልቦና ቀውስ በሽተኞች መድረክ አድርጎታል::

የፊት አውራሪው ሕወሓት ወደ ሥልጣን መምጣት ገበያ ያደራለት የተበድዮ ፖለቲካ በዚሁ ሥነ ልቦና የተጠቁ አባብሉኝ ባይ ፖለቲከኞችን እያፈላ ይገኛል:: ቀደምት የበደል ፖለቲካ ቁስ-ገበዞች፣ የሕወሓት ባለንጀሮች እነ አቶ ሌንጮ ለታ እና ጓዶቻቸው ከሕወሓትም ተፋተው፣ ዕድሜ ብቻ ያደረጋቸውን፣ እንደስማቸው የሚታወቁበትን የበደል ትረካ ፖለቲካ ጥቅም ጉዳት መዝነው፣ ዛሬ የተለየ መንገድ ይዘናል ቢሉም የዘሩት ዘር ግን እነሱ የተቀየሩ ዕለት የሚቀየር አይደምና በዝቶ ተባዝቶ በቦታው አለ:: የነ ሌንጮ ለታ የበደል እየየ ስብከት ዛሬ መምህሩን የሚያስከነዱ የጥላቻ ደቀመዛሙርትን አምርቷል:: በእንዲህ ያለው ደዌ የተለከፉ በአብዛኛው የምሁርነትንም ካባ የደረቡ ልሂቃን የሚደውሩት የከረረ የኦሮሞ ብሔርተኝነት ፖለቲካ የሕመሙን ክፋት ከሚያሳዩ ብዙ ምልክቶች አንዱ በቅርቡ የተያዘው የአገራችን ዋና ከተማ አዲስ አበባ የአንድ ብሔር (የኦሮሞ) ተቀዳሚ ንብረት ነች የሚለው ጉዳይ ነው::

## የብቻ አዲስ አበባ?

የአዲስ አበባ ቀደምት ነዋሪዎች የኦሮሞዎች ናቸው በሚለው እሳቤ እርግጠኛ ተሁኖ አዲስ አበባም መተዳደር ያለባት በኦሮሚያ ክልል ሥር ነው የሚል ክርክር በቅርቡ ተፋፍሞ ማነጋገሩን ቀጥሏል:: ይኼው የአዲስ አበባ ቀደምት ነዋሪነት እና ተቀዳሚ ባለቤትነት ተረክ ሌሎች የዚሁ እሳቤ ውላጅ የሆኑ መብት ጥያቄዎችን ያስከትላል:: በአዲስ አበባ ላይ ሕገ መንግሥታዊ የልዩ ጥቅም ባለመብትነት ጉዳይ፣ የአዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ መገኘት ኦሮሚያን በአዲስ አበባ ላይ የባለቤት ፀዳል ለማላበስ በቂ ሁኔታ ነው የሚሉት ክርክሮች መነሻቸው ይኼው የቀደምት ነዋሪነት ጉዳይ ነው::

የኦሮሚያ ክልል አዲስ አበባ ላይ ጅኦግራፊያዊ እና ታሪካዊ ባለቤት እንደሆነች የሚወተውተው ክርክር ዋናው መሠረቱ ኦሮሞዎች በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ኖሩ የአዳም ዘሮች ናቸው የሚለው ተረክ ነው:: በአዲስ አበባ ላይ የኦሮሞዎችን ቀደምት ነዋሪነት ትርክት ተአማኒ/ኢ-ተአማኒነት ማስረገጥ በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ መካከል ባለው "የባለቤት/ባለ ልዩ መብትነት" ጉዳይ ለሚነሱ ንትርኮች በታሪካዊ መዛግብት የተደገፈ ማስረጃ ሊቀርብ ያስፈልጋል:: በታሪክ ምስክርነት ሳይታገዝ የሚቀርብ የኔነው የኔነው ሽሚያ ያደገን ሰው እንደ ሕፃን ልጅ ሁሉን ነገር ለእኔ የሚያስብል የሥነ ልቦና ቀውስ ምልክት እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም!

## "ተው ማነህ ተው ማነህ.."!

ባለፈው ሳምንት OMN በተባለው ቴሌቭዥን የተጋበዙት ፀጋዬ አራርሳ "በ1800 ዓ.ም. መቶ ፐርሰንቱ የአዲስ አበባ ነዋሪ ኦሮሞ ነበረ፤ አሁን ግን በወራሪዎች ግፍ ተገፍቶ ተገፍቶ ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች ውስጥ ዐሥራ ዘጠኝ በመቶው ብቻ ኦሮሞ እንዲሆን ተደርጓል ይላሉ::" የዚህ ክርክራቸውን ታሪካዊ ማስረጃ አብረው አልጠቀሱም:: ሆኖም ክርክሩ አዲስ አበባ ሰው ማኖር ስትጀምር ለመጀመሪያ ጊዜ የኖሩባት ኦሮሞዎች ናቸው የሚለውን ተረክ ለማጠናከር የተመዘዘ ሐሳብ እንደሆነ መረዳት አይከብድም::

በ1800 የአዲስ አበባ መቶ ፐርሰንት ነዋሪ ኦሮሞ ብቻ እንደ እንደሆነ ያውም ምሁር በተባለ ሰው አፍ ተሞልቶ ሲነገር ታሳቢ መደረግ ያለበት ነገር ይህን ያህል አስተማምኖ የሚያናግር የሕዝብ ቆጠራ በ1800 ያካሄደው አካል ማን ነው? ድሮ ቀርቶ ዛሬ የአገራችን የሕዝብ ቆጠራ የትክክለኝነት ደረጃ እስከ የእንትንት ምድር ባለቤት እንቶኔ ደግሞ መጻተኛ የሚያስብል ነው ወይ? ያኔ ይቅር ዛሬ በኮምፒውተር ዘመን የአገራችን ሕዝብ ቆጠራ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ የገባበት ጠፋ የሚባልበት፣ የበዛው አንሶ ያነሰው በዝቶ የሚቀርብበት እንደሆነ በደንብ የምናውቀው የቤታችን ጉድ ነው:: ታዲያ በ1800 አዲስ አበባ ላይ የታየ የአዳም ዘር ሁሉ አንድ ሳይቀር ኦሮሞ ነበር ማለት ሊበሉ ያሰቧትን አሞራ ጅግራ የማለት የሥነ ልቦና ቀውስ ካልሆነ ትርጉሙ ምንድን ነው? ደግሞስ እንዴት ባለ ምትሃት ነው በአንድ ምድር ላይ በስህተት እንኳን አንድ ሰው ሳይደባለቅ ኦሮሞ ብቻ ሊሰፍር የሚችለው? እሽ ይሄም በሆነ ምትሃታዊ ኀይል ምክንያት ሆነ እንበልና የ1800 አሰፋፈር የአሁኗን አዲስ አበባ የባለቤትነት መብት ሊወስን የበቃው እንዴት ነው?

ዛሬ ላይ ተቁሞ፣ ሁለት ሦስት ምዕተ ዓመት ወደኋላ ተጉዞ፣ የከተማ ባለቤትነትን መብት መወሰን ከተቻለ በዚሁ ስሌት ከዐሥራ ስምንተኛው ምዕተ ዓመትም ወደኋላ መሄድና የባለቤትነት ጥያቄ ማንሳት ሊቻል ነው ማለት ነው:: ከዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ወደኋላ ሲኬድ ደግሞ አዲስ አበባ ላይ ቀርቶ መላ ኦሮሚያ ላይም የኦሮሞ ሕዝብ እንዲህ በገፍ አልሰፈረም ነበርና በአሁኗ ኦሮሚያ ላይ ልዩ ጥቅም ሊጠበቅለት የሚገባ ሌላ ቀደምት የመሬት ባለቤት ሕዝብ ፍለጋ መኳተን ሊያስፈልግ ነው:: ነፍሱን ይማርና ጋሼ አሰፋ ጫቦ "ተው ማነህ ተው ማነህ የተኛው አለ ትቀሰቅሰለህ" ይል የነበረው እንዲህ ያለውን ነገር ነበር:: ዛሬ ሀብታምነቷ፣ ለምለምነቷ፣ ስፋቷ፣ የሕዝብ ብዛቷ እየተጠቀሰ በአክራሪ የኦሮሞ ብሔርተኞች ዘንድ "ዋ! እንዳንገነጠል" ዓይነት ማስፈራሪያነት የምትውለዋ የኦሮሚያ ምድር ከማንም ዘር ጋር አብራ ያልተወለደች፣ ይልቅስ በፊተኛው ዘመን ሌሎችን ሕዝቦችን ይዛ እንደኖረችው ሁሉ ከጊዜ በኋላ ደግሞ በተፈጥሯዊው የሰው ልጆች የመውረር መወረር አይቀሬ ክስተት ኦሮምኛ ተናጋሪ ወገኖችንም ተቀብላ ያስተናገደች ምድር እንደሆነች ታሪክ አገላብጦ ማወቅ ያስፈልጋል::

## ታሪክ ምን ይላል?

የመካከለኛውን ዘመን የአገራችን ታሪክ ግልፅ አድርገው ከጻፉ ጸሐፍት አንዱ አቶ ይልማ ደሬሳ ናቸው:: ጸሐፊው "የኢትዮጵያ ታሪክ፤ በዐሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን" በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ ለኦሮሞ ሕዝቦች ወደ መሃል እና ሰሜን ኢትዮጵያ የመስፋፋት ታሪክ የመደቡት ገፅ አነስተኛ ቢሆንም በጥሩ ሁኔታ አቅርበውታል:: እግረመንገዴን ይህን መጽሐፍ ያላነበበ አንባቢ ቢያነበው እመክራለሁ:: በያዝነው አጀንዳ ላይ በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ እንዲኖር ስለሚያስፈልግ ሰፋ ተደርጎ የተቀመጠውን ማስረጃ ከሥር መሠረቱ ማቅረብን መርጫለሁ:: አቶ ይልማ የኦሮሞን ሕዝብ የመስፋፋት ታሪክ ሲያስረዱ በምሥራቅ አፍሪካ ከታየበት ዘመን ጀምረው እንዲህ ይተርካሉ::

"ኦሮሞዎች ከመቼ ጀምሮ በምስራቅ አፍሪካ መኖር እንደ ጀመሩ፣ እነሱ በዛ ስፍራ ከመስፈራቸው በፊት በቦታው የነበሩ ሰዎች ማንነት በውል ባይታወቅም በዐሥረኛው ክፍለ ዘመን ሶማሌ የተባለው ነገድ ከታጁራ ሰርጥ አቅጣጫ ባነሳባቸው ተግዳሮት የተነሳ ወደ ደቡብ እና ምሥራቅ በመጓዝ በዋቢ ሸበሌና ጁባ ወንዞች መሃከል ቤናዲር በተባለው ስፍራ እና በቆላማው ባሌ ሰፈሩ:: ኦሮሞዎች ጥንታዊውን አገራቸውን ለቀው ከቤናዲር በቆላው ባሌ ከሰፈሩ በኋላ የፀጥታ ኑሮ ለማግኘት አልቻሉም:: ... ከሰሜን ወደ ደቡብ በተጓዙ ጊዜ በሰፈሩበት አገር በስተ ደቡብ ባንቱ የሚባሉ አርበኛ ነገድ ጎረቤት ሆኗቸው:: ስለዚህ ከሰሜን የሱማሌዎች፣ ከደቡብ ባንቱዎች የሚያደርባቸው ጦርነት ምንም ጊዜ ሰላም የሰጣቸው አይመስልም:: ስለዚህ ከዚህም ከአዲሱ አገራቸው እንደገና መሰደድ ግዴታ ሆነባቸው::... ጠብ አጫሪ ከሆኑት ከሶማሌዎች እና ከባንቱዎች ለመራቅ ይህ ሰላማዊ የነበረው ሕዝብ ዋቢንና የገናሌን ወንዝ ተከትሎ ወደ ደቡባዊ ኢትዮጵያ ወይናደጋ መሰደድ ጀመረ:: ... የኦሮሞ ሕዝብ በስጋ እና በወተት የሚመገብ [አርብቶ አደር] ስለነበረ ድርቅ ከሆነው ከቤናዲር አውራጃ ተጉዞ ወላቡ ወይናደጋ በገባ ጊዜ ይህች ምድር ማርና ወተት ታፈሳለች እንደተባለችው እንደ ምድረ ከነዓን የምትቆጠር ሁና አገኟት:: ኦሮሞዎች ወላቡ ብለው የሰየሙት አዲሱ አገራቸው ብዙ ዝናብ የሚዘንብበት፣ ለምለም ምድር በመሆኑ ነድተው ላመጧቸው መንጋዎች ወሰን የሌለው ጦሽ የሚበቅልበት ሆኖ ተገኘ:: በወረዳውም ውስጥ ለሰውና ለከብት ወሰን የሌለው ውኃ የሚገኝበት አገር ነው::... ከአገሪቱ ልምላሜ ሌላ ይህ አውራጃ ጠብ ጫሪ ከሆነው ከሱማሌ ጎሳ፣

ወደሚቀጥለው ገጽ ▶

ከባንቱዎች ጉርብትና የራቀ በመሆኑ የወላቡ ሰፈር ለኦሮሞ ሕዝብ ምድረ-ገነት ሆኖ በሰላም፣ በምቾት ትዳራቸውን የሚያስፋፉበት ፋታ ሰጣቸው:: ኦሮሞዎች በወላቡ የነበሩበትን ዘመን በማያቋርጥ ናፍቆት በታሪካዊ ግጥማቸው እና ዝሙራቸው መዝግበውታል:: ወደ ደጋው በመሰደድ ምክንያት ከጠረኞች ስለራቁ ወደ ወይና ደጋው ከገቡ ዘመን አንስቶ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ጦርነት እና ውጊያ አልነካቸውም" (ይልማ ደሬሳ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ገፅ፣ 212-216)

ከዚህ ታሪክ የምንረዳው ኦሮሞዎችም እንደማንኛውም ሕዝብ በሰዋዊው የመግፋት መገፋት፣ መወረር መውረር፣ ማሰደድ መሰደድ ማኅበራዊ ሕግ እየተገዙ የሰፈሩ ሕዝቦች እንጂ አሁን ያሉበትን የኦሮሚያ ክልል መሬት ይዘው የተወለዱ ልዩ ፍጡራን እንዳልሆኑ ነው:: በምክንያት ለሚያምን ይህ በራሱ ማንም ሰው የሚኖርበት መሬት ባለቤት የመሆን መብት እንዳለው አስረጅ ነው:: ምክንያቱም ያኔ ከቤናዲር መገፋት አብርሮ ያመጣው የኦሮሞ ሕዝብ የሰፈረበት መሬት ባለቤት ሆኖ እየኖረ ነው:: የኦሮሞ ሕዝብ በሰፈረበት መሬት ላይ ባለቤት ሆኖ፣ ከመሬቱ ስባት እያረሰ እያረባ ከኖረ ሌላው ህዝብ የሰፈረበት መሬት ባለቤት የማይሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? ኦሮሚያን እንገነጥላለን የሚሉ ፖቲከኞች ደግሞ ጭራሽ የኦሮሞ ሕዝብ በሰፈረበት ለም መሬት ማረስ ማርባቱ ስለማይበቃው መሬቱን ይዞ ይገንጠል ባዮች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች የመገንጠሉን ነገር ሲያመቻቹ ኦሮሞ ያልሆነ በተለይ ደግሞ ኦሮሚያን ወሮ ያዘ የሚሉት አማራው ከኦሮሚያ ምድር መውጣት እንዳለበት ሲያስገድዱ ሰው ወደ ገደል እስከመወርወር በደረሰ ጭካኔ ነበር:: የዛሬው አዲስ አበባ የኦሮሞ ንብረት ነች ዜማም የዚሁ ምክንያት አልቦ ተረክ ቅጅ ነው:: ለራሱ ጎሳ ሲሆን ሰፋሪው ወገን የሰፈረበትን መሬት ሙሉ ባለቤትነት አንሶት መሬቱን ጠቅልሎ ይዞ የመገንጠል መብት እንዳለው የሚከራከር አካል ሌላ ሰፋሪ ለፍቶ ደክሞ ባያቀናው ከተማ ባይትዋር እንዲሆን የሚፈልግ ከሆነ እንዴት መግባባት ይቻላል?

ወደ ታሪኩ ስንመለስ ኦሮሞዎች ቀደም ብለው ያደረጉት መስፋፋት መዳወላቡ እንዳደረሳቸው የሚነግሩን አቶ ይልማ ከቤናዲር በረሃ ወደ በመዳወላቦ ምድረ-ገነት መጥቶ የሰፈረው የኦሮሞ ሕዝብ አሁንም መስፋፋትን ግድ የሚል የሕይወት ሕግ ስለገጠመው መስፋፋቱን እንደቀጠለ እንዲህ ከትበዋል፡ -"ኦሮሞዎች ከላይ በተመለከትነው አኳኋን በወላቡ ዙሪያ ብዙ ትወልድ ካሳለፉ በኋላ ከልክ ያለፈ ተራብተው ምድር ጠበባቸው ከደረቁ ቤናዲር ይዘዋቸው ወደ ወይናደጋው ያመጧቸው የቦረና ዘር ላሞች ግጦሽ ከመላበት ከለምለሙ ወይና ደጋ በደረሱ ጊዜ አለመጠን ረቡላቸው:: ስዚህ ኦሮሞዎች ከወላቡ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት በግጦሽም መሬት እንደጠበባቸው አይጠረጠርም:: ከዚህ ሌላ በጥንት ዘመን ከቀድሞ መኖሪያቸው ከአፍሪካ ቀንድ ወግቶ ያስወጣቸው የሶማሌ ሕዝብ ዐሥራ አምስተኛው መቶ ሲጋመስ ከወይናደጋው ድረስ እየመጣ አዲሱን አገራቸውን መውረር ጀመረ:: በዚህ አኳኋን የኦሮሞ ሕዝብ ለመከላከል እና ለግጦሽ የሚፈልገውን መሬት አስፍቶ ለመያዝ ከሰላማዊ አኗኗር ወደ አርበኝነት ሐሳቡን መለሰ::... በዚህ ዘመን ኦሮሞዎች ከረዩ፣ ቱለማ፣ ሜጫ፣ ወሎ በሚባል ትልልቅ ነገድ ተከፍለው ይገኙ ነበር:: ስለዚህ ከረዩ የተባለው ነገድ ባሌን ፈጠጋርን ደዋሮን እንዲወር፣ ቱለማ ወደ ሰሜን ተጉዞ ዛሬ የሸዋ ኦሮሞ ምድር የተባለውን እንዲይዝ ሜጫ በስተምዕራብ እና በስተደቡብ የሚገኘውን የኢናሪያዎችን አገር እንዲወስድና ወሎ የተባለው ነገድ በሸዋ በስተምሥራቅ ተጉዞ ከወሎ አውራጃ እስከ ትግሬ ተዘረጋውን አንጎት የተባለውን አውራጃ እንዲይዝ የተቀየሰው ኦዳ ነቤ በነበሩ ጊዜ ነው:: ነገዶቹ ሁሉ ወረራውን በአንድ ጊዜ አለመጀመራቸውን ስንመለከት የጦሩ ስልት የታቀደበትን አኳኋን በማስተዋል ስንመረምር ከወረራው አስቀድሞ ጉዳዩ በስርአት የታሰበበት መሆኑን ልንገነዘብ እንችላለን::" (ገፅ 225-226):: ይህ ታሪክ ወደ ተነሳንበት የአዲስ አበባ ባለ ልዩ ጥቅም ባለመብትነት/ባለቤትነት ጥያቄ ሥረ ነገር ይመራናል::

ከላይ ያነበብነው ታሪክ በአፍሪካ ደረጃ ሳይቀር በታላቅነቱ የሚነሳው የኦሮሞ ሕዝብ ወደ ሰሜን መስፋፋት ብዙ ሰው እንደሚያስበው በግብታዊነት የተደረገ የግፋኝ ጉዞ ሳይሆን በወቅቱ በሰፊው ኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ የነበሩ ጎሳዎች ተከፋፍለው፣ የቀዳሚ ተከታዩ የጊዜ ምጥነት ተደርጎለት፣ ማን በየት አቅጣጫ እንደሚሄድ በጥንቃ ድልድል የተደረገበት መስፋፋት ነበር::በዚህ ድልድል መሠረት የዚህ ጽሑፍ ሥረ ነገር የሆነው በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ በመሃሉ የከተመችበት የሸዋ ኦሮሞ ክልላዊ ግዛት የተወረረው ቱለማ በተባለው የኦሮሞ ነገድ እንደሆነ ነው ከላይ ይልማ ደሬሳ የከተቡት ታሪካዊ ድርሳን የሚያስረዳው:: ሌላው የታሪክ ጸሐፊ ተክለጻዲቅ መኩሪያ "የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ልብነድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ" በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ (ገፅ 94-95) አቶ ይልማ በሰፊው ያቀረቡትን ታሪክ እንዲህ ያጠቃልላሉ፡- "ነገር ግን ኦሮሞዎች እንደ ሱማሌዎች የኢትዮጵያ ሰፊ ግዛት ነው እያልን በምንመካበት በደቡብ ኢትዮጵያ ከብዙ ዘመን ዠምሮ መኖራቸው የታወቀ ነው:: ነገር ግን በየምክንያቱ በመዠመሪያ ጊዜ በጥቂቱ፣ በአፄ ልብነድንግልና በግራኝ መካከል በተደረገው ጦርነት ጊዜ ግን በየነገዳቸው እየተከፈሉ ኦሮሞዎች ቁጥራቸውን አበርክተው ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ማኽል ሸዋ ወደ ዳሞት እና ወደ ጎጃም ወደ በጌ ምድር መግባታቸው የታወቀ ነው::" ስለዚህ የዛሬዋ አዲስ አበባ የተንጣለለችበት ግዛት ከኦሮሞዎች ጋር በመካከለኛው ዘመን (ከ1562 በኋላ) የተዋወቀ እንጅ የዘመናችን አክራሪ የኦሮሞ ብሔርተኞች አዳም ሲፈጠር በኤደን ገነት እንደተገኘ እንደዛው ሁሉ በአዲስ አበባ ምድር የሰው ፍጡር ሲታይ ቀድሞ የታየው ኦሮሞ ነው እንደሚሉት ዓይነት አይደለም! እንዲህ ታሪክ ተድበስብሶ ነው እንደግዲህ አዲስ አበባ ለኦሮሞ ቤት ለሌላው የሰው ቤት ነች እየተባለ አስተዛዛቢ ሙግት እየተነገረ ያለው::

አዲስ አበባ የኦሮሞ ንብረት በመሆኗ እንደ ማንኛውም በኦሮሚያ ክልል እንደሚገኝ ከተማ ትተዳደር የሚለው ክርክር በአስረጅነት የሚጠቅሰው በታሪክ በውል ያልተደገፈው የኦሮሞ ሕዝብ ቀደምት የአዲስ አበባ ነዋሪነት ታሪካዊ መብት አለው የሚለው ተረክ ከላይ በተጠቀሰው፣ ሸዋ ራሷ መቼ እና እንዴት በኦሮሞዎች እንደተያዘች በሚያስረዳው ታሪካዊ ማስረጃ ከእውነት የራቀ እንደሆነ አይተናል:: ሆኖም ለግራቀኙ ክርክር ንፅፅር እና ፍርድ እንዲመች አዲስ አበባ የኦሮሞ ቀደምት ቤት ነች የሚሉ ወገኖችን ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል:: አስረጅ ሲያቀርቡ ያጋጠመኝ የዚህ ክርክር ባለቤቶች "በ18ኛው ክፍለ ዘመን የአዲስ አበባ ነዋሪ ሁሉ መቶ ፐርሰንት ኦሮሞ ነበር" የሚል ከላይ የተጠቀሰው የፀጋዬ አራርሳ ገራሚ ክርክር ሲሆን ሌላው ዶ/ር ነጋሶ ሐምሌ 8 ቀን 2009 ዓ.ም. ከወጣው የከአዲስ አድማስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ታሪክ ጠቅሰው ያቀረቡት ክርክር ነው:: ዶ/ር ነጋሶ ጋዜጠኛው "የአዲስ አበባ እና ኦሮሞዎች በታሪክ ያላቸው ግንኙነት መቼ ነው የሚጀምረው?" ለሚለው ጥሩ ጥያቄ የመለሱት መልስ በአፄ ምኒልክ አባት እና አያት ዙሪያ የሚያጠነጥን፣ የተለመደው ታሪክን ከወገቡ የሚጀምር የኦሮሞ እና የትግራይ ብሔርተኞች (ኦነግ እና ሕወሓት) ውሸትን ደጋግሞ እውነት የማስመሰል፣ ከምክንያታዊነቱ ይልቅ ማደናቆሩ የበዛ የብልጣብልጥነት መልስ ነው:: ብዙ የሚዞረው የዶ/ር ነጋሶ መልስ ነጥብ ያለው እንዲህ በሚለው ማሳረጊያው ላይ ነው "....አፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥታቸውን አሁን ወዳለበት ያመጡት ለፍል ውኃ ቅርብ ለመሆን ነው፤ እንጅ ቦታው ላይ ኦሮሞዎች በ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምረው ይኖሩበት ነበር:: ... ቦታውን ምኒልክ ሲይዙት ብዙ የጎሳ መሪዎች ተገድለዋል:: ጎሳ መሪዎቹ ተገድለው መሬታቸው ለቤተ መንግሥት ሰዎች፣ ለውጭ አገር ዲፕሎማቶች ነው የተከፋፈለው:: በሕይወት የተረፉት ሸሽተዋል:: ሆን ተብሎ በማፈናቀልም ወደ አርሲ፣ ባሌ፣ አካባቢ እንዲሰፍሩ የተደረጉ አሉ:: ባሕሉና ቋንቋውም በክርስትና መስፋፋት ጠፍቷል::" የዶ/ር ነጋሶ መልስ ከላይ ለተነሳው የቀደምትነት ጥያቄ ልከኛ ማስረጃ የሚሆነው ዓለም የተፈጠረው፣ታሪክ የተቆጠረው ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ቢሆን ነበር:: እውነታው ግን ያ አይደለም! አፄ ምኒልክ ፍውኃውን ከጓሯቸው ለማድረግ፣ ለባሕር ማዶ ወዳጅ አገራት ኢምባሲ ለመሥራት የአገሬውን ሰው አፈናቅለው ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን እነዚህ ተፈናቀሉ የሚባሉ ሰዎች ኦሮሞዎች ብቻ ስለመሆናቸው ምን ማስረጃ ይቀርባል? የተፈናቀሉት ሰዎች ኦሮሞዎች ብቻ ነበሩ የሚለውን ብንቀበልስ ለመላው አዲስ አበባ

የኦሮሞ ቀደምት ርስትነት ማስረገጫ በምኒልክ ዘመን በፍል ውኃ አካባቢ ኦሮሞዎች የነበሩ መሆናቸው እና በምኒልክ መፈናቀላቸውን ብቻ ማስረጃ አድርጎ ማረብ ማንን ያጠግባል? ዶ/ር ነጋሶ ሲቀጥሉ "... ሰሜን ሸዋ አሁን ላሎ ተብሎ ሚጠራው አካባቢ ለአዲስ አበባ እጅጉን ቅርብ ነው፤ ስለዚህ አዲስ አበባ አካባቢ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኦሮሞዎች እንደ ነበሩ የሚታወቅ ነው ማለት ነው::" ዶ/ር ነጋሶ በሰሜን ሸዋ አካባቢ ላሎ የሚባል ቦታ ላይ ኦሮሞዎች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ መኖራቸው በምን ስሌት አዲስ አበባን የኦሮሞ ንብረት ያደርጋታል ብለው እንዳሰቡ ለኔ ግራ ነው:: ኦሮሞዎች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምረው የአሁኑን የሸዋ ኦሮሞን ግዛት እንደያዙ ታሪክም ከዶ/ር ነጋሶ ሐሳብ ጋር ይስማማል:: እዚህ ላይመነሳት ያለበት ጥያቄ ግን 16ኛው ክፍለ ዘመን የዘመን ጅማሬ አይደለምና በዚህ ሰዓት የወረረ አካል የአገር ብቸኛ ባለቤት ነው ከተባለ ከዚያ በፊት በቦታው የነበሩ የሰው ዘሮች ባለቤት የማይሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለው ነው:: ለዚህ ክርክር አክራሪ የኦሮሞ ብሔርተኝነት ፖለቲከኞች ሲያነሱ የሚያጋጥመኝ መልስ ኦሮሞ በሚስፋፋበት ዘመን የሚይዘው መሬት ሰው ያልሰፈረበት ምድረበዳ እንደሆነ ነው:: ይሄም የሚያስኬድ አይደለም:: የታሪክ መዛግብትን እንፈትሽ::

የኦሮሞን ታሪክ የጻፉ ሌላው ጸሐፊ አለቃ አፅሜ "የኦሮሞ ታሪክ ክፍል አንድ" በሚለው መጽሐፋቸው (ገፅ 171) ላይ ይህን ጽፈዋል፡- "...ኦሮሞ አማራን አባሮ ፈጅቶ፣ኢትዮጵያን ከትግሬ በቀር ወረሳት::" ይህ ማስረጃ እኛ ከምናውቀው አባራሪ ተባራሪ ምድብ ያፈነገጠ፤ አባራሪን (ኦሮሞ) ተባራሪን (አማራ) አድርጎ የዘመናችን ፖለቲካ በደመነፍስ ያስቀመጠውን የበዳይ ተበዳይ ድልድልን ያቀያየረ ነው:: ታሪክን ከወገቡ ጎምዶ የሚያቀርበው ወቅታዊ ፖለቲካችን የአገራችን ብቸኛ ወራሪ አማራ የዘወትር ተባራሪ ደግሞ ኦሮሞን አድርጎ ያቀርባል:: ከጎማዳው ታሪክ እልፍ ሲሉ ያለው እውነታ ግን ሌላ ነው:: የኑሮ ስንክሳር፣ የኀይል ሚዛን እንዲያባርር ያስገደደው ሁሉ ያባርራል፣ ያፈናቅላል::ሁሉም መውረር መወረር፤ መስማማት መጣላት የኢኮኖሚ ጥያቄ፣ የኀይል ሚዛን ጉዳይ ነው! ባለበት ተገትሮ የሚቀር ነገር የለምና አባራሪም የተባራሪነት እጣ ይገጥመዋል:: በዚህ ውስጥ ጎሳዊ ቅድስናው ተባራሪ፣ ጎጣዊ እርኩስነቱ አባራሪ የሚያደርገው የሰው ልጅ የለም:: ስለዚህ ሁኔታ አለቃ ተክለኢየሱስ ዋቅጅራ በፃፉት እና ዶ/ር ሥርግው ገላው አርትኦት በሠሩበት "የኢትዮጵያ ታሪክ" የሚል ርዕስ ባለው መጽሐፍ (ገፅ 156) ላይ ይህን ጽፈዋል፡- "... ያን ጊዜ አማራ እና ኦሮሞ ሞጋሳ ተባብለው ቃል ኪዳን ተገባቡ:: አማራ እና ኦሮሞ ከዚያ ወዲህ ተደባለቀ:: ያን ጊዜም ለሚመጣው ለኋለኛው ዘመን ንግር ተነገረ:: ንግሩም እንዲህነው:: ኦሮሞ አማራን እያሳደደ ግቤን ወንዝ ባሻገረው በአማራ በዘጠነኛው በኦሮሞ በዐሥረኛው ትውልድ ሲሆን ግፍ ብድር አይቀርምና ፈንታውን አማራ ኦሮሞን ያሳድደዋል ተብሎ ተነገረ:: ይህም ንግር ጊዜው በደረሰበት ላይ በኋላ ይጻፋል":: ለማከል ያህል ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ "የአባ ባሕርይ ድርሰቶች" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ (ገፅ 123) እንዲህ ይላሉ፡- "ኦሮሞዎች ወደ መሃል ኢትዮጵያ ገብተው የያዙት አገር ግራኝ ባዶ ያደረገውን ነው የሚሉትን የዛሬ ኦሮሞ ታሪክ ጸሐፊዎችን የአባ ባሕርይ ጥናት አይደግፈውም:: ኦሮሞዎች አገር ሲወሩ ነባሩን ሕዝብ እያጠፉና ኦሮሞ እያደረጉ ነበር..." አባ ባሕርይ ለዚህ ያቀረቡትን ነባራዊ አስረጅ እዚህ ለመጻፍ ስለማልችል አንባቢዎቼ መለስ ብለው እንዲያነቡ እመክራለሁ:: ከላይ የተጠቃቀሱት ታሪካዊ ማስረጃዎች በኦሮሞዎች መስፋፋት ወቅት በአገራችን የነበረውን አጠቃላዩን ነባራዊ ሁኔታ የሚያስረዱ ናቸው:: የዚህ ጽሑፍ ዋና ጉዳይ የሆነው የአዲስ አበባ እና የኦሮሞ ሕዝብ ታሪካዊ መስተጋብርን ከዚህ ከትልቁ ምስል የማይወጣ በመሆኑ አንባቢ ከትልቁ ምስል አንጻር ደግሞ እንዲያየው በማሰብ ያመጣሁት ነው::

የአጠቃላይ ነገሩን ማስረጃ እዚህ ላይ ልግታና የጽሑፉ ልብ የሆነው አዲስ አበባ የምትገኝበት የአሁኑ የሸዋ ኦሮሞ ግዛት በ16 ክፍለ ዘመን ኦሮሞዎች ሲወረር ባዶ መሬት ነበር/አልነበረም የሚለውን ወደመመርመሩ እንለፍ:: የአቶ ይልማ ደሬሳን መጽሐፍ (ገፅ 245) እንመልከት፡- "በ1562 ዓ.ም. የሐንሩፋ ገዳ 8 ዓመት ተፈፅሞ ከአርባ ዓመት በፊት በሙዳና ገዳ ጊዜ ቡታ ያረደው ትውልድ ልጆች ባለገዳ ለመሆን ደረሱ:: ቡታ ባረዱም ጊዜ ገዳውን ሮበሌ ብለው ሰየሙት:: በዚህ በሮበሌ ገዳ ጊዜ ትልቅ ዘመቻ ያደረገው የቱለማ ጎሳ ነው፤ እላይ እንደተመለከትነው ሁሉ ከረዩዎች ወደ ምሥራቅ፣ መጫዎች ወደ ምዕራብ፣ ወሎዎች ወደ ምሥራቅ ሰሜን መኳዛቸውን ስናትት ቱለማዎችን ኦዳ ነቤ ላይ ተውናቸው:: በ1562 ዓ.ም. ቱለማዎች ከኦዳ ነቤ ዙሪያ ተነስተው ሸዋን ለመውረር በተጓዡ ጊዜ በአዝማች ዘረ ዮሃንስ የተመራ የንጉሠ ነገሥት ጦር መንገድ ላይ ጠብቆ ገጠማቸው:: ከጦርነቱም ላይ አዝማች ዘረ ዮሐንስ ሞቱ፤ ሠራዊቱም ተሸነፈ:: በዚያን ጊዜ ሮበሌ ባለገዳዎች የሸዋና የጎጃም መንገድ እንደተከፈተላቸው ቆጥረው በግስጋሴ ወደ ፊት ተራምደው ዛሬ የሸዋ ኦሮሞ ምድር ከተባለው አገር ላይ ሰፈሩ::" ከዚህ የምንረዳው ቀላሉ ነገር ኦሮሞዎች የአሁኑን የሸዋ ኦሮሞ ግዛት ሲወሩ በቦታው ሌሎች ሰፋሪ ሕዝቦች እንደነበሩ ነው:: ሕዝቦቹ ገዥ ንጉሠ ነገሥት የነበራቸው ነገር ግን የኦሮሞዎቹ ጉልበት ስለጠናበት ወረራውን መቋቋ የተሳነው በመሆኑ ሳይወድ በግድ መወረሩን የተቀበለ እንደሆነም እንረዳለን:: ይህ የመውረር መወረር ክስተት ያለ እና የነበረ በመሆኑ በታሪክ ሁነትነቱ ከመቀበል ሌላ ትርጉም ያለው ነገር የለም:: ኦሮሞዎቹ በሸዋ ምድር ከመስፈራቸው በፊት የነበሩ ሕዝቦችን ማንነት የማፈላለግ ሥራ ፊት ጥያቄ አንስቼ፣ የአዲስ አበባ ባለቤቶች ኦሮሞዎች ሳይሆኑ ከነሱ በፊት በንጉሥ እንቶኔ ሲመሩ የነበሩት የእንትን ጎሳ ሰዎች ናቸው የሚል አዋጭ ያልሆነ ክርክር ውስጥ መግባት አልፈልግምና የታሪክ መዛግብት ምርመራየን እዚህ ላይ ልግታና እስካሁን ያየናቸው የታሪክ መዛግብት የሚያቀብሉን መረጃ ከወቅታዊው የአዲስ አበባ ባለቤትነት ጥያቄ ጋር ያለውን መስተጋብር ላንሳ::

ይኼን ሁሉ ያነጋገረን ጉዳይ አዲስ አበባ በታሪክ ቀደምት ነዋሪዎቿ ናቸው የተባሉት የኦሮሞዎች ንብረት መሆን እንዳለባት የሚነሳው ክርክር ነው:: ይህ በታሪክ መነፅር ሲፈተሽ ኦሮሞዎች እና አዲስ አበባ የምትገኝበት ሸዋ የተዋወቁት በ1562፣ ኦሮሞዎች ቀድሟቸው በአካባቢው ተገኝቶ፣ አገዛዝ መሥርቶ የነበረን የንጉሠ ነገሥት ጦር አሸንፈው አካባቢውን በመውረራቸው ሳቢያ እንደሆነ አረጋግጠናል:: ስለዚህ ኦሮሞ የአዲስ አበባ ቀደምት ነዋሪ ነው በሚለው ከእውነት የራቀ ክርክር ላይ ተቁሞ የሚነሳው ኦሮሞ ሕዝብ የበለጠ የአዲስ አበባ ባለቤትነት መብት ይከበርለት የሚለው ጥያቄ የማያስኬድ ነው ማለት ነው:: በነገራችን ላይ በግሌ የቀደምት ነዋሪነት ክርክር ራሱ ሳይንሳዊ አይመስለኝም:: ምክንያቱም ቀደምት የምንለው ታሪክ ራሱ ሌላ ቀደምት አለውና ዘመንን ከሚመች ቦታ ጀምሮ ቆጥሮ እኔ ቀደምት ነኝ የሚለው ክርክር ትርጉም የማይሰጥ ነው:: የሆነው ሆኖ የቀደምትነቱ ጨዋታ ቀደምትነትን ከሚመቻቸው ቦታ ለሚቆጥሩ አካላት ሌላ የቀደምትነት አቅርቦት ስላለው እዳው ገብስ ነው::

ከባዱ ነገር የቀደምትነት የታሪክ ልቃቂት ሲጎለጎል፣ የታሪክ ሐቅ ከፈለጉት ቦታ አንስቶ ወዳልፈለጉት ቦታ ሲያስቀምጥም የቀደምትነቱን ዜማ እንደያዙ መቆየቱ ነው:: አክራሪ የኦሮሞ ብሔርተኛ ፖለቲከኞች የቀደምትነት ውሽልሽል ክርክራቸው ላይ ተመሥርተው የአዲስ አበባ ባለቤትነትን ጥያቄ ሲያነሱ የሚወክሉት የራሳቸውን ስስታምነት እና የሥነ ልቦና ቀውስ እንጅ በጉዲፈቻ ላሳደገው ልጅ ሀብት ንብረቱን ከወለደው ልጅ እኩል የሚያካፍለውን የኦሮሞ ሕዝብ ሥነ ልቦና አይመስለኝም:: እነዚህ ፖለቲከኞች ቀደምት ነዋሪነትን ጠቅሰው የአዲስ አበባ ባለቤትነት ይገባናል ካሉ ከአዲስ አበባ ቀድመው መጠየቅ ያለባቸው ታሪክ ሲገለጥ የኦሮሞ ሕዝብ ከአዲስ አበባም ከመዳወላቡም ቀድሞ ይኖርበት የነበረውን በረሃማውን የቤናዲርን ግዛት ነው:: ይህን ግን አያደርጉም:: ምክንያቱም ያልሆነውን የቀደምትነት ጥያቄ ያስነሳቸው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የለፋበት የአዲስ አበባ ወቅታዊ መንቆጥቆጥ እንጅ እነሱ የሚሉት፣ ታሪክ ግን የማያውቀው የቀደምትነትን ነገር አይደለም::

መስከረም አበራን በኢሜይል አድራሻዋ
meskiduye99@gmail.com ሊያገኟት ይችላሉ::

# “[ቋንቋ] ሀገራዊ ስሜትን ለመፍጠር ያለው ችሎታ ሀገርን ለመበተንም ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል”

ዶ/ር ግርማ ጌታሁን

*የሥነ ጽሑፍ መምህሩ ዶ/ር ያለው አወቀ “ጠንቃቃና ታታሪ ምሁር” ሲሉ የሚገልጿቸው የዛሬው ዕንግዳችን፣ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቁት “የጉጃም ትውልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ ታትሞ በቀረበው መጽሐፋቸው ነው:: በቅርቡ ደግሞ “የ-ግይጊ ማከያ መዝገበ-ቃላት” በሚል ርዕስ የተዋጣለት ሥራቸውን ሰጥተውናል:: ቀደም ሲል በብሪቲሽ አካዳሚ አማካይነት የታተመውን መጽሐፋቸውን ጨምሮ ሌሎች የታተሙ እና በሕትመት ዝግጅት ላይ የሚገኙ በርከት ያሉ ሥራዎችም አሏቸው:: ባልደረባችን መብራቱ በላቸው በሥራዎቻቸውና በሕይወታቸው ዙሪያ አወያይቷቸዋል:: ውይይቱን እነሆ:-*

**ውይይት፡- ስለልጅነትና የትምህርት ጊዜህ ብታጫውተኝ፤ ከቋንቋና ከቃላት ጋር የነበረህን ቀረቤታ ጨምረህ::**

**ዶ/ር ግርማ**፡- የተወለድኩት ዐዲስ አበባ ነው፤ ዕሣማ ግቢ/ይልማ በድሉ ዘይት ፋብሪካ እሚባል መንደር ውስጥ፣ በመሳለሚያ እና በራስ ኀይሉ ሜዳ (አኹን አበበ ቢቂላ ስታዲየም) መካከል። የተማርኩት ደግሞ (እስከ 10ኛ ክፍል) መድኀኔዓለም ትምህርት ቤት ነው። በልጅነቴ የዐማርኛ መጻሕፍት አነብብ ነበር። ግን ለቋንቋ እና ቃላት ከሌሎች ልጆች የተለየ ቀረቤታ አልነበረኝም። ግጥም አንብቦ በቃል መያዝ (በተለይ የከበደ ሚካኤልን) እወድድ ነበር፤ የዐማርኛ ቅኔ መፍታትም። ሰዋስው ግን የሚከብደኝ እና የሚያስለቸኝ ትምህርት እንደነበር አልረሳም። ታዲያ ይህ ኹሉ ከሌሎች ልጆች የተለየ የቋንቋ ቀረቤታ እንዳልነበረኝ አመልካች ነው።



በርግጥ ከዐብሮ-አደግ እኩዮቼ ትንሽ ለየት ያለ ጥረት አደርግ ነበር፤ እንግሊዝኛ ለማወቅ የታላቆቼን መማሪያ መጻሕፍት እጠቀም ነበርና። የማላውቃቸውን ቃላት ፍቺዎች ለመረዳት ብዙ ጊዜ አጠፋ እንደነበር ይታወሰኛል። ብዙ ጊዜ ለማላውቀው ቃል የተሰጠው መፍቻ ሌሎች የማላውቃቸው ቃላት ይኖሩታል። የመጀመሪያውን ቃል ፍቺ ለመረዳት የኋላኞዎቹን አስቀድሞ ማወቅ ግድ ነበር። ግን ለዚህ የሚበጅ ትዕግሥት ነበረኝ። ያኔ የቃላት ኀይል እና ሚና፣ ውበት እና አማላይነት ሀዲም አእምሮዬ (subconscious mind) ውስጥ ሥር ሰድደው ይኾን?

*ዜጎቻቸውን በምጣኔ-ሀብት ብቻ ሳይኾን በባህል፣ በስሜት እና በሥነ-ልቦና አስተሳስረው ወደ ተሻለ የሥልጣኔ እና የብልጽግና ደረጃ ለማድረስ የሚፈልጉ ሀገራት የብሔራዊ ቋንቋን ወሳኝ ሚና ተረድተው እርሱን ለማዳበር እና ከፍተኛ ደረጃ ያለው ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ*

በርግጠኛነት መናገር የምችለው ግን ለዐማርኛ ቋንቋ እና ሥነጽሑፍ ልዩ ፍላጎት ያደረብኝ ከየካቲቱ አብዮት ጋር ዴሞክራሲያ፣ አብዮት እና ጎሕ መጽሔት ብቅ ሲሉ ነበር። ያኔ በስውር የሚሰራጩ የጥናት የተቃውሞ ጽሑፎች በረከቱ፤ እንደ “ሰቈቃወ ገባር” ያሉ በቴፕ የተቀረጹ የተቃውሞ ግጥሞችም ነበሩ። የፖ`ለቲካ፣ የምጣኔ-ሀብት፣ የፍልስፍና፣ ወዘተ. ጽንሰ-ሐሳቦችን የሚፈቱ ቃላት ተፈጠሩ። ለነዚህ ቃላት አፈጣጠር ደግሞ የግእዝ ርባና ፍንትው ብሎ ታየ። በለጋ አእምሮዬ ውስጥ በደምሳሳው ይሰቡኝ የነበሩ ከንካኝ ነገሮች - የድኾች እና ድኩማን ጕስቍልና፣ የፍትሕ ዕጦት፣ ወዘተ. - ድንገት እኒህን ዐዳዲስ ቃላት በሚጠቀሙ የተቃውሞ ጽሑፎች ቅጥ እና ጕባሬ (form and coherence) አግኝተው የሥርዐተ-ማኅበር ለውጥ አስፈላጊነት ግንዛቤዬን አዳበሩልኝ። ልቤ ወደ ቋንቋ እና ሥነ-ጽሑፍ ያዘነበለው ያኔ ነው።

**ውይይት፡- የ-ግይጌ ማከያ መዝገበ-ቃላት ብለህ የሰየምከውን መዝገበ-ቃላት ለማዘጋጀት ምን አነሳሳህ? ፍላጎቱ እንዴት ሊያድርብህ ቻለ?**

**ዶ/ር ግርማ፡-** ይህ በማከያው መግቢያ ላይ ከሞላ-ጐደል ተመልሷል። ለማከያው ጥንስስ በመኾን ያገለገለ አንድ የቃላት ክምችት ነበረኝ። “የጐጃም ታሪከ-ነገሥት” በመባል የሚታወቀውን የአለቃ ተክለ-ኢየሱስ ዋቅጅራ ጽሑፍ ወደ እንግሊዝኛ በምተረጕምበት ጊዜ ከነፍቺዎቻቸው የመዘገብኳቸው ነበሩ። ብዙዎቹ በዕጥር-ምጥን (concise) መዛግብተ-ቃላት ውስጥ አይገኙም። ከሚገኙትም ጥቂት የማይባሉት በዘወትር ፍቺዎቻቸው ብቻ የተሰጡ ነበሩ። ስብስቡ እያደገ ሲመጣ በመዝገበ-ቃላት ምድን (discipline) ተዘጋጅቶ በማከያ መዝገበ-ቃላት ቢታተም ብዙ ባለሙያዎችን፣ ልሂቅ ተማሪዎችንን እና መምህራንን ሊጠቅም እንደሚችል ዐሰብኩ። አጋጣሚው ቃላቱን በነአለቃ ኪዳነ-ወልድ የሆሄ ጥንቀቃ እድብ ለማቅረብም መልካም እንደሚኾን ታየኝ። ያነሣሡኝ ሐሳቦች እኒህ ነበሩ።

**ውይይት፡- ከዚህ ቀደም በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ የተለያዩ መዝገበ ቃላት እንዳሉ ይታወቃል:: ለመሆኑ አንተ ያዘጋጀህው መዝገበ-ቃላት ምን የተለየ ነገር የዟል ማለት ይቻላል? ምን አዲስ ነገር ጨምሯል? አስፈላጊነቱንስ እንዴት ትገልጸዋለህ?**

**ዶ/ር ግርማ፡-** የኔ ማከያ እንጂ ወጥ እና ሙሉ

መዝገበ-ቃላት አይደለም:: በተጨማሪ ማከያው ልሳነ-ክልኤ እንጂ ልሳነ-ዋሕድ አይደለም፤ የዐማርኛ ቃላትን በእንግሊዝኛ ስለሚፈታ:: ስለዚህ ቃላቱንም መፍቻውንም በዐማርኛ ከሚሰጥ ልሳነ-ዋሕድ መዝገበ-ቃላት በጣም ይለያል::

ጥያቄውን ትንሽ ቀየር አድርጎ ማከያውን ከብጤዎቹ ስለሚለየው ነገር ጥቂት ማለት ይበጅ ይኾናል:: ዐማርኛ ቃላትን በእንግሊዝኛ ከሚፈቱ መዛግብተ-ቃላት ጋር ሲነጻጻር ማከያው ለየት የሚያደርጉ ገጽታዎች አሉት:: አንደኛው ተካታቾቹን ቃላት በቅድሚያ በሥርውቃላዊ ሆሄ ጥንቀቃ ማቅረቡ ነው፤ (በጽሑፍ እና በንግግር የሚታዩበትን/የሚደመጡበትን ቅርጽ ሳይዘነጋ):: እንዲያ በማድረጉ ድምፀ-ሞክሼ ሆሄያት ያላቸውን ልዩ ርባና - የፍቺ እና የታሪክ ልዩነቶችን የማጕላት መጠነኛ ርባና - አለው:: ሠባ እና ሰባ፣ አባይ እና ዐባይ፣ ወዘተ. ውስጥ ያሉ ድምፀ-ሞክሼ ሆሄያት በዐማርኛ ድምፆቻቸው ስለተመሳሰሉ በግድየለሽነት እየተተካኩ መጻፋቸው ካለማወቅ የተነሣ አጕል ልማድ ነው:: በዚህ ረገድ ማከያው ግንዛቤ ለመፍጠር በትንሹም ቢኾን ሊረዳ ይችላል::

ማከያው በዘመናዊ ዐማርኛ ውስጥ የተረሱ ቃላትን በማካተት ከአንባቢ ጋር ያስተዋውቃል:: እንደ ቅርምዝ፣ በለዲ፣ አባደ ያሉት ቃላት በውሰት የምንጠቀምባቸውን crimson, rose/pink, alienate በቀጡ የሚገልጹ ናቸው:: "ሳይቸግር ጤፍ ብድር" እንዳይተረትብን የቃላት ጥሪታችንን እንድናዳብር የሚያበረታታ ይመስለኛል::

ማከያውን ከብጤዎች ለየት ከሚያደርጉ ገጽታዎች አንዱ ከእላዬ ቃላት ምድን ወጣ ብሎ መድበሉን አማላይ እና መዜንው የሚያደርጉ የቦታ ስያሜዎችን (ላፍቶ፣ መካኒሳ፣ ቡሬ)፣ በዘፈን እና የልጆች ግጥሞች ውስጥ የሚደመጡ እንግዳ ቃላትን (ለምሳሌ ቍልቢጥ፣ ጭንብር ቦቃ)፣ ወዘተ. ፍቺዎች የሚያመላክቱ መጠነኛ ቃላት ማካተቱ ነው::

በቃላት አፈታት ረገድም የፍቺ መቀራረብ እና መራራቅን ሊያሳይ የሚረዳ አደረጃጀት አለው:: ፍቺዎችን በሚገልጿቸው ስሜቶች እያቧደነ በቍጥር፣ በሆሄያት እና በንኡስ ቍጥሮች ይደረድራል:: በዚህ ዐይነት የሚፈታቸውን ቃላትም እስከተቻለ የተሟላ ፍቺ እንዲኖራቸው ይሞክራል፤ ከታተሙ እና ካልታተሙ የጽሑፍ ምንጮች አገባባዊ ምሳሌ እየሰጠ::

**ውይይት፡- በኢሕአፓ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ እንደነበረህ ለመረዳት ችያለሁ:: በዚያ ወቅት ይወጡ የነበሩ መጣጥፎች ላይ ቃላት ታርም እንደነበርም ተባራሪ ወሬ ሰምቻለሁ:: እስኪ ከሥነ ጽሑፍና ከቋንቋ አኳያ የነበረህን አስተዋጽዖ ጨምረህ፣ በወቅቱ ስለነበረህ ተሳትፎ ግለጽልኝ::**

**ዶ/ር ግርማ፡-** በ-ኢሕአፓ መራሹ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከብጤዎቼ የላቀ ወይም የጐላ ተሳትፎ አልነበረኝም:: በዚያን ዘመን የኹለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እንኳ ያላጠናቀቅኹ ለጋ ወጣት ነበርኩ:: እንኳን በነዮሐንስ ብርሃኔ እና ጸጋዬ ደብተራው የሚቀርቡ ጽሑፎችን ላርም፣ እነርሱ የሚጽፉትን እንብቤ በቅጡ ለማኰት የሚያስችል እውቀት አልነበረኝም:: የሰማኸው "ዋርካ በሌለበት እምቦጭን አድባር የሚያደርጉ" ሰዎች የሚሉትን ነው:: መሠረት የለውም::

በርግጥ እንዳቅሚቲ አጽፍ ነበር፤ በወጣት ማኅበር ሥነጽሑፍ ክበብ በምሳተፍ ጊዜ:: ለወጣት ሊጉም ቀስቃሽ ጽሑፎች፣ ግጥሞች እና መዝሙሮች አዘጋጅ ነበር:: ያኔ ያወቁትን ማሳወቅ (ዕውቀቱ ቍንጽል እና ግልብ ቢኾንም) የወጣቱ "አብዮታዊ ግዴታ" ነበር:: አንዳንድ ግጥሞቼን በቃል አጥንተው የያዙ ወጣቶችም አጋጥመውኛል:: ግን የኔ ግጥሞች እና ዐጫጭር ልቦለድ-ቀመስ ጽሑፎች ለጎሕ መጽሔት ኅትመት የሚበቁ አልነበሩም::


**ውይይት፡- ቋንቋ ላንተ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ግርማ፡-** በዚህ ጥያቄ ላይ ዐጭር እና የተሟላ መልስ መስጠት አልችልም:: እንዲያ ብዩ ከመተው ግን የዋህ እና ደምላላ (general) መልስ ለመስጠት እሞክራለኹ:: ቋንቋ ለኔ ታላቅ የመግባቢያ መሣሪያ ነው:: በርሱ የሚግባቡ ሰዎችን በሐሳብ፣ በባህል፣ በምናብ፣ በመንፈስ ያስተሳስራል:: ዘወትር በሚጠቀሙበት (እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ በሚናገሩት) ሰዎች መኻል ሀገራዊ ስሜት ይፈጥራል:: እንዲያ በመኾኑም ኃያል ነው:: በደንብ ዐውቆ ለሚጠቀምበት ሰው ቋንቋ ትልቅ ሥልጣን ያጐናጽፋል፤ ሐሳብን/ስሜትን እንደልብ የመግለጽ ሥልጣን፤ ውኸንብርን በማጥራት፣ የግጭት መንሥኤ እና መፍትሔን በማመላከት ሌሎችን የማሳመን ወይም የማግባባት ሥልጣን:: ሐሳብን/ስሜትን/ምናብን በቅጡ መግለጽ የሚችል ሰው ደግሞ አለመቻል ከሚያስከትለው ባሕሪያዊ እና ሥነ-አእምሯዊ ችግሮች ራሱን ይጠብቃል:: የቋንቋ ክሂል ሐሳብን ከማደራጀት ችሎታ ጋር ተመጋጋቢ ይመስለኛል::

ቋንቋ፣ ለኃያልነት ምንጭ በኾነ ባሕሪው የተነሣ፣ ምቹ የፖለቲካ መሣሪያም ይኾናል:: ሀገራዊ ስሜትን ለመፍጠር ያለው ችሎታ ሀገርን ለመበተንም ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል:: ለዚህ ይመስለኛል ለብሔረተኞች፣ በተለይም ለዘውግ ብሔረተኞች ምቹ እና ተመራጭ መሣሪያ የሚኾነው:: እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ልሳነ-ብዙ እና ዘውገይር (multiethnic) ሀገራት፣ በተለይ የዜጎች ሰብአዊ እና ዴምክራሲያዊ መብቶች በማይከበሩባቸው ሀገራት፣ ቋንቋ ለዘውጌ ብሔረተኛ እንቅስቃሴ ዐይነተኛ መሣሪያ መኾኑን ዘወትር እናያለን::

**ውይይት፡- በአማርኛ ቋንቋ ከሚነሱ አከራካሪ ነጥቦች አንዱ ድምፀ-ሞክሼ ፊደላትና ድምፀ-**




**ሞክሼ ቃላት በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው:: በዚህ ላይ ያንተ አቋም ምንድን ነው? ለምን? ብታብራራልኝ::**

**ዶ/ር ግርማ**፡- የዐማርኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት በዐዋጅ ወይም ልማድ ባዳበረው እድብ የጸና መደበኛ አጻጻፍ የለውም፤ ኹሉም ሰው እንዳሻው የሚጽፍበትን ልማድ መደበኛ ካላልነው በቀር:: ለዚህ ኢመደበኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት አንዱ ምክንያት በቋንቋው ፊደል ውስጥ ያሉ ድምፀ-ሞክሼ ሆሄያት ናቸው:: ጽሑፉን በንግግር እንደሚደመጠው የመጻፍ ልማድ ደግሞ ሌላ ምክንያት ነው:: ተጨማሪ ምክንያቶችም ይኖራሉ:: እነዚህ ኹለቱ ግን ዐበይት ይመስሉኛል::

ዐማርኛ ድምፀ-ሞክሼ ሆሄያት ያሉት ከሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር የተዛመደ ስለኾነ፣ መሠረታዊ የቃላት ሀብቱንም ከነርሱ ስለሚዋረስ፣ ለጽሕፈቱ ደግሞ የግእዝ ፊደልን በማከያ ሆሄያት አምልቶ ስለሚጠቀም ነው:: አፋዊ ቋንቋው በኺደት አንዳንድ ድምፆችን ስላጣ ጥንት የተለያየ ድምፅ ወካይ የነበሩ አንዳንድ ሆሄያቱ ዛሬ አንድ ድምፅ የሚወክሉ ድምፀ-ሞክሼ ኾነዋል:: የሆሄያቱ ጥንታዊ ሙያ ግን (ማለትም ፍቺ-ዐዛይ መኾናቸው) አልተለወጠም:: ሀ እና ሐ የዐማርኛ ድምፃቸው ይመሳሰል እንጂ ፍቺ-ዐዛይ ሙያቸው ይለያያል፤ ቢያንስ ሴማዊ ለኾኑ ቃላት:: ስለሚለያይም ‹ምሁር› እና ‹ምሑር› ብለን ስንጽፍ ቃላቱ በ"ሁ" እና "ሑ" የተነሣ የፍቺ ልይዩነትን ሲያስከትሉ እናያለን:: ምሁር በዕውቀት ብልጹግ መኾንን ሲገልጽ፣ ምሑር ደግሞ ይቅርታ/ስርየት ማግኘትን ይገልጻል:: የ<ሐ> ልዩ ድምፅ ባልጠፋበት ትግርኛ ለምሳሌ ይህ ልዩነት ግልጽ ነው:: በግእዝም እንዲሁ:: ዐማርኛን ብቻ ለሚያውቅ ወይም በተናጠል ለሚያስብ ሰው ይህ የሆሄያቱ ጥንታዊ የድምፅ ልይዩነት - የፍቺ-ዐዛይነት እየቅላዊ ሚናቸው - ዐይታየውም:: ስለማይታየውም ሆሄያትን እንግደፍ/እንቀንስ የሚል ሐሳብ በቀላሉ ይማርከዋል::

ድምፀ-ሞክሼ ሆሄያት ያሏቸውን የፍቺ-ዐዛይነት ሙያ አጥንተን እነርሱን ባግባቡ መጠቀም በዐማርኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት ውስጥ የሚታየውን ኢመደበኛነት በከፊል ማስወገድ

ወደሚቀጥለው ገጽ ▶

ያስችለናል። በጽሑፍ የሚቀርቡ ሐሳቦችን በአቅጩ ለመግለጽ ይረዳናል። ቋንቋው ከሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር ያለውን ዝምድና ለማየት/ለማሳየት ያበቃናል።

በርግጥ የዐማርኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት መደበኛነትን በቅንስ ፊደል ማጽናት ይቻላል፤ ከድምፀ-ሞክሼ ሆሄያቱ አንዳንድ ብቻ አስቀርቶ ሌሎቹን በመግደፍ። ይህ ምርጫ ግን ከላይ የጠቀስኳቸውን የሥርውቃላዊ ሆሄ ጥንቀቃ (orthography) ጥቅሞች የሚያሳጣ ነው። በታሪክ፣ በርቅቀት (sophistiation) እና በውበት የላቀን ፊደል ትቶ የተራቈተ ፊደልን መምረጥ ነው። ቅንሱ ፊደል የመማር ማስተማር ኺደትን ያቀልላል፣ መሃይምነትን ለማጥፋት የሚደረግ ጥረትን ያቀላጥፋል የሚሉ ማመካኛዎች ግን በኔ አተያይ እምብዛ አሳማኝ አይደሉም።

እንዲያም ብዬ ግን ቅንሱ ፊደል ይዘት-ጠበቅ ኾኖ ሥራ ላይ እስከዋለ፣ ደግሞም የምልኡ ፊደል ተኪ እስካልኾነ በዐማርኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት ውስጥ ግልጋሎት ሊኖረው እንደሚችል ዐስባለኹ። ለምሳሌ ወግ-ለቀቅ (in-formal) ጽሑፎችን ለማቅረብ ተመራጭ ፊደል ሊኾን ይችላል። መንግሥታዊ ሰነዶች፣ የሕግ፣ የፍልስፍና፣ የትምህርት፣ ወዘተ. ጽሑፎች በምልኡ ፊደል ሆሄ ጠንቅቅው መጻፋቸው ደንብ ከኾነ፣ ጓደኛሞች የሚለዋወጧቸው ደብዳቤዎች፣ ወዘተ. ደግሞ በቅንሱ ፊደል ይዘት-ጠብቀው ቢጻፉ ጉዳት ያለው አይመስለኝም። ወገኛም ወግ-ለቀቅም ጽሑፎች መደበኛ ኾነው (ሆሄ ጠንቅቀው) እስከተጻፉ ችግር የሚኖር አይመስለኝም። እንዲያውም ሦስተኛ ሥርዐተ-ጽሕፈትም ማከል ይቻላል፤ በዐማርኛ ሌጣ ሆሄያት (ግእዝ በሚባሉት) ብቻ የሚጻፍ። እንዲህ ዐይነቱ ደግሞ በተንቀሳቃሽ ስልክ ለሚላክ ዐጭር ጽሑፍ መጻፊያ ምቹ ሳይኾን አይቀርም።
ቅንሱን ፊደል ብቻ ብንጠቀም መደበኛ የጽሕፈት ሥርዐት በገዛራሱ (automatical-ly) አይፈጠርም። ለምሳሌ በምልኡ ፊደል "ሥርዐት" ብለን የምንጽፈውን ቃል በቅንሱ ፊደል "ስራት፣ ስርአት፣ ስርኣት" ብለን እንደ አባባላችን ልንጽፈው እንችላለን። በሌላ አነጋገር ሠ እና ዐ ግዱፍ የኾኑበቱ ቅንሱም ፊደል ቢኾን ብሂል-መር አጻጻፍን እስከተከተለ መደበኛነት አያገኝም። ችግሩ የድምፀ-ሞክሼ ሆሄያትን አጠቃቀም አለማወቅ ብቻ አይደለም፤ ከብሂል-መር አጻጻፍም አለመላቀቅ እንጂ። ሥርውቃላዊ አጻጻፍ አስፈላጊነቱ ለድምፀ-ሞክሼ ሆሄያት መለያ ብቻ እንደኾነ ማሰብ ስሕተት ነው። ‹አረገ›፣ ‹ግርግዳ›፣ ... የሚሉት ብሂል-መር አጻጻፎች ‹አደረገ›፣ ‹ግድግዳ›፣ ... በሚሉ አጻጻፎች ሊታረሙ የሚችሉት የቃላቱን ዐምዶች ወይም ሥሮች በማወቅ ነው።
ለማጠቃለል አንድ መደበኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት ለዐማርኛ ሥነ-ጽሑፍ እድገት አስፈላጊ ነው እላለኹ። ለቋንቋው ሥነ-ጽሑፍ ግን ከአንድ በላይ መደበኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት መኖሩ ችግር አይመስለኝም። ችግር የሚኾነው ቋንቋውን ፍጹም አምልቶ እና አስውቦ ሊያቀርብ የሚችለውን ጥንታዊ ፊደል ጥሎ በዘበናይ ቅንስ ፊደል መጻፍ እና ከኹሉም ይልቅ የሚጠቀሙበትን ፊደል ደንብ ሳይጠብቁ መጠቀም ነው።

**ውይይት፦ ቋንቋው እንዲያድግ (እንዲዳብር) በትምህርት ተቋማት፣ በመንግሥት፣ በምሁራን፣ በኅብረተሰቡ ወዘተ. ሊሠሩ ይገባቸዋል የምትላቸው ሥራዎች ምን ምን ናቸው?**

**ዶ/ር ግርማ**፦ መንግሥት፣ የትምህርት ተቋማት እና በነዚህ ዙሪያ ያሉ ምሁራን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ምንም ማለት አልችልም። ይህን ያድረጉ፣ ያንን አያድርጉ ለማለት ስለ ቋንቋው ያላቸውን ፖሊሲ እና እንዴት በተግባር እንደሚገልጹት በቅርብ ማጤን አስፈላጊ ነው። ጉዳዩ የትምህርት ፍልስፍናን፣ ሀገራዊ ራእይን፣ የጥሪት ዐቅምን፣ ወዘተ. የሚመለከትም ይመስለኛል። በዚህ ኹሉ ረገድ እኔ መሀይምን ነኝ።
ቋንቋውን እና ሥነ-ጽሑፉን የሚያፈቅሩ፣ ለእድገቱ እና ብልጽግናው በጎ የሚመኙ ሰዎች ግን በግል እና በመተባበር ሊያደርጉ የሚችሏቸው ነገሮች አሉ። ከነዚህ መሠረታዊ የምላቸውን ልጥቀስ።

- የቋንቋው ሥርዐተ-ጽሕፈት መደበኛ አለመኾን ለእድገቱ እንዴት መሰናክል እንደሚኾን አጥንቶ ማኅበራሰባዊ ግንዛቤ መፍጠር
- በሥርውቃል ዕውቀት የተመራ ሥርዐተ-ጽሕፈት መደበኛ እንዲኾን ጥረት ማድረግ
- የድርሰት ረቂቆች ከመታተማቸው በፊት የከተባ እና ሌሎች ስሕተቶችን ነቅሶ ለማውጣት በአርትዖት ሥራ መረዳዳት፣
- ባለሙያዎችን ለአርትዖት፣ ለኅትመት እና ለስርጭት ሥራ የሚያሳትፍ ፕሮፌሽናል አሳታሚ ድርጅት አቋቁሞ የድርጅቱን ደረጃ (in-house standard) የሚጠብቁ ጽሑፎችን ለንባብ ማብቃት

እነዚህ የመንግሥት ተቋማትን ርዳታ ግድ የማይሉ ማኅበራዊ/ባህላዊ እንቅስቃሴዎች (social/cultural activities) ይመስሉኛል። በነዚህ እና መሰል ጥረቶች የጥራት እና ብቃት ደረጃቸው ከፍ ያሉ ሥነ-ጽሑፎችን ለአንባቢያን ማቅረብ እንደሚቻል ዐስባለኹ። እንዲህ ዐይነት ሥራዎች ተቀባይነት ሲያገኙ ደግሞ ሌሎች ይከተሏቸዋል። በኺደት ሀገራዊ የሆሄ ጥንቀቃ እድብ ይፈጠራል፤ ለቋንቋው ሥነ-ጽሑፍ እና ሥርዐተ-ጽሕፈት መደበኛነት የሚያስገኝ እድብ።
አኹን ባለው ውጥንቅጥ ሥርዐተ-ጽሕፈት ውስጥ በምልኡ ፊደል የሚጻፉ አንዳንድ ቃላት ሆሄ ጠንቅቀው ይጻፋሉ። ለምሳሌ ‹አባት› እንጂ ‹ዐባት/ዓባት› ተብሎ ሲጻፍ አናይም። እንዲያ ቢጻፍ ብዙ አንባቢ አላባት መጻፉን ልብ ይላል። የሚለብመው ግን በመንግሥት ወይም በተቋም ዐዋጅ አማካይነት አይደለም። ቃሉን በሚያነብበት አጋጣሚ አዘውትሮ የሚያየው አሌፍ አ በሌላ ድምፀ-ሞክሼ ሆሄ ተተክቶ ስለሚያይ ግር ተሰኝቶ ነው፤ ደንብ ያልጠበቀ አጠቃቀም ኾኖ ስለሚታየው ነው። ይህ የሚያሳየን ይዘት-ጠበቅ በኾነ ሆሄ ጥንቀቃ አንብቢን ወደ አንድ መደበኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት ማምጣት እንደሚቻል ነው። በርግጥ ጊዜ ይወስዳል። ሲጸና ግን በመንግሥታዊ ዐዋጅ ከሚኾነው የበለጠ ቅቡልነት አለው፤ በፍቃድ እና በአብነት ሀገራዊ እድብ ስለሚኾን።
ጉዳዩ ይመለከተናል፣ ኀላፊነት ይሰማናል፣ ለችግሩ መፍትሔ ማስገኘት እንችላለን የሚሉ ደራሲያን፣ ጋዜጠኞች፣ መምህራን፣ ወዘተ. በሥረውቃል ደንብ ሆሄ ጠንቅቀው ቢጽፉ እልፍ አእላፍ አንባቢዎቻቸው የነርሱን ፈለግ የሚከተሉ ይመስለኛል። ቀስ-በ-ቀስ መደበኛ የዐማርኛ ሥርዐተ-ጽሕፈት ይሰፍናል።
የኮምፒዩተር ፕሮግራም ጸሓፊዎችም ከቋንቋው ሊቃውንት ጋር ተባብረው ሆሄ ማጠንቀቂያ ፕሮግራም (spell checker) ማዘጋጀት ይችላሉ። እንዲህ ዐይነቱ ፕሮግራም ከዐማርኛ መክተቢያ ፕሮግራም ጋር የተቀናጀ ሲኾን የሥርዐተ-ጽሕፈትን እድብ ለማጽናት ከፍተኛ ተዋፅኦ ያደርጋል። በዚህ ረገድ የአቶ ወሌ ነጋው የዋዜማ ሥርዐት (http://gzamargna.net/) እና የኢትዮክላውድ አገልግሎት (https://www.ethiocloud.com/) ጅማሮዎች ተስፋ የሚሰጡ ናቸው።

**ውይይት፦ መዝገበ ቃላት ላንድ ቋንቋ መዳበርና ማደግ ያለውን አስተዋጽዖ እንዴት ትገልጸዋለህ? ለዚህ ይረዳ ዘንድስ አንተ ያዘጋጀህው መዝገበ ቃላት ምን አስተዋጽዖ ያበረክታል ትላለህ? ሌሎች ተመሳሳይና ሰፊ መዝገበ ቃላቶች ያስፈልጋሉስ ትላለህ? ካስፈለገስ እንደዚህ ዓይነት ሰፊ ጥናት፣ ዕውቀትና ትዕግስት የሚጠይቅ ሥራ ለመሥራት ምን ያስፈልጋል ትላለህ?**

**ዶ/ር ግርማ**፦ መዝገበ-ቃላት የቋንቋን የቃላት ሀብት በሥርዐት ሰብስቦ እያንዳንዱ ቃል በሥነ-ጽሑፍም ኾነ በሥነ-ቃል አጠቃቀም ያዘለውን ፍቺ (ያዘላቸውን ፍቺዎች) መሠረት ያደረገ ብያኔ የሚሰጥ መድበል ነው። እንዲያ በመኾኑም ለቋንቋው ወጥ እና መደበኛ ኾኖ ማደግ ያለው ተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። የቃላቱን ሆሄ ጥንቀቃ በማሳየት ሥርዐተ-ጽሕፈቱ መደበኛነት እንዲኖረው ይረዳል። ቃላቱ በጽሑፍ ወይም በንግግር ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚሰጡትን ፍቺዎች በመዘርዘር ዝንኵር አጠቃቀሞቻቸውን ለማረሚያ መመሪያ ይኾናል። መዝገበ-ቃላቱ ልሂቅ እና ፍጹም የተሟላ ሲኾን፣ ያካተታቸውን ቃላት ታሪካዊ አመጣጥ፣ ሰዋሰዋዊ ምድባቸውን፣ ወዘተ. በተጨማሪ መረጃነት ስለሚያቀርብ የ-ኢንሳይክሎፒዲያ ባሕሪ ያለው ታላቅ የዕውቀት ምዕቃል (pool) በመኾን ያገለግላል።
የኔ ማከያ መዝገበ-ቃላት ተዋፅኦ ውሱን ነው። ወጥ እና የተሟላ ሥራ አይደለም። ማከያ በመኾኑ ጠቀሜታው እርሱ በሚያግዛቸው ዕጥር-ምጥኖቹ የዐማርኛ መዛግብተ-ቃላት

ቀዳማዎች (objectives) ላይ የተመሠረተ ነው። እንዲያም ኾኖ ስለ ዐማርኛ የቃላት ሀብት ግዙፍነት፣ ስለ ሥርውቃላዊ ሆሄ ጥንቀቃ ፋይዳ፣ ስለ እላዴ ቃላት ሥነ-ዘዴ (lexicographic methodology) ፍንጭ ሰጭ በመኾን መድበሉን በሚጠቀሙ ደራሲያን፣ ተርጓሚዎች፣ አርታዒዎች፣ ተመራማሪዎች፣ የቃላት መድበል አዘጋጆች፣ ወዘተ. ዘንድ የባለቤትነት፣ የተቆርቋሪነት ስሜትን ያነቃቃ ይኾናል ብዬ ተስፋ አደርጋለኹ።
ዐማርኛ ቋንቋ መዛግብተ-ቃላት ያስፈልጉታል። የሚያስፈልጉት ግን በእላዴ ቃላት ምድን (discipline) የተዘጋጁ፣ በሥነ-ሥርውቃል ዕውቀት የተመከሩ፣ ብዙ ምሁራንን እና አርታዒያንን አሳትፈው በበቂ መረጃ እና ማስረጃ የበለጸጉ መድበሎች ናቸው። መዛግብተ-ቃላት አስተማማኝ ማጣቀሻ እና ማመሳከሪያ በመኾን ያገለግሉ ዘንድ በተቻለ መጠን የተሟሉ እና ከስሕተት የጸዱ መኾን አለባቸው። ለተማሪዎችም ኾነ ለልሂቃን በየደረጃው በየዕውቀት ዘርፉ የሚዘጋጁ መዛግብተ-ቃላት በነዚህ ሦስት ግብአቶች ከተደራጁ የቋንቋውን ደረጃ ከፍ ለማድረግ እና የገለጻ ክሂሎቱን ላማጎልበት ትልቅ መሣሪያ ይኾናሉ።

**ውይይት፡- መዝገበ ቃላት ማዘጋጀት ትልቅ ትዕግስትና ከፍ ያለ የቋንቋ ዕውቀት እንደሚያስፈልግ ይሰማኛል:: አንተ ይሄን መጽሐፍ ስታዘጋጅ ያሳለፍከውን ውጣ ውረድና አጠቃላይ ሂደቱን ብታስረዳኝ:: በዚህ ሂደት ውስጥስ ያጋጠመህ ተግዳሮትና ፈተና ምን ነበር?**

**ዶ/ር ግርማ**፡- መዝገበ-ቃላት ማዘጋጀት የቃላቱ ምንጭ ስለኾነው ቋንቋ ሰዋስው፣ ሥነ-ቃል እና ሥነ-ጽሑፍ በቂ ዕውቀት ይጠይቃል። ስለ ተዛማጅ ቋንቋዎች መሠረታዊ ግንዛቤ ማግኘት በጣም ጠቃሚ ነው። ስለ መዝገበ-ቃላት አደረጃጀት ስለ ፍቺ አሰሰጣጥ አጠቃላይ እና ልዩ (universal and particular) ደንቦችን ማወቅ ለሥራው የጥራት ደረጃ እና ዘለቄታዊ ጠቀሜታ ጕልሕ ሚና አላቸው። ቀደምት አላዲ-ቃላት ያዘጋጇቸውን ሥራዎች ማጥናት እና የነርሱን መልካም ቅድጅቶች (achievements) ይዞ የሚቀጥል ዘመነኛ መድበል ማቅረብ ግዴታ ነው።
በርግጥ የመድበል አላዲ ግለሰብ/ቡድን የሚያስፈልጉት የዕውቀት ግብአቶች እንደ ቋንቋው እድገት - ማለትም እንደቃላት ጥሪቱ እና የሥነ-ጽሑፍ ሀብቱ - ይለያያል። ለምሳሌ ተናጋሪ ማኅበረሰብ ለሌለው እንደ ግእዝ ያለ ቋንቋ አላዲውን በዋናነት የሚያስፈልጉት የቋንቋው ሰዋሰው እና ሥነ-ጽሑፉ ይኾናሉ። የራሱ ፊደል እና ሥነ-ጽሑፍ ለሌለው ቋንቋ ደግሞ ሰዋሰዉ እና ሥነ-ቃሉ ተፈላጊ የዕውቀት ዘርፎች ናቸው።
መዝገበ-ቃላት በግለሰብ ደረጃ ማዘጋጀት አላዲውን በብዙ ረገድ ይወግጣል። ከወገጦቹ (challenges) አንዱ ሥራው ብዙ ትዕግሥት መጠየቁ ነው። ከትዕግሥት ሌላ በብቸታ ለመሥራት አእምሯዊ ዝግጁነትን ይጠይቃል። ቃላት ለቀማው እና ስደራው ብዙ ማሰላሰል ስለማይጠይቅ አሰልቺ ይኾናል። ፍቺ አሰጣጥ ግን በእማሬ፣ በፍካሬ፣ በፈሊጥ፣ በቀበልኛ፣ ወዘተ. አጠቃቀም ውስጥ ያሉ ስሜቶችን አምልቶ እና አንጠርጥሮ ለመግለጽ ማሰላሰልን፣ ከአፈታት ደንብ ላለማፈንገጥ ጠንቃቃ መኾንን ስለሚጠይቅ አማላይ ነው። በርግጥ የቃልን ፍቺ በቃል መግለጽ ላይም ትልቅ ፈተና ይገጥማል። የቋንቋው ገላጭነት፣ የአላዲው የገለጻ ችሎታ ሥራውን ሊያከብዱትም/ሊያቀልሉትም ይችላሉ።
የተካተተ ቃል ፍቺዎች ኹሉ አለመዘንጋታቸውን ለማረጋገጥ ከቀደምት መዛግብተ-ቃላትም ኾነ ከታተሙ እና ካልታተሙ የሥነ-ጽሑፍ ምንጮች መመርመር ጊዜ የሚወስድ ጕዳይ ነው። ቀደምት መዛግበተ-ቃላትን ዘመነኛ ለማድረግ በየጊዜው ዐዳዲስ ዝግጅቶች የማሳተም ባህል በሌለበት ኹኔታ ደግሞ የአላዲው ሥራ ሳያስፈልግ ይበልጥ አድካሚ ይኾናል፤ በፈረንጆች አገላለጽ "ጌልጌላን ዳግም እንዲፈጥር" (to re-invent the wheel) ስለሚያስገድዱት። ለምሳሌ ታላቁ የኦክስፈርድ እንግሊዝኛ መዝገበ-ቃላት በአንድ ተቋም ኀላፊነት የሚዘጋጅ በመኾኑ ከተገኙ ጠቀሜታዎች አንዱ በየጊዜው መዝገበ-ቃላቱን ዘመነኛ ማድረግ ሲያስፈልግ ሥራው ነባሩን በማስፋት እና በማምላት ብቻ እንዲወሰን ማስቻሉ ነው።
ሥራው ያለምንም ተቋማዊ እና የገንዘብ ድጋፍ ሲካኼድ ደግሞ ተጨማሪ ትዕግሥት እና ቊርጠኛነት ይጠይቃል። መፍቅዶችን ለማሟለት በሚደረግ ደፋ-ቀና የእላዴ ቃላቱ ሥራ ለወራት እና አንዳንዴም ዓመታት የመቋረጥ ዕድል ይገጥመዋልና።
ከላይ ያነጥብኳቸው ጥቂት ወገጦች እኔንም የገጠሙኝ ናቸው።

**ውይይት፡- በሌሎች አገሮች መዝገበ-ቃላት የሚዘጋጁትና በስፋት የሚሰራጩት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አማካይነት ነው:: በዚህ ረገድ እንደኦክስፎርድና ኬምብሪጅ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያዘጋጇቸው መዝገበ ቃላት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ዕድገት ያደረጉትንና እያደረጉ ያሉትን አስተዋጽዖ መጥቀስ ይቻላል:: በአገራችን በአንጻሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዚህ መስክ ሲሰማሩ አይታይም:: በዚህ ላይ ያለህ አስተያየት ምንድነው? ምንስ ቢደረግ ይሻላል ትላለህ?**

**ዶ/ር ግርማ**፡- በብዙ የለሙ ሀገሮች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወይም ብሔራዊ አካዳሚዎች የብሔራዊ ቋንቋን አስፈላጊነት ስለሚገነዘቡ ቋንቋው መደበኛ እና ልሂቅ ይኾን ዘንድ ዐይነተኛ መሣሪያ እና ማጣቀሻ የሚኾን መዝገበ-ቃላት እንዲዘጋጅ ከፍተኛ ትኵረት ይሰጣሉ። በቂ በጀት መድበው፣ ባለሙያዎች ቀጥረው፣ አስፈላጊዎቹን ቁሳቁስ አቅረበው ሥራው እንዲከውን ያደርጋሉ፤ ወይም የተሠራው ከቋንቋ እድገት ጋር እየተሻሻለ በዐዳዲስ ዝግጅቶች እንዲወጣ ያስችላሉ።
እንዲያ ለማድረግ ሀገራዊ ራእይ እና ምሁራዊ ትጋት ዋና ተፈላጊዎች ናቸው። ዜጎቻቸውን በምጣኔ-ሀብት ብቻ ሳይኾን በባህል፣ በስሜት እና በሥነ-ልቦና አስተሳስረው ወደ ተሻለ የሥልጣኔ እና የብልጽግና ደረጃ ለማድረስ የሚፈልጉ ሀገራት የብሔራዊ ቋንቋን ወሳኝ ሚና ተረድተው እርሱን ለማዳበር እና ከፍተኛ ደረጃ ያለው ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። የሀገራቱ ምሁራን ደግሞ የዚህ ጥረት ግንባር-ቀደም ተሳታፊዎች እና ሐሳብ አመንጪዎች ይኾናሉ። የጥረቱ ጠቀሜታ በመግባባት እና የአንድነት ስሜት በመፍጠር ብቻ አይወሰንም፤ ሀገራዊ በራስ መተማመንንም የሚያጎለብት ይመስለኛል። ቀደም ብለው የለሙትም ኾነ በቅርቡ ፈጣን እድገት እያሳዩ ያሉት ሀገራት ለየራሳቸው ብሔራዊ ቋንቋ ያላቸው ትኵረት ከፍተኛ ነው። አንድን ቋንቋ በርካታ ሀገሮች ሲጠቀሙ እንኳ ይህ ትኵረት በየሀገሩ ሲቀንስ አይታይም። ቻይና ብቻ ሳትኾን፣ ታይዋን፣ ሲንጋፖር እና ማሌዢያ ለመደበኛው ማንዳሪን (ኦፊሴላዊው ቻይንኛ) ከፍተኛ ክብደት ይሰጣሉ። ለዐረብኛ ቋንቋ መደበኛነት የሚተጉ በአልጄሪያ፣ በኢራቅ፣ በጆርዳን፣ በግብጽ፣ ወዘተ. አካዳሚዎች አሉ። እነዚህ አካዳሚዎች፣ ተቋሞች እና ማእከሎች ለየቋንቋው ሥርዐተ-ጽሕፈት ደንብ በማውጣት፣ ለቃላት ሀብቱ እድገት እና የገለጻ ብልጽግና መዛግብተ-ቃላት በማዘጋጀት፣ ለሥነ-ጽሑፉ እና ሥነ-ቃሉ መዳበር ዐይነተኛ መሣሪያ የኾኑ ዜጎችን በገንዘብ እና ቁሳቁስ በመደገፍ የጐላ ሚና ይጫወታሉ።
ከሀገራዊ ራእይ ይልቅ ተፎካካሪ ዘውግ-ተኰር (ethnocentric) ራእዮች ሲገኑ፣ ዩኒቨርስቲዎችም በመንግሥት ጣልቃገብነት እና በካድሬ ምሁራን ሽኵቻ ሲሰናከሉ ለሀገራዊ ቋንቋ እድገት እና ብልጽግና የሚሠራ ተቋም ወይ በጥርጣሬ አሊያም በጥላቻ የሚታይ ይመስለኛል። ስለዚህ የሚቻል ከኾነ ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት እና ከማንኛውም ወገነኛ ሥነ-ሐሳብ ነጻ የኾነ ለትርፍ የማይሠራ መ/ያ/ድ መሥርቶ ለዐማርኛ መዝገበ-ቃላት ስንድት ጥረት ማድረግ መልካም ነው። ምናልባት በእንዲህ ዐይነት ተነሣሽነት አላስፈላጊ ከኾነ ንትርክ ርቆ፣ ከሚያሽቈለቊል የፉክክር አዙሪት አምልጦ ለሀገር እና ለወደፊት ትውልድ ቅርስ የሚኾን (ለሌሎች የሀገሪቱ ቋንቋዎችም አብነት ያለው) መዝገበ-ቃላት ማዘጋጀት ይቻላል።

**ውይይት፡- ከዚህ ሥራ በተጨማሪ የሠራሃቸው ሌሎች ሥራዎች ምን ምን ናቸው? ስለ ይዘታቸው ብታብራራልኝ::**

**ዶ/ር ግርማ**፡- ከዚህ ቀደም በአለቃ ተክለ-ኢየሱስ ዋቅጅራ የተጻፈውን የትውልድ መድበል - "የጐጃም ትውልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ" አዘጋጅቼ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ አሳትሜያለኹ። መድበሉ ዛሬ በጐጃም እና አጐራባቿ የአባይ ተፋሰስ አውራጆች ያሉ ሕዝቦችን የዘውግ ጥንቅር ታሪካዊ ዳራ እና የማንነት ውሕዘት (fluidity) በማሳየት ዛሬ የተጠናወተንን ገራገር፣ ክምም ወይም ዘንባላ

ወደሚቀጥለው ገጽ ▶

(simplistic, blinkered or biased) የማንነት ፖለቲካ አባዜ ሊያሳይ የሚችል ሥራ ነው፤ የሥነ-ሰብእ፣ የታሪክ እና የቋንቋ ምሁራን በጥልቀት ሊያጠኑት እና ምርምር ሊያደርጉበት የሚገባ ሥራ:: ከትውልድ መድበሉ በኋላ በእኒሁ የንጉሥ ተክለ-ሃይማኖት ባለሚል የተጻፈውን እና "የጐጃሙ ታሪከ-ነገሥት" በሚል ስያሜ የሚታውቀውን ሥራቸውንም ተርጒሜ፣ በመግቢያ እና ማስታወሻዎች አዳብሬ በብሪቲሽ አካዳሚ አሳትሜያለኹ:: ኅትመቱ ሙሉውን ሥራቸውን አይሸፍንም፤ 1770-1901 ስለኾነው ታሪክ የሚያወሳውን የጽሑፋቸው ክፍል ብቻ እንጂ:: በፀሓይ አሳታሚ ድርጅት በመታተም ላይ ያለ የትርጒም ሥራም አለኝ:: "ዘመቻ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር" በሚል ርእስ የሚታተመው ትንሽ መጽሐፍ ጂ.ጄ. ቫንደርሃይም ከዐፄ ምኒልክ ጋር ወደ ወላይታ ዘምተው ያዩትን የዘገቡበት የጒዞ ማስታወሻ ነው::

ሌሎች በጅምር እና በመካከለኛ እርከን ላይ የሚገኙ ዐማርኛ-ነክ የጽሑፍ ሥራዎችም አሉኝ:: የዐማርኛ መዝገበ-ቃላት፣ የዕፀዋት እና እንስሳት መድበል፣ አሳሳቢ በምላቸው የቋንቋ አርእስት-ነገር ላይ የሚያተኵሩ ምጥን ጽሑፎች (essays) እና የኅትመት ዳሰሳዎች ናቸው:: የዮሐንስ አድማሱን "እስቲ ተጠየቁ" እና ሌሎች ሥራዎችንም በዐዲስ ዝግጅት የማሳተም ሕልም አለኝ::

**ውይይት፡- በአሁኑ ዘመን በአማርኛ ቋንቋ እየታተሙ ስለሚወጡ የኅትመት ውጤቶች የቋንቋ አጠቃቀም ያለህን አስተያየትና ምልከታ ብታካፍለን:: ልንጠቀምባቸው ስለሚገቡ የቋንቋ ስርዓቶችና አግባቦች የምትጠቁመን ካለ ብታካፍለን::**

***ዶ/ር ግርማ፡-*** ከላይ ለጥያቄዎችኽ የሰጠኋቸው መልሶች ይህን ጥያቄ በገደምዳማ የመለሱት ይመስለኛል:: በተጨማሪ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ የታተሙ ጥቂት የመጻሕፍት ዳሰሳዎች በዚህ ጒዳይ ላይ አስተያየቴን ይገልጻሉ::

ባለፉት ኹለት እና ሦሶስት ዐሥርታት ለንባብ የበቁ እጅግ ብዙ የኅትመት ውጤቶች አሉ:: በፈጠራ ሥነ-ጽሑፍ ረገድም የብዛት ብቻ ሳይኾን የዘውግ ልይዩነት (diversity of genre) ይታያል:: እጅግ ብዙ የቴክኖሎጂ እና የጽንሰ-ሐሳብ ቃላት ተፈጥረዋል:: በደራሲያን ሥራዎች ላይ ምሁራዊ የጥናት ጽሑፎች እና ዳሰሳዎች ይታተማሉ፣ ለጒባኤ እና ለዲግሪ ማግኛ ይቀርባሉ:: በኪናዊ ምናባቸው፣ በፈር-ቀዳጅ ሞካሪነታቸው፣ ወዘተ. የሚያስደምሙ ደራሲያን ከሥራዎቻቸው ጋር ብቅ ብለዋል:: ይህ ኹሉ ደስ የሚያሰኝ ነው:: ግን በብዙ ኅትመቶች ውስጥ የከተባ፣ የሰዋስው እና አገባብ ችግሮች ይታያሉ::

እንከኖቻቸው በተቻለ መጠን ሳይወገዱ የሚታተሙ ሥራዎች በጸሓፊዎቹም ኾኑ "በአሳታሚዎቹ" ዘንድ የቋንቋው ጥራት ደረጃ እምብዛ አሳሳቢ ጒዳይ እንዳልኾነ እንድገምት ያደርጉኛል:: ፍጽምና ያላገኙ ሥራዎችን

> ***ከሀገራዊ ራእይ ይልቅ ተፎካካሪ ዘውግ-ተኰር (ethnocentric) ራእዮች ሲገኑ፣ ዩኒቨርስቲዎችም በመንግሥት ጣልቃገብነት እና በካድሬ ምሁራን ሽኩቻ ሲሰናከሉ ለሀገራዊ ቋንቋ እድገት እና ብልጽግና የሚሠራ ተቋም ወይ በጥርጣሬ አሊያም በጥላቻ የሚታይ ይመስለኛል***

ፈጥኖ የማሳተም ፍላጎት ከምን እንደሚነሣ አስረግጦ መናገር ይቸግራል:: ኾኖም የግንዛቤ ማነስ እና ደንታ-ቢስነት ከምክንያቶቹ ጥቂቱ ሊኾኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል:: እንዲህ ለመገመት የሚያስችሉ ኹለት ምክንያቶችን ላቅርብ::

አንደኛው ምክንያት ለቋንቋው ተቈርቋሪነት የሚሰማው ጸሓፊ በመጀመሪያ ረቂቅ መልክ ያለን ጽሑፍ በቀጥታ ወደ ዐታሚ ድርጅት አይወስድም ብዬ ማሰቤ ነው:: የሐሳብ እና የቋንቋ ጥራት የሚያስጨንቀው ጸሓፊ፣ በዚህ ረገድ ድጋፍ/አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያ አርታዒ እና አሳታሚ ካላገኘ፣ የጽሑፉን ረቂቅ ደጋግሞ እያነበበ ማረሚያ እና ማሻሻያ ለማድረግ፣ የሙያ ጓዶቹን እና የሌሎች ወዳጆቹን ተማግቦ እና ምክር በማካተት ለመከለስ፣ በመጨረሻም ለኅትመት ዝግጁ የተባለውን ክትብ/ኤሌክትሮኒክ ጽሑፍ (typescript) በከተባ ስሕተት ዐራሚ ለማጥራት ይገደዳል ባይ ነኝ:: እንዲህ ሳያደርግ ወደ ማተሚያ ቤት አይኼድም የሚል እምነት አለኝ::

የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኀበር አባላት አብነት ለዚህ እምነቴ ጥሩ ምሳሌ ይመስለኛል:: የአሳታሚ ድርጅት ሙያዊ ድጋፍ አለመኖር የኅትመት ውጤቶችን ጥራት እየጐዳ መኾኑ የማኀበሩን አባላት ሳያሳስባቸው አልቀረም:: ታዲያ የድጋፍ ዕጦቱ የፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት የዘየዱት ነገር ነበረ:: ጒዳዩን በቅርበት ባልከታተልም በአርትዖት ሥራ፣ የኅትመት ወጪዎችን በዟሪ እክብ (rotating fund) በመሸፈን፣ ወዘተ. የርስበርስ ትግግዝ ጀመሩ:: ይህም የኅትመት ውጤቶቻቸው ጥራት አንጻራዊ ልህቀት እንዲያገኝ ረድቷቸዋል::

ኹለተኛው ምክንያቴ የሥነ-ጽሑፍ ጥናት እና ዳሰሳ አቅራቢዎች ሰዋስው እና አገባብ-ነክ ችግሮችን፣ ይዘት-ለቀቅ ሆሄ ጥንቀቃዎችን፣ አጒል እና ዝንኵር የቃላት አጠቃቀሞችን በቸልታ አሊያም በማድበስበስ ማለፋቸው ነው:: ስለ ጽሑፍ ትልም፣ ትርክት፣ ፈትለ-ነገር፣ ስለ ገጸ-ባሕሪያት ፋይዳ እና ተአማኒነት፣ ወዘተ. ዝርዝር ሐተታ እየሰጡ ቋንቋ እና ሥርዐተ-ጽሕፈት ነክ ችግሮችን ነቅሶ አለማውጣት ወይ ከደንታ-ቢስነት አሊያም ችግሩን ከማቅለል (እንደ ችግር ካለማየት) የሚመነጭ ይመስለኛል::

ብዙውን ጊዜ የግል ጋዜጦች እና መጽሔቶች በቋንቋ እና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት የሠለጠኑ ተቀጣሪ አርታኢዎች (inhouse copy editors) አይኖሯቸውም:: የዝግጅትም፣ የአርትዖትም የከተባ ስሕተት ዕረማም የጥቂት ሰዎች ኀላፊነት ይኾናሉ:: መልእክት፣ መረጃ እና ታሪክን ለአንባቢ በጽሑፍ ማቅረብ እንጂ የሥራው ኪናዊ እና ሥነ-ጽሑፋዊ ደረጃ ታሳቢ አይኾኑም::

በሀገሪቱ የሚገኙ አሳታሚዎችም (በርካታዎቹን እንዲያ መጥራት ከተቻለ) የማተም እንጂ በባለሙያ እውቀት እና ልምድ የታገዘ የግምገማ፣ የአርትኦት፣ የስርጭት፣ ወዘተ. አገልግሎት አይሰጡም::

ነባር እና ዘመን-አመጣሽ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ የፖለቲካ፣ የፍልስፍና፣ ወዘተ. ባዕድ ቃላትን የሚተኩ ዐዳዲስ የዐማርኛ ስያሜዎች በኅትመት ውጤቶች ውስጥ ይታያሉ:: ጥረቱ መልካም ኾኖ ሳለ በነዚህ ቃላት ፈጠራም ኾነ አጠቃቀም ላይ የቋንቋው ምሁራን ተሳትፎ ጒልቶ የሚታይ አይመስልም:: ስለ ቃላቱ በምክንያት የተደገፈ ሒሳዊ ሐተታ ስለማይሰጡም አንዳንድ አጒል የተመሠረቱ ቃላት ወይም አጠቃቀሞች ሰፊ ተቀባይነት አግኝተዋል::

የግመገማ እና አርትዖት አገልግሎትን በጥርጣሬ የማየት ዝንባሌ በጸሓፊዎች ዘንድ ይኖር ይኾን እላለኹ:: ሐሳብ እና የፈጠራ ሥራ እንዳይሰረቅ ከሚኖር ተገቢ ሥጋት ያለፈ የትችት ፍራቻ እና ጥላቻ ጸሓፊዎች ዘንድ ካለ ጽሑፍን ማስገምገም እና በባለሙያ አርታዒ ማሳረም የማይታሰብ ነገር ይኾናል፤ አሊያም አላስፈላጊ ለኾነ ወጪ እና የጊዜ ብክነት እንደሚዳርግ ጅል ውሳኔ ይቈጠራል::

በሌላ በኩል በሥነ-ቃል፣ በአፋዊ ቋንቋ እና በሥነ-ጽሑፍ መካከል ያሉ አንድነቶች እና ልዩነቶችን አስመልክቶ የአተያይ/አረዳድ ችግሮች ይኖሩ ይኾን እላለኹ:: ሥነ-ጽሑፍ ከአፋዊ ቋንቋ በምንም ረገድ እንደማይለይ ለሚገነዘብ ሰው ከላይ የተነሡት ችግሮች ችግሮች አይደሉም:: ሥነ-ጽሑፍ በአገባብ፣ በቃላት መረጣ፣ በሐሳብ አደረጃጀት እና አቀራረብ፣ በኪናዊ ምጥቀት፣ ወዘተ. ከንግግር ቋንቋ የላቀ እና የረቀቀ መኾን እንደሚገባው ለሚረዳ ሰው ግን ችግሮቹ ጒልሕ እና አሳሳቢ ናቸው::

ለማጠቃለል የዐማርኛ ጽሑፋዊ ቋንቋ ችግር ገጸ-ብዙ ነው:: መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው ደግሞ ቢያንስ በቋንቋው የሚሠሩ ጸሓፊዎች፣ ደራሲያን፣ መምህራን፣ ሐያሲያን እና አሳታሚዎች ባለድርሻ መኾናቸውን ተገንዝበው፣ ደግሞም በያገባኛል ስሜት ተነሣሥተው በግል እና በኅብረት ሲንቀሳቀሱ ነው::



ብሩህ ዓለምነህ

# የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ እንደ አውሮፓዊው አቻው ለምን ዘመናዊ ማኅበረሰብን መፍጠር ተሳነው? (፫)

ለማስታወስ ያህል፣ በክፍል አንድ መጣጥፌ ላይ የዘመናዊነትን ትርጉምና የአክሱም ሥልጣኔ ከአውሮፓው የግሪክ ሥልጣኔ ጋር በተመሳሳይ ዘመን ተነስተው፣ በተመሳሳይ ዘመንና ምክንያት እኩል መዳከማቸውን ተመልክተናል:: አውሮፓ ከ1000 ዓመታት እንቅልፍ በኋላ ዳግም በትንሳኤ ሲነሳ፣ የእኛው ሥልጣኔ ግን በብሕትውና ሕይወት የተነሳ ለ1700 ዓመታት ተኝቶ መቅረቱን እንዲሁ ተመልክተናል:: የብሕትውና ሕይወት በሦስት ምክንያቶች የክሽፈታችን መንስኤ ነው፡ - ማኒያዊ ባሕልን በመፍጠር፣ በጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥ የሥነ ሰብዕ ትምህርቶች እንዳይካተቱ በማድረግና ማኅበራዊ እንቅስቃሴን በመገደብ:: በክፍል ሁለት ጽሑፌ ላይ የብሕትውና ሕይወታችን ማኒያዊ ባሕልን በመፍጠር እንዴት ለክሽፈታችን መንስኤ እንደሆነ ተመልክተናል:: በዛሬው ጽሑፌ ደግሞ የብሕትውና ሕይወታችን በጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥ የሥነ ሰብዕ ትምህርቶች እንዳይካተቱ በማድረግ እንዴት ለክሽፈታችን መንስኤ እንደሆነና የፈላስፎቻችንን የአዲስ ሥርዓተ ትምህርት ፍለጋ እንመለከታለን::

የብሕትውና ሕይወት ለክሽፈታችን መንስኤ የሆነበት ሁለተኛው ምክንያት ለዘመናት በቆየው ሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥ የሥነሰብዕ ትምህርቶች እንዳይካተቱ ማድረጉ ነው:: የሥነ ሰብዕ ትምህርቶች ማለት የሰውን ልጅ ሕይወት ማዕከል ያደረጉ ትምህርቶች ናቸው፤ "ሰው -ሰው" የሚሸቱ፣ የሰውን ልጅ ሕይወትና ባሕል የሚያንፀባርቁ፣ የሚገመግሙ፣ የሚመረምሩና የሚተቹ፣ የሰውን ልጅ መንፈስና ባሕሪ ዓለማዊ በሆነ አመለካከት የሚያንፁ ትምህርቶች ናቸው - እንደ ቋንቋ፣ ታሪክ፣ ፍልስፍና፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ኪነ ጥበብ … ያሉት::

አውሮፓውያንና አክሱማውያን የብሕትውናን ሕይወት ከተቀበሉ በኋላ ለ1000 ዓመታት እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ መንፈሳዊ ትምህርት ብቻ ሲማሩና ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ፣ አውሮፓውያን ግን ከ12ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ጀምሮ ጥንት በግሪክ-ሮማውያን ዘመን ሲሰጡ ወደነበሩት የሥነ ሰብዕ ትምህርቶች ፊታቸውን ማዞር ጀመሩ:: በተለይ በመስቀል ጦርነቶች ወቅት የአርስቶትል ሥራ ከዐረቦቹ ላይ መገኘት ለአውሮፓ የ13ኛው ክፍለ ዘመን የባሕል ዕድገት አዲስ ኃይል ሰጥቷል:: ለምን የአርስቶትል?

ምክንያቱም የአርስቶትል ሥራዎች በ12ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ እስኪገኙ ድረስ የመካከለኛውን ሙሉ ዘመን ሥነ ዓለማዊ አመለካከት የያዘው ፕሌቶናዊውና ክርስትያናዊው አመለካከት ነበር፤ የሁለቱን አመለካከቶች ጋብቻ ያፈጸመው ደግሞ ቅዱስ አጎስቲን (354 -430) ነው:: ፕሌቶናዊውም ሆነ ክርስቲያናዊው አመለካከት ውስጥ ማዕከላዊውን ስፍራ የሚይዘው እግዚአብሔር (God/The Form of the Good) ነው:: እግዚአብሔርን ከዚህ ማዕከላዊ ስፍራ ያስለቀቀው አርስቶትል ነው:: የአርስቶትል እግዚአብሔር፣ ይኼን ዓለም ፈጥሮ በራሱ እንዲሰራ ትቶታል:: በመሆኑም ለአርስቶትል እግዚአብሔር ሞራላዊ አይደለም:: ክርስትና፣ እግዚአብሔር በሰው ልጅ የዕለተለት ሕይወት ውስጥ ማዕከላዊውን ስፍራ ይዞ እንዲቀይ ያደረገው ሞራላዊ - ለሰው የሚጨነቅ፣ የሚያዝን፣ የሚንከባከብ፣ የሚያፈቅር፣ የሚፈርድ - አድርጎ ስላቀረበው ነው:: አርስቶትል እነዚህን የእግዚአብሔርን ሞራላዊ ባሕሪያት አይቀበልም:: እናም በአርስቶትላዊው ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ማዕከላዊውን ስፍራ ያጣል::

ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአውሮፓ ከፕሌቶ በላይ አርስቶትል ይበልጥ ተቀባይነት እያገኘ መሄዱ ስለሰው ልጅ ሕይወት አዲስ ዓይነት ግንዛቤ እየተፈጠረ እንዲሄድ ምክንያት ሆኗል:: ቀደም ብለው በ11ኛውና በ12ኛው ክፍለ ዘመን የተከፈቱት ዩኒቨርስቲዎችም በዚህ ዘመን ላይ የዓለማዊ ትምህርቶች የልሕቀት ማዕከል (Center of Excellence) ሆኑ:: አዲሱ ትኩረትም የሰውን ልጅ ሕይወት ማዕከል ወዳደረገ የሥነ ሰብዕ ትምህርቶች ሆነ:: እነዚህንም ትምህርቶች ማዕከል አድርገው መላው ምዕራብ አውሮፓ ህዳሴ (ዳግም ልደት/ ትንሳኤ) ብለው ወደጠሩት አዲስ ወደ ሆነ የባሕል ንቅናቄ ገቡ::

አውሮፓ ላይ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ኢትዮጵያውያን ፍራሽ ቀይረው - ከአክሱማዊነት ወደ ላሊበላዊነት ተሸጋግረው - ለጥ ብለው ተኝተው ነበር:: እኛ ኢትዮጵያውያን በጣም የቆየ ሥርዓተ ትምህርት ቢኖረንም፣ የትምህርቶቹ ይዘት ግን ሙሉ በሙሉ ሃይማኖታዊ ሲሆን ዓላማውም በራሳቸው የሚያስቡ ነጻ ዜጎችን መፍጠር ሳይሆን ሃይማኖታዊውን አስተምህሮ ማጥመቅን (indoctrination) ዓላማው ያደረገ ነበር፤ ከሥር ከንባብ ቤት ጀምሮ ያሉ ትምህርቶች በሙሉ በመንፈሳዊ ሕይወት ብቻ የተቃኙና ማጥመቅን ብቻ ዓላማ ያደረጉ ናቸው::

መርስዔኀዘን ወልደቂርቆስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለዘመናት የቆየ አራት የትምህርት ደረጃዎች እንዳሉ ይጠቅሳሉ:: እነሱም ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤት እና ትርጓሜ (መጻሕፍት) ቤት ናቸው::

አቶ ግርማ አማረ Aims and Purposes of Church Education in Ethiopia በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ እነዚህን ባሕላዊ ትምህርቶች ከዘመናዊ ትምህርት ቤቶች ጋር ያስተካክሏቸዋል:: የንባብ ቤትን ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር፣ ዜማ ቤትን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር፣ ቅኔ ቤትን ከኮሌጅ ጋር፣ እንዲሁም ትርጓሜ ቤትን ከዩኒቨርሲቲ ጋር ያስተካክሉታል::

አብዛኛዎቹ የዓለም አገራት፣ እንኳን

ወደሚቀጥለው ገጽ ▶

እንደዚህ ዓይነት ጥንቅቅ ያለ ሥርዓተ ትምህርት ሊኖራቸው ቀርቶ ሐሳባቸውን ወረቀት ላይ የሚያሰፍሩበት ፊደል እንኳን ጭራሽ ባልነበራቸው በዚያ በራቀው ዘመን፣ ኢትዮጵያውያን ግን ለማጠናቀቅ ከ30 ዓመታት በላይ የሚፈጅ የትምህርት ሥርዓት ባለቤት መሆናችን የሚያስደንቅና የሚያኮራ ነው::

| የትምህርቱ ደረጃ | | ትምህርት ቤቱ | ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| ጀማሪ | 1. | ንባብ ቤት | ከ1 ½ - 2½ዓመት |
| መካከለኛ | 2. | ዜማ ቤት | ከ7 - 10 ዓመት |
| | 3. | ቅኔ ቤት | 3 ዓመት |
| ከፍተኛ | 4. | ትርጓሜ (መጻሕፍት) ቤት | ከ13 - 18 ዓመት |
| | | ጠቅላላ | ከ24 - 33 ዓመት |

ጥንቅቅ ያለውን ባሕላዊ ትምህርቶች የሚሰጡ የትምህርት ማዕከላትም በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለምሳሌ - አክሱም፣ ላሊበላ፣ ጎንደር፣ ጎጃም (ዲማ፣ ደብረ ወርቅ፣ ዋሸራ) - ተቋቁመው ነበር:: ከዚህም በተጨማሪ፣ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የልሕቀት ማዕከሎችም ነበሩ:: አቶ ግርማ እነዚህን የልሕቀት ማዕከሎች አሁንም ከአውሮፓውያን የመካከለኛው ዘመን ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ያስተካክሏቸዋል::

"ለምሳሌ ፓሪስ በሥነ መለኮት ትምህርቷ፣ ቦሎኛ በሕግ፣ ቻርትረስ በሥነ ጽሑፍ እንደሚታወቁት ሁሉ፤ በኢትዮጵያም በተለያዩ አካባቢዎች የልሕቀት ማዕከሎች ነበሩ:: ለምሳሌ፣ ዙር አምባ በዝማሬና በመዋሥዕተ ዜማ፣ ዋልድባ እና ደብረ አባይ በቅዳሴ፣ ቤተልሔም በድጓ እና አንዳቤት በጽሑፍ ጥበቡ (በቁም ጽሑፍ አጣጣሉ) የታወቁ የትምህርት ማዕከላት ነበሩ::"

እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የአብነት ትምህርት ቤቶች በዚህ ሥርዓተ ትምህርት አማካኝነት ለቤተ ክህነትና ለመንግሥት ሥራ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ሲያመርቱ ቆይተዋል:: መሳፍንቱና መኳንንቱም ይኼን የሰው ኃይል በየቤታቸው በመምህርነት በመቅጠር ትምህርት እንዲስፋፋ ትልቅ አበርክቶት አድርገዋል::

ጥንቅቅ ያለ ጥንታዊ የሥርዓተ ትምህርት ባለቤት መሆናችን የሚያኮራንን ያህል፣ በርካታ ሐዘንና ቁጭትም ግን አለብን:: የመጀመሪያው ሐዘናችንም የትምህርቱ ዓላማ ዕውቀትንና ተመራማሪነትን ማዳበር ሳይሆን ማጥመቅንና ማነብነብን (ንባብና የቃል ትምህርትን) ብቻ ዓላማው ማድረጉ ነው:: ማነብነብን ይበልጥ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ያለ አንዳች ግንዛቤ የሚከወን መሆኑ ነው:: "በተለይ ንባብ ቤት..." ይላል ግርማ አማረም፡- "በተለይ ንባብ ቤት ለተማሪዎች መንፈሳዊም ሆነ አእምሯዊ ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ምንም ነው:: ይኼ ማነብነቡ (memorization) እና መጻሕፍቱን ሳይመረምሩ እንደወረደ መቀበል አጠቃላይ የቤተ ክህነቱ ተማሪዎች የአስተሳሰብ መገለጫ ነው::"

የችግሩ መነሻ ደግሞ ተማሪዎቹ የሚማሩት በማያውቁት የግዕዝ ቋንቋ መሆኑ ነው:: በዚህም የተነሳ ተማሪዎች ንባብ ቤትና ዜማ ቤት ውስጥ ያሉትን 13 ዓመታት የሚያሳልፉት ስለሚማሩት ነገር አንዳች ግንዛቤ እንኳ ሳይኖራቸው ነው፤ የሚማሩበትን ቋንቋ መማር የሚጀምሩት ገና ወደ ፊት ቅኔ ቤት ሲገቡ ነውና::

የምትማርበትን ቋንቋ ካላወከው ትምህርቱ ሊገባህ አይችልም:: ትምህርቱ ካልገባህ ደግሞ እንደወረደ በሽምደዳ ከመቀበል ውጭ ልትጠይቅና ልትመራመር አትችልም:: በዚህም የተነሳ የተማሪዎች የልጅነት አእምሯቸው "በተቀባይነት" መንፈስ ብቻ ይቀረጻል:: ከዚህ በኋላ ግዕዙን አውቀው መማር ቢጀምሩ እንኳ አንድ ጊዜ ያዳበሩት የተቀባይነት መንፈስ አይላቀቃቸውም:: በመሆኑም በንባብ ቤትና በዜማ ቤት የተጀመረው የተቀባይነት መንፈስ ወደ ቅኔ ቤትና ትርጓሜ ቤት ሲገቡ እንኳ አይሰበርም:: የተቀባይነቱ መንፈስ እስከመጨረሻው ድረስ ተጣብቷቸው ይኖራል:: በዚህም የተነሳ ሜካኒካል ሰው ያመርታሉ:: ለዚህም ነው ከቤተ ክርስትያኑ ትምህርት የወጣው ልሂቅ የሕዝቡን ባሕል፣ አኗኗርና ጉድፉን ማየት ያልቻለው:: ይህ ልሂቅ የነበረውን ልማድ የሚያስቀጥል እንጂ የለውጥ መሣሪያ መሆን ያልቻለው ሥርዓተ ትምህርቱ በተሸከመው ችግር የተነሳ ነው:: ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ ይሄንን የተቀባይነት መንፈስ ነበር በ17ኛው ክፍለ ዘመን ሰብሮ የወጣው::

መምህራኑም ላይ በልምድ የተላለፈ ችግር አለ:: መምህራኑ ራሳቸው የማነብነቡ ትምህርት ውጤት ስለሆኑ ተማሪዎቻቸው እንዲጠይቁና እንዲመራመሩ አይፈቅዱም:: የሚጠይቅ ተማሪም ካለ በመምህሩ ይገሰጻል፤ የጠያቂነቱና የተመራማሪነቱ መንፈስ እንዳያድግ ይኮረኮማል፤ ስም ይወጣለታል፤ "ገና ከአሁኑ መጠየቅ ጀመርክ፣ አንተ መናፍቅ!!" ይባላል:: በዚህም የማወቅና የመመራመር ፍላጎቱን ገና በለጋነቱ ያኮላሹበታል:: ሌላው ይቅርና የግዕዙን ንባብ መምህሩ ወደ አማርኛ እንዲተረጉምለት መጠየቅ አይችልም፤ "የአማርኛው ፀሎት አይሰምርም!! በግዕዙ ተወጣው!!" ይሉታል::

በቤተ ክርስትያን ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የዳበረው ይኼ የተቀባይነት መንፈስና የሚጠይቅን ተማሪ የመኮርኮሙና ስም ለጥፎ የማጥቃቱ ልማድ በአገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥም ሰርጎ ገብቷል:: ሲጀመር የአገሪቱን የፖለቲካ ሥልጣን የተቆጣጠሩት በቤተ ክርስትያኗ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ያለፉ ልሂቃን ናቸው:: በዚህም የተነሳ ፖለቲካችን የቤተ ክህነቱን ባሕል ቢወርስ አያስገርምም:: አዲስ ሐሳብን መፍራትና የተለየ ሐሳብ ያለውን ሰው "ስም" እየለጠፉ እንዲሰደድና ከኅብረተሰቡ እንዲገለል ማድረግ፣ ማስደብደብ፣ ያለ ፍትሕ ማሰር፣ ባስ ሲልም መግደል ከ14ኛው ክፍለ ዘመን የአፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት የኢሕአዴግ ዘመን ድረስ ሊላቀቀን ያልቻለ ክፉ ደዌያችን ነው:: ኢሕአዴግ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ይለዋል:: ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ማለት በቤተ ክርስትያን ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የኔታው ተማሪዎችን "እንዳትጠይቁ፣ እንዳትመራመሩ፣ እኔ የምላችሁን ብቻ ተቀበሉ" እያሉ ያስተማሩት የሃይማኖታዊው ልማድ ፖለቲካዊ መልክ ነው::

የፖለቲካ ደዌያችን ሥረ መሠረቱ ደግሞ በጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ያለው ችግር ነው:: ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብም በመጀመሪያ አምፆ የወጣው በዚህ የጥንቱ ሥርዓተ ትምህርት ላይ ነው:: የአመፁ መጀመሪያውም ሥርዓተ ትምህርቱ "ማጥመቅና ማነብነብ" በሚል ዓላማ ላይ መቆም የለበትም የሚል ነው:: አክሱም ወንበር ዘርግቶ ሲያስተምር "ማጥመቅ" የሚለውን

*አዲስ ሐሳብን መፍራትና የተለየ ሐሳብ ያለውን ሰው "ስም" እየለጠፉ እንዲሰደድና ከኅብረተሰቡ እንዲገለል ማድረግ፣ ማስደብደብ፣ ያለ ፍትሕ ማሰር፣ ባስ ሲልም መግደል ከ14ኛው ክፍለ ዘመን የአፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት የኢሕአዴግ ዘመን ድረስ ሊላቀቀን ያልቻለ ክፉ ደዌያችን ነው*

▶ሃይማኖታዊውን የትምህርት ዓላማ “ወገንተኛ ሳይሆኑ መመርመርና መጠየቅ” በሚለው ተካው፣ “ማነብነብ” የሚለውን የማስተማሪያ ዘዴ ደግሞ “መወያየትና መከራከር” በሚለው ዘዴ ለወጠው:: ይሄ ነው የዘርዓያዕቆብ የትምህርት አብዮት!!!

ሁለተኛው የሐዘናችን ምንጭ ደግሞ፣ ከ30 ዓመት በላይ በሚፈጀው በዚህ ረጅም ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም መንፈሳዊ ዕውቀት ብቻ መሆኑ ነው:: ሊቀ ሥልጣናት ሀብተማርያም ወርቅነህ “ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት” በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ይሄ አስተያየት ቤተ ክርስትያን ላይ ከበፊት ጀምሮ ሲሰነዘር እንደነበረ ያምናሉ፦ “ብዙ ጊዜ እንደሚተቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን በልዩ ልዩ ጥበብ ሳትራቀቅ የቀረችው በዜማ ተወስና ነው፤ ዜማ ቤት ቤተ ክርስትያንን ገደለ ይላሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ራሱ ዜማው አንድ ጥበብ ከመሆኑ ሌላ ለሌሎች ጥናቶች በር የሚከፍት ትምህርት ነው::”

የትችቱ መነሻ “ቤተ ክርስትያን የዜማ ትምህርት ላይ ኃይሏን ጨርሳለች” የሚል ቢሆንም፣ በሌሎች ትምህርቶች ላይም መንፈሳዊ ዕውቀት ላይ ብቻ የሙጥኝ ማለቷ የሰውን ልጅ ምልዑነትን (የመንፈሳዊና ዓለማዊ ሕይወት ከፍታን) ማምጣት ተስኗታል:: ባጠቃላይ፣ ትምህርቶቹ የሰውን ልጅ ምድራዊ ሕይወትና ዕውቀት የሚያንቋሽሹ፣ ምነናን፣ ምንኩስናንና ብሕትውናን የሚያወድሱ እንዲሁም የአምላክን፣ የመላዕክትንና የቅዱሳንን ኃያልነት እያሳዩ፣ ቅዱሳኑ ለሰው ልጅ የሚያደርጉትን በረከት የሚያወድሱ ናቸው:: ማስተማሪያ መጻሕፍቱ ሁሉ በጸድቃን፣ በሰማዕታትና በመላዕክት ገድል እና ድርሳናት ብቻ የተሞሉ ናቸው::

በዚህ ሁሉ ውስጥ ታዲያ የሰው ልጅ ሕይወቱ፣ ኑሮው፣ ኃይሉና ታሪኩ የተረሳ ነው:: በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ የሰው ልጅ ወደ ጠርዝ የተገፋና ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ታላላቅ ተግባራትን ሊያደርግ እንደማይችል ይታመናል:: ያሬድ ዜማን ሲፈጥርና ድምፅን ወደ ጽሑፍ ሲቀይር፣ ንጉሥ ላሊበላ አስገራሚ ፍልፍል የቤተክርስቲያን ኪነ ሕንጻዎችን ሲሠራ፣ አለቃ ገብረሃና የተክሌ አቋቋምን ሲፈጥሩ እንደ እግዚአብሔር ተዓምር ተቆጠረ እንጂ ስለ ሰዎቹ ችሎታ አንዳች ነገር አልተባለም::

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ለ1700 ዓመታት በቆየው ሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥ የሥነ ሰብዕ ትምህርቶች ቦታ አልነበራቸውም:: ሃይማኖታዊው ትምህርት ብቻ ይበቃናል ስላልንና ስላልጠገብነውም የጥንቱን የቅድመ ክርስትናውን አክሱማዊ ሥልጣኔ ወደ መናፈቅ አልገባንም:: በመሆኑም እንደ አውሮፓውያኑ ዓይነት የሥነ ሰብዕ ፕሮጀክት በእኛ አገር አልነበረም:: የሥርዓተ ትምህርቱ ዓላማ የሰውን ልጅ ምድራዊ ሕይወትና የማኅበረሰቡን ኑሮ በዕውቀት ማሻሻል ሳይሆን፣ ጭራሽ ምድራዊ ሕይወትን በመናቅ መንፈሳዊ ከፍታን ማምጣት ነው:: እሳቤውም ከዚህ ዓለም ይበልጥ ስንነጠል፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ይበልጥ ከፍ እንላለን የሚል ነው:: በሥርዓተ ትምህርቱ ይበልጥ ወደ ላይ ከፍ እያልን ስንሄድ ይበልጥ ምናኔውን እያሳደገው ይሄዳል፤ ለዓለማዊ ሕይወት ያለንን ንቀት እየጨመረው ይሄዳል::



ይኼ ነበር የ17ኛው ክፍለ ዘመን ፈላስፎቻችን ተቃውሞ፤ ምናኔንና መንፈሳዊ ሕይወትን ብቻ ዓላማው ያደረገ ሥርዓተ ትምህርት የሰውን ልጅ ዕድሜ ከመብላት ውጭ በሰው ልጅ ምድራዊ ሕይወት ላይ ምንም ፋይዳ የለውም:: ለ1700 ዓመታት የቆየ ሥርዓተ ትምህርት እንዴት አንድ ነገር እንኳ መለወጥ ያቅተዋል? ፐ/ር መስፍን “መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ” በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ “ነጻነትንና ክብርን ከአባቶቹ የወረሰው ትውልድ ለሚቀጥለው ትውልድ ምን አወረሰ? ምን አዲስ ነገርን ፈጠረ? ማኅበረሰቡን በምን የኑሮ ደረጃ ላይ አደረሰ?” እያሉ ትውልዱን ከሚወቅሱ ይልቅ ጣታቸውን ለ1700 ዓመታት በቆየው ሥርዓተ ትምህርታችን ላይ ቢቀስሩ እና 1700 ዓመታት ሙሉ መካን ያደረገንን ሥርዓተ ትምህርት ቢሞግቱ ይሻላቸው ነበር::

ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብም አምፆ የወጣው፣ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን ልማድ ከማስቀጠል በስተቀር በሰው ልጅ ሕይወት ላይ መሠረታዊ ለውጥ በማያመጣው በዚህ ሥርዓተ ትምህርት ላይ ነው:: ደግሞም ማመፅ ብቻ ሳይሆን ተገዳዳሪ ትምህርትም አምጥቷል:: በእኛ አገር ሰውን ማዕከል ያደረገ ትምህርት (የሥነ ሰብዕ ፕሮጀክት) ለመጀመር እንቅስቃሴ የተጀመረው የብሕትውና ሕይወትን ከተቀበልን ከ1100 ዓመታት በኋላ በ17ኛው ክፍለ ዘመን በፈላስፎቹ በዘርዓያዕቆብና በወልደ ሕይወት ነው:: ዘርዓያዕቆብና ወልደ ሕይወት እንደዚህ ዓይነት የሰውን ልጅ ዕውቀትና ችሎታ የሚያኮስስና ምድራዊ ሕይወቱንም ወደ ጠርዝ የሚገፋ ትምህርት ቀርቶ የሰውን ልጅ ዕውቀት፣ ችሎታና ሕይወት ማዕከል ያደረገ ትምህርት እንዲጀመር ሙከራ ያደረጉ ግንባር ቀደም ኢትዮጵያውያን ናቸው::

በእነዚህ ፈላስፎች ትምህርት ውስጥ እግዚአብሔር “አጋዥ” እንጂ ዋናውን ሥራ ለሰው ልጅ የሚሠራ ኃይል አይደለም:: እግዚአብሔር፣ የሰው ልጅ በጥረቱ አንድ ነገር ካሳካ በኋላ “የሚያመሰግኑት” ኃይል እንጂ የሰውን ልጅ ጥረት ተክቶ የሚሰራ ኃይል አይደለም:: ዘርዓያዕቆብ እንዲህ ይላል፦ “ወልደዮሐንስ እንደገና በውሸት ሲከሰኝ ግን መሸሽ ስለተቻለኝ እግዚአብሔር እንዲያድነኝ እንደበፊተኛው ሳልፀልይ ሸሸሁ:: ሰው እግዚአብሔርን በከንቱ ሳይፈታተነው የሚቻለውን ሁሉ በራሱ ሊያደርግ ይገባዋልና::”

ኢትዮጵያውያን ግን እግዚአብሔርን የሚያስቡት እንደ ፈላስፎቹ አይደለም:: ለኢትዮጵያውያን እግዚአብሔር የማይገባበት ቦታ የለም፤ በእያንዳንዷ ስንጥር ሕይወታችን ውስጥ - በምቀኝነታችንና በእርግማናችን ውስጥ ሳይቀር - እግዚአብሔር አለ:: ፐ/ር መስፍን ወልደማሪያምም ኢትዮጵያውያን እግዚአብሔር ላይ ያለንን ከመጠን በላይ የሆነ ቅጥ ያጣ ጥገኝነት ሲገልፁ “እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ረስቶ የኢትዮጵያውያንን የዕለተለት ሕይወት በመከታተል ብቻ ባተሌ (busy) ሆኗል፤” ይላሉ “ኢትዮጵያ ከየት ወዴት?” በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ::

አሁን ድረስ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያውያን ፐ/ር መስፍን እንዳሉት ነው:: ዘርዓያዕቆብና ወልደ ሕይወትም በ17ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሲታገሉ የነበረው ከዚህ ቅጥ ያጣ የእግዚአብሔር ጥገኝነት ተላቀን ስለራሳችን ሕይወት ራሳችን ሙሉ ኃላፊነት እንድንወስድ ነው:: የሰው ልጅ ስለ ራሱ ሕይወት ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ ደግሞ፣ በመጀመሪያ ስለራሱ ተፈጥሮና ችሎታ፣ በውስጡ ስላለው የአመክንዮ ኃይል ማወቅ አለበት:: የሥነ ሰብዕ ትምህርቶች በተለይም የፍልስፍና ዋና ዓላማ ይኼ ነው - የሰውን ልጅ ስለ ራሱ ማስተማር:: በክፍል 4 እና በመጨረሻው መጣጥፌ ደግሞ የብሕትውና ሕይወት ማኅበራዊ እንቅስቃሴያችንን በመገደብ እንዴት የክሽፈታችን መንስኤ እንደሆነ እንመለከታለን:: ፀ

*ብሩህ ዓለምነህ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር ሲሆኑ፣ “ፍልስፍና (ቁጥር ፩ እና ፪)” የተሰኙ መጻሕፍት ደራሲ ናቸው። በኢሜል አድራሻቸው* brooha3212@gmail.com *ላይ ይገኛሉ ።*



ተሾመ ተስፋዬ

# ፖለቲካዊ ሙስና፤

## “ትላልቅ ሙሰኞች” እና “የፀረ ሙስና ትግሉ” ፈተናዎች

ዕውቁ የሰላማዊ ትግል አባት ማሕተመ ጋንዲ “ምድር ለሁላችንም የሚያስፈልገንን ለማሟላት የምትበቃ ቢሆንም የእያንዳንዳችንን ስግብግነት ግን ማሟላት አትችልም::” በማለት ዘመን ተሻጋሪ መልዕክት አስተላልፎልናል፤ ሰሚ ከተገኘ:: በአገራችን ተንሰራፍቶ ለሚገኘው ስግብግብነትና ሙስና በጊዜ መላ ካልተበጀለት እንደ አገር የመቀጠላችን ዕድል ጭምር አደጋ ላይ ሊወድቅ የሚችል መሆኑን ለማስረዳት አቅም ያለው ይመስለኛል፤ ሰሚ ከተገኘ:: በአገራችን ያለው ሙስና አስጊ ሁኔታ ላይ የደረሰውና መፍትሔ ያላገኘው ገዢው ፓርቲ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ ሥልጣኑን ለማደላደል ሲፈጽማቸው ከነበሩ ፖለቲካዊ ሙስናዎች ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው ነው:: ሙስና የሚፈጸመው በባለሥልጣናቱ ብቻ ሳይሆኑ ገዢው ፓርቲ እራሱ ሥልጣኑን ያደላደለው የተለያዩ ፖለቲካዊ ሙስናዎችን በመፈጸም ነው በማለት ብዙዎች ይከራከራሉ::

ኢሕአዴግ ሥልጣን በያዘ ማግስት በወቅቱ በነበረው ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ግፊት እና የምዕራባዊያንን ድጋፍ ለማግኘት በማሰብ የታገለለትን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮት ለጊዜው መሳቢያ ውስጥ በመክተት በሊብራሊዝም አስተሳሰብ የተቃኘ የነጻ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት ቃል ገብቶ የነበረ መሆኑ ይታወቃል:: በዚሁ መሠረት የፖሊሲና የሕግ ማሻሻያዎችን ያደረገ ቢሆንም ሂደቱ ፖለቲካዊ ሙስና የተፈፀመበት ነበር በማለት በርካቶች ይተቻሉ:: ለምሳሌ አቶ ጉደታ ከበደ በጥናታዊ ጽሑፋቸው ላይ ሌሎች የውጭና የአገር ውስጥ ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ ኢሕአዴግ በወቅቱ የነበረውን የሥልጣን የበላይነት በመጠቀም ግልጽነት በጎደለውና አድልዎ በሰፈነበት አሠራር የመንግሥትና የሕዝብን ንብረት ከፓርቲው ጋር ለተጣቡ የኢንዶውመንት የንግድ ድርጅቶችና ደጋፊ ግለሰብ ነጋዴዎች በማዛወር ፖለቲካዊ ሙስና ፈጽሟል በማለት ይሞግታሉ::

መንግሥት በበኩሉ ድርጅቶቹ ለሕዝብ ጥቅም የተቋቋሙ እንጂ የፓርቲ ንብረት አይደሉም፤ የተፈፀመ አድልዎም የለም በማለት ከመከራከር ቦዝኖ አያውቅም:: ተቺዎቹ ግን ድርጅቶቹ ኢንዶውመንት የሚለውን ስም ከመያዝ ባለፈ በአገሪቱ ኢንዶውመንት ሕግ መሠረት የማይተዳደሩ፣ በፓርቲውና በመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት የሚመሩና ልዩ ድጋፍ የሚደረግላቸው፣ ለሕዝብ ጥቅም ሳይሆን ፓርቲው አጠቃላይ ኢኮኖሚውን በመቆጣጠር ሥልጣኑን ለማደላደል የተጠቀመባቸው መሆኑን ይገልጻሉ:: ጉዳዩ እስካሁንም መቋጫ ያልተበጀለት ቢሆንም ተጨባጭ እውነታው ሲታይ የተቺዎቹ ሐሳብ ሚዛን የሚደፋ መሆኑ ላይ ብዙዎች ይስማማሉ::

### የ“ዝንቦቹ” ወረራ

መልካም አስተዳደርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል የሚቻለው ከፖለቲካ ገለልተኛ ሆኖ በሙያዊ ብቃት የሚመራ የሲቪል ሰርቪስ ተቋም ሲኖር እንደሆነ አያከራክርም:: ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞች ቅጥርና የዕድገት አሰጣጥ ሥርዓት ብቃትንና የሥራ ውጤት ምዘናን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል:: የዓለም ባንክ እ.ኤ.አ. በ1997 ባወጣው ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው መንግሥት ሙስናንን ለመዋጋትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ለማድረግ ቃል ገብቶ ነበር:: ማሻሻያውን ተግባራዊ ለማድረግም በርካታ የፖሊሲ፣ የሕግ እና የመዋቅር ለውጦች ተደርገው ነበር:: ሆኖም ፕሮግራሙ የተተገበረበት መንገድ እና ውጤቱ ሲታይ ሲቪል ሰርቪሱ ገለልተኛ ሆኖ መልካም አስተዳደርን ከማስፈን ይልቅ በገዢው ፓርቲ ፖለቲካዊ ቁጥጥሩ ሥር እንዲውል ተደርጓል ማለት ይቻላል:: መንግሥት በተለይም ከፍተኛና መካከለኛ የመንግሥት ሠራተኞችን ለመሾምና ለመመደብ የተከተለው ፖሊሲ ለጉዳዩ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው:: መንግሥት ከትምህርትና ብቃት ይልቅ የፖለቲካ ታማኝነትንና የብሔር ተዋጽዖን እንደዋና መስፈር እንደሚጠቀም ተደጋግሞ የተገለጸ ጉዳይ ነው:: አቶ መለስ እራሳቸው አንድ ሰው የኢሕአዴግ ፖሊሲን እስከተቀበለና ለድርጅቱ ታማኝ እስከሆነ ድረስ ትምህርት ባይኖረውም ሚኒስትርም ሆኖ ሊሾም እንደሚችል በአደባባይ መናገራቸው አይዘነጋም::

በ1993 የሕወሓት ክፍፍልን ተከትሎ በተካሄደ የማዕከላዊ ኮሚቴ ጉባኤ ላይ አቶ መለስ በትግርኛ ጽፈው ባቀረቡት የመወያያ ሰነድ ላይ “…. ሥልጣን የያዝን በመሆኑ ወደ እኛ የተጠጋ የተለያዩ ጥቅሞችን ማግኘቱ አይቀርም:: ማር ባለበት አስቀድሞ የሚያንዣብበው ዝንብ ነው፤ ሥልጣን ባለበት ደግሞ አስቀድሞ የሚያንዣብበው ከዚሁ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልግ ነው:: ዝንብን ከንብ የምትለይበት ተጨባጭ መስፈርት እስከሌለ ድረስ የሚካሄደው ምልመላ አጋጣሚ ብቻ ሳይሆን፣ ንብና ዝንብ ተደባልቀው ለመለየት የሚያስቸግሩበትና በርካታ ዝንቦች የሚያንዣብቡበት ይሆናል::” የሚል ትርጉም ያለው ሐሳብ ማስፈራቸውን አቶ ገብሩ አሥራት “ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ” በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ገልጸዋል:: መንግሥት የተሿሚውን ፖለቲካዊ ድጋፍ የሚያገኝ ሲሆን ተሿሚው ደግሞ ኢኮኖሚያዊና ተዛማች ጥቅሞችን ያገኛል:: በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ ኢሕአዴግ አባላትን ለማብዛት ባደረገው ሰፊ እንቅስቃሴ የተነሳ ዝቅተኛ ሥራ ለማግኘት እንኳን የፓርቲ አባልነት የሚጠየቅበት ደረጃ ላይ መደረሱ የአደባባይ ሚስጢር ነው:: ኢሕአዴግ ሲመጻደቅበት የነበረው የ6 ሚሊዮን አባላት አለኝ ጉራም የጥቅም ትስስር ላይ የተመሠረተ ነው ለማለት ይቻላል:: የብሔር ተዋጽዖን ለማመጣጠን መሞከር አገሪቱ ከምትከተለው የብሔር ፌደራሊዝም መርሆ አንጻር ተቀባይነት ያለው ቢሆንም የፖለቲካ ታማኝነትን እንደዋና መስፈርት መውሰዱ ግን ፖለቲካዊ ሙስና ነው::

አሠራሩ ከገዢው ፓርቲ የተለየ የፖለቲካ አስተሳሰብ ያላቸውንና ገለልተኛ ሆነው ለመሥራት የሚፈልጉ ዜጎች እንዲገለሉ አድርጓል:: በፖለቲካና በመንግሥት ሥራ መካከል ግልጽ ድንበር ባለመበጀቱም ሲቪል ሰርቪሱ በገዢው ፓርቲ አባላት፣ ደጋፊዎችና ጥቅም ፈላጊ አስመሳዮች እንዲሞላ ሆኗል:: ለብልሹ አስተዳደርና ሥር ለሰደደ ሙስና እንዲጋለጥ በማድረግ አገር ላይ ኪሳራ አድርሷል::

### ሙስናን በግለ ሂስ የማለፍ ፖለቲካዊ አካሄድ እና የሕግ የበላይነት

ሕወሓት በትጥቅ ትግል ወቅት ጥብቅ የግምገማ ባሕል እንደነበረው ይታወቃል:: ሂደቱ ከዴሞክራሲያዊነትና ከሰብአዊ መብት አንጻር ጥያቄ ሊቀርብበት ቢችልም በርካታ የዲሲፕሊንና ሌሎች ግድፈቶች በማረም በኩል ጉልህ ሚና እንደነበረው ብዙዎች ይመሰክራሉ:: የዛሬን አያድርገውና አንድ ታጋይ የገበሬ ሚስት አሸኮርምመሃል በሚል እንኳን እርምጃ ይወሰድበት እንደነበር ይጠቀሳል:: ይህ ጥብቅ የአባላት ዲሲፕሊን ትግሉ በሚካሄድበት አከባቢ ያሉትን ሕዝቦች ሰፊ ድጋፍ በማስገኘት ድርጅቱ ለድል እንዲበቃ የጎላ አስተዋጽዖ እንደነበረው ነው የሚነገረው:: ሆኖም ድርጅቱ መንግሥት ከሆነ በኋላ የሚያደርጋቸው ግምገማዎች ሕግን የሚጥሱበት አጋጣሚዎች ስላሉ በብዙዎች ይተቻል:: ኢሕአዴግ ደጋፊዎቹንና አባላቱን ሙስና ፈጽመው ሲገኙ በሕጉ መሠረት ጉዳያቸው ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ቀርቦ እንዲታይ ከማድረግ ይልቅ በግለ ሂስ እንዲታለፉ ወይም የዲሲፕሊን እርምጃ በመውሰድ ብቻ እንዲታለፉ የሚያደርግባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው:: እንደሚታወቀው ድርጅቱ የፓርቲ ሥራውን በከፍተኛ ሚስጥራዊነት የሚሠራ ቢሆንም በአንዳንድ አጋጣሚዎች ሁኔታው ፍንትው ብሎ ታይቷል:: አቶ ገብሩ አሥራት ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ላይ ሕወሓት ሥልጣን በያዘ ማግስት ከፍተኛ አመራሮቹ ከተለመደው ሶሻሊስታዊ የአኗኗር ዘይቤ በተለየ የተንደላቀቀ ኑሮ በመጀመራቸውና ሙስናም እየተለመደ መምጣቱን ተከትሎ ዝቅተኛው ካድሬ ቅሬታ በማቅረቡ፣ ጉዳዩ በ1985 ዓ.ም. ለሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ በቀረበበት ወቅት ችግሩ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መኖሩ የታመነ ቢሆንም ድርጅቱ አደጋ ላይ ይወድቃል በሚል ምክንያት በከፍተኛ አመራሩ ላይ እርምጃ እንዳልተወሰደ፣ ይልቁንም የታችኛው ካድሬ ላቀረበው ቅሬታ ፖለቲካዊ ትርጉም በመስጠት እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑን በጸጸት እንደሚያስታውሱት ገልጸዋል::

የምርጫ ቦርድ ሊቀመንበር የነበሩት አቶ አሰፋ ብሩ በሙስና ተጠርጥረው ከተያዙ በኋላ ግለ ሂስ አውርደዋል በሚል በፖለቲካዊ ድርድር የተለቀቁበት አጋጣሚ በይፋ የተከወነ ነው:: በ2001 ዓ.ም. ኢሕአዴግ ባደረገው ግምገማ ላይ በርካታ ባለሥልጣናት አላግባብ መሬትና ሌሎች ንብረቶችን መውሰዳቸውን አምነው በሕግ ሳይጠየቁ በድርጅታዊ እርምጃ ብቻ መታለፋቸው ይታወሳል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም በቅርቡ ከንግዱ ማኅበረሰብ ጋር ባደረጉት ስብሰባ ላይ "ወደ እስር ቤት የሚያስገባ" ተግባር የፈፀሙ የሪል እስቴት አልሚዎች ቢኖሩም "እስር ቤቱን ላለማጣበብ" ተደራድረው ያለፉበት ሁኔታ መኖሩን ጠቅሰዋል:: የሥርዓቱ መሠረታዊ ችግር የፀረ ሙስና ትግሉን እንኳን የፓርቲ ጉዳይ አድርጎ መመልከቱ ነው:: የሚዘረፈው ሀብት የሕዝብ እንጂ የፓርቲው አይደለም:: የሕዝብ ሀብት የዘረፈ ደግሞ የሚጠየቅበት የሕግ ሥርዓት ዘርግተናል ተብሏል:: ታድያ አንዱን ተራ ሰበብ እየፈለጉ ማሰር እና ሌላውን እሹሩሩ ከማለት የባሰ በዜጎች መካከል ልዩነት ማድረግና የሕግ የበላይነትን መናድ አለ?

በቅርቡ የታሰሩት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ዓለማየሁ ጉጆ "ጉዳዩ በፖለቲካዊ መግባባት ቢፈታ ጥሩ ነው" በማለት በፍርድ ቤት የተናገሩትም ይህንኑ የመንግሥት የአሠራር ባሕል ታሳቢ ያደረገ ነው ለማለት ይቻላል:: ኢሕአዴግ የሚመራው መንግሥት የፖለቲካ ባሕል ሲቪል ሰርቪሱ የመልካም አስተዳደር ጉድለትና የሙስና መፈልፈያ እንዲሆን አድርጓል:: መንግሥት ሕጋዊነትን በአደባባይ በመጣስ የሕግ የበላይነትን ንዷል:: የፀረ ሙስና ትግሉ እንዲዳከም አድርጓል:: በዜጎች መካከል በተለይም የድርጅት አባል በሆኑና ባልሆኑ መካከል ልዩነት እንዲፈጠርም አድርጓል:: የሥርዓቱ አራማጆና ደጋፊዎች ሳይቀር ኢሕአዴግ በጥቅም ፈላጊዎችና አስመሳዮች በመሞላቱ የውደቀቱ ዋነኛ ጠንቅም ከዚህ ጋር እንደሚያያዝ ይገልጻሉ::

## "ትላልቅ ሙሰኞች" እና "የፀረ ሙስና ትግሉ" ፈተናዎች

ሙስና አቶ መለስ ለጥቅም ተጠጉን ያሏቸው "ዝንቦች" ብቻ ሳይሆን የብርቱ ታጋዮችም ጉልበት የተፈተነበት ጉዳይ ነው:: የደርግ ወታደር መሣርያ አፈሙዝ ያልበገረውን የታጋዮች ልብ አፍረክርኮ በጓደኞቻቸው መስዋዕትነትና አደራ ላይ ተረማምደው ከዚህ ደሃ ሕዝብ በተዘረፈ ገንዘብ የአሜሪካና አውሮፓ ቱጃሮችን ጭምር የሚያስቀና ኑሮ ለመኖር ያስቻላቸው መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነዉ:: በኢትዮጵያ የሙስና ሁኔታ ላይ የተለያዩ ተቋማት በተለያየ ጊዜ ጥናት በማድረግ ውጤቱን ይፋ አድርገዋል:: ጠቅለል ተደርጎ ሲታይም ሪፖርቶቹ በአገሪቱ ያለው ሙስና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን፣ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነጻጸርም ከፍተኛ ሊባል የሚችል መሆኑን እና ሕዝቡ ለተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ያለው አመለካከት ጥሩ እንዳልሆነ ያሳያሉ:: መንግሥትም ሪፖርቶቹ የተጋነኑና እየተመዘገበ ያለውን ለማጠልሸት የቀረቡ መሆናቸውን በመጥቀስ የሚሞግት ቢሆንም ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት መስፋፋቱንና በጊዜው ካልተቀጨ ልማቱን ሊቀለብስ የሚችል መሆኑን በተደጋጋሚ ከመግለጽ ተቆጥቦ አያውቅም:: አቶ መለስ በሕይወት በነበሩበት ወቅት መንግሥት በሙስና አንድ እጁ የታሰረ መሆኑን እስከመግለጽ ደርሰው ነበር:: ኢሕአዴግ በ2008 ዓ.ም. በባሕር ዳር ባደረገው ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ ከፍተኛ አመራሩ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት ውስጥ እጁ ያለበት መሆኑ ተገልጿል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ከከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር ባደረጉት አንድ የውይይት መድረክ ላይ አንዳንድ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የሙስና ኔትዎርክ ውስጥ እንዳሉበት መናገራቸውም ይታወሳል::

መንግሥት በቅርቡ ከ50 የሚበልጡ ባለሥልጣናትን፣ ነጋዴዎችንና ደላሎችን በሙስና ወንጀል በቁጥጥር ሥር ማዋሉን ለሕዝብ ይፋ ካደረገበት ጊዜ አንስቶ በጥናት ላይ የተመሠረተ መጠነ ሰፊ የፀረ ሙስና ዘመቻ በማድረግ ሙስናን ለመዋጋት ቆርጦ መነሳቱን እየገለጸ ይገኛል:: ከእንግዲህ በየትኛውም የሥልጣን ደረጃ የሚገኝ ባለሥልጣን ሙስና ለመፈፀሙ ማስረጃ ከተገኘበት ተጠያቂ የሚሆን መሆኑንንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል:: ሆኖም በአገራችን ያለው የሙስና ሁኔታ ከሥርዓቱ የፖለቲካ ህልውና ጋር የተሳሰረና ሥር የሰደደ ችግር በመሆኑ መሠረታዊ ፖለቲካዊ ለውጥ በማምጣት እንጂ በዘመቻ የተወሰኑ ባለሥልጣናትን በማሰር ይፈታል ማለት አይቻልም:: መንግሥት የወሰደውን የእስር እርምጃ ዋነኛ ሙሰኛ የሆኑ ትላልቅ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ያልነካ በመሆኑ የሕዝቡን ተቃውሞ ለማርገብና ትኩረት ለማስቀየር የተደረገ የተለመደ ድራማ ነው እየተባለ ከየአቅጣጫው ትችት እንደሚቀርብ ይታወቃል::

እርምጃውን አስመልክቶ ጠቅላይ አቃቤ ሕጉ አቶ ጌታቸው አምባዬ ሐምሌ 22 ቀን 2009 ዓ.ም. ላይ መግለጫ በሰጡበት ወቅት ከፍተኛ አመራሩ ለምን በሕግ ተጠያቂ እንደማይሆን ማብራሪያ እንዲሰጡ ተጠይቀው መልስ በሰጡበት ወቅት "የመንግሥት ኃላፊነት ደረጃ ላይ ከፍተኛ የመወሰን ድርሻ ያለው በዳይሬክተርነት ደረጃ ያለው ኃይል ነው::"፤ "የመንግሥት ሀብትና ገንዘብ በስፋት የማንቀሳቀስና የማሰማራት ኃላፊነት የተሰጠው ኃይል በዳይሬክተርነት ደረጃ ያለው ኃይል ነው:: ጉዳዮችን የሚያመቻቸውና የሚፈጽመው ይኼ ኃይል ነው:: ይህ ኃይል በሚያቀርባቸው የውሳኔ ሐሳቦችና ሙያዊ አስተያየቶች ላይ ተመሥርቶ ሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትር ዴኤታው ሊወስን ይችላል::" በማለት ያነሷቸው ሐሳቦች በብዙዎች ዘንድ አልተወደደላቸውም:: የመንግሥት ደጋፊዎች ጭምር የሕግና ሌሎች ጥያቄዎች ያነሱበት ሲሆን ያስከፋ ሲሆን መንግሥት ትላልቅ ባለሥልጣናትን ለመያዝ ፍላጎት የሌለው ለመሆኑ ማሳያ ተደርጎ ተወስዷል::

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያግዙ አሠራሮች አንዱ የተሿሚዎችን ሀብትና ንብረት መዝግቦ መያዝና ለሕዝብ ይፋ ማድረግ፣ ከሀብትና ገቢያቸው ጋር ያልተመጣጠነ ንብረት እንዳላቸው ሲታወቅ ተጠያቂ የሚደረጉበትን የሕግ ማዕቀፍና አሠራር መዘርጋት ነው:: ለዚህ እንዲረዳም ተሻሽሎ በወጣው የወንጀል ሕግ ምንጩ ያልታወቀን ሀብት ይዞ መገኘት በሙስና ወንጀል የሚያስጠይቅ ተግባር ሆኗል:: የባለሥልጣናትና ቤተሰቦቻቸውን ንብረት መዝግቦ በማጣራት ውጤቱን ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ የሚያስችል ሕግም ወጥቷል:: ሆኖም ተመዘገበ የተባለው የባለሥልጣናትና የመንግሥት ሠራተኞች ሀብት ቃል በተገባው መሠረት ለሕዝብ ክፍት/ይፋ አልሆነም:: መንግሥት በተደጋጋሚ ሕዝቡ ማስረጃ

ወደሚቀጥለው ገጽ

እንዲያቀርብ፣ የትኛውም ባለሥልጣን ሙስና ውስጥ መኖሩ ከተረጋገጠ ተጠያቂ አደርጋለሁ እያለ ነው:: ሕዝቡ ደግሞ ባለሥልጣናቱ በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው፣ ካስፈለገም በቅምጦቻቸው ስም ያላቸውን ንብረት ስለማውቅ፣ ያስመዘገቡት ንብረት ግልጽ ይደረግና ልዩነቱ ይታወቃል እያለ ነው:: መንግሥት ግን የተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶችን በማቅረብ በእምቢታው ቀጥሎበታል:: መንግሥት ሙስናን ለመታገል ቆርጬ ተነስቻለው እያለ በነበረበት በቅርቡ እንኳን ለኮሚሽኑ የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቡድን አስተባባሪ አቶ ብሩክ ነጋሽ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ስለጉዳዩ ጥያቄ አቅርቦላቸው "መረጃውን በጽሑፍ ለሚጠይቅ እየተሰጠ ነው:: በዘንድሮው ዓመት ብቻ 78 መረጃዎች ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ ፖሊስና ሌሎች አካላት ጠይቀው ወስደዋል:: ይፋ መደረግ አለበት የሚለውን ግን ኮሚሽነሮቹ በተደጋጋሚ ከሰጡት መግለጫ የተለወጠ ነገር ስለሌለ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ::" ማለታቸውን ጠቅሶ ጽፏል:: ይህም ጉዳዩን ይፋ ለማድረግ መንግሥት ፍላጎት የሌለው መሆኑን ያሳያል:: ከዚህም በመነሳት ሕዝቡ ትላልቅ ባለሥልጣናት ተጠያነትን ለመከላከል ያደረጉት ነው የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርስና መንግሥት እያደረገ ያለው የፀረ ሙስና ትግል ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበት አድርጓል ለማለት ይቻላል::

ትላልቅ ባለሥልጣናት ተጠያቂነትን ለማስቀረት የፀረ ሙስና መታገያ የፍትሕ ተቋማትን የማሽመድመድ እና በሙስና ያገኙትን ሀብት የአገሪቱ ሕግ የማይደርስበት የውጭ ባንኮች የማስቀመጥ ድርጊት ውስጥ እንደሚገቡ ጥናቶች ያሳያሉ:: ለመስማት የሚዘገንን የገንዘብ መጠን ከዚህ ደሃ ሕዝብ ተዘርፎ ወደውጭ እንደተሰደደ በበርካታ ሪፖርቶች ይፋ መሆኑ ይታወቃል:: በዚህም የተነሳ የፀረ ሙስና ትግሉ የተወሳሰበና ዓለም አቀፍ ገጽታን የተላበሰ እንዲሆን አድርጓል:: የሌሎች አገሮችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ድጋፍ ታክሎበት ሰፊ ሕዝባዊ ንቅናቄ ካልተደረገ በስተቀር የተዘረፈን ንብረት ለማስመለስ አስቸጋሪ ይሆናል:: የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበሩት አቶ አሊ ሱለይማን የተለያዩ ተቋማት ይፋ ያደረጓቸው አለአግባብ ወደውጭ የወጡ ገንዘቦችን በተመለከተ ስለተወሰደ እርምጃ ከአንዴም ሁለቴ ተጠይቀው እሱን ነገር አታንሱት ውስብስብ ነው የሚል ከእርሳቸው የማይጠበቅ ምላሽ መስጠታው ይታወሳል:: በርካቶችም መልሳቸውን ትላልቅ ባለሥልጣናትን ተጠያቂ ለማድረግ ኮሚሽኑ ፍራቻ ያለው ለመሆኑ በማሳያነት ያቀርቡታል:: ኮሚሽኑ በሕግ ደረጀ ነጻ ነው ቢባልም የሙስና ወንጀልን ከመመርመር ከመክሰስ ጋር በተያያዘ ከጣልቃ ገብነት ነጻ አለመሆኑን በርካታ ጥናቶች ያረጋግጣሉ:: የምርመራና የክስ ሂደቶችን በአንድ ተቋም ሥር ለማሰባሰብ በሚል ሰበብ የሙስና ወንጀል የምርመራና የክስ ሥራ ከኮሚሽኑ ተነጥቆ ለጠቅላይ አቃቤ ሕግ እና ለፖሊስ መሰጠቱና በቅርቡም ኮሚሽነሩ በአምባሳደርነት ስም ገለል እንዲሉ መደረጉም የፀረ ሙስና ትግሉን የበለጠ ለማዳከም የተወሰደ እርምጃ አድርገው የሚቆጥሩ አሉ::

## ጥይት እና ስኳር

ጠንካራ የሲቪል መንግሥት በሌለበት ሁኔታ መከላከያው በሰፊው ወደ ኢኮኖሚው መግባቱ የፀረ ሙስና ትግሉን ከባድ የሚያደርገው መሆኑ አከራካሪ አይደለም:: የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ አገሪቱን ወደልማታዊ መንግሥት የዕድገት አቅጣጫ ከመሯት በኋላ የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማሳካት ተስፋ የተጣለባቸው ትላልቅ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በብድር በተገኘ ገንዘብ ጭምር ግዙፍ ካፒታል ተመድቦላቸው መቋቋማቸው ይታወቃል:: መከላከያውም ወደኢኮኖሚው ውስጥ በሰፊው እንዲገባ የተደረገ ሲሆን ግዙፍ ፕሮጀክቶችን የሚያንቀሳቅስ መሆኑ ይታወቃል:: የአገር መከላከያ ሠራዊት በቴክኖሎጂ እና በአቅም መጠናከሩ የሚደገፍ ቢሆንም የግል የንግድ ተቋማት ሊሠሩት በሚችሉት የሲቪል ሥራዎች ላይ በስፋት መሰማራቱ ግን በሂደት ችግር ሊፈጥር የሚችል በመሆኑ በርካታ ሰዎች አስተያየታቸውን ሲሰጡበት ቆይተዋል:: ለምሳሌ የዚህ መጽሔት አምደኛ እና የሕግ ጠበቃ የሆኑት አቶ ሄኖክ አክሊሉ ዕንቁ መጽሔት ላይ "ጥይት ከስኳር ይለይ!" በሚል ርዕስ በጻፉት መጣጥፍ ላይ መከላከያው በሂደት በኢኮኖሚው ውስጥ ገኖ ከወጣ የከፍተኛ ወታደራዊ ኦፊሰሮች የግል ተጠቃሚነትንና ጥቅምን ለማስጠበቅ የሚደረግ ትግልን ከመፍጠር አልፎ፣ ከሲቪል አስተዳደሩ ቁጥጥር ሥር በመውጣት በአገሪቱ ላይ የከፋ ችግር ሊያደርስ የሚችል መሆኑን የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በማሳያነት በማቅብ ስጋታቸውን ገልጸዋል::


የመከላከያው ግዙፍ ኩባንያዎች በተቋቋሙበት ወቅት በአቶ መለስ ብርቱ ክንድ ሥር ስለነበሩ ያን ያህል ስጋት አልነበረም ለማለት ይቻላል:: አቶ መለስ ሙስናን እንደፖለቲካ መሣርያ ይጠቀሙ የነበረ መሆኑ ባይካድም በባለሥልጣናቱና በወታደሩ ዘንድ ለአምልኮ የተጠጋ ተፈሪነት ስላላቸው እንዳሁኑ ተጠያቂነት የሌለበት ዝርፊያ ላይካሄድ ይችል ነበር ለማለት ይቻላል:: እርሳቸውን የተኩት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የፖለቲካ ብቃታቸውና ተሰሚነታቸው ላይ በርካቶች ጥርጣሬ የነበራቸው ቢሆንም ከሙስና የጸዱ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን በሂደት ኃይል አሰባስበው ሙስናን ይዋጋሉ በሚል ተስፋ ጥለውባቸው ነበር:: ሆኖም ሁኔታዎች እንደሚያሳዩት ሰውየው ከሥልጣናቸው ጋር የሚመጣጠን ተፈሪነት የላቸውም:: ከአቶ መለስ የተጠጋጋ ተፈሪነት ያለው ሌላ የሲቪል ኃይል አለ ለማለትም አይቻልም:: ይህም የስጋቱን እውነትነት ሳያፋጥነው አልቀረም:: መከላከያው ከሚገነባቸው ፕሮጀክቶቹ መጓተት ጋር በተያያዘ በነበሩ ውዝግቦች የስኳር ኮርፖሬሽኑ ባለሥልጣናት ከመከላከያው ጋር የነበረው የሥራ ግንኙነት በውል መሠረት እንደማይገዛና ጫና እንደሚያሳድርባቸው ማሳወቃቸው በመገናኛ ብዙሃን ይፋ መሆኑ ይታወሳል:: በተቋሙ ውስጥ ለሙስና በር የሚከፍቱ የአሠራር ግድፈቶች እንዳሉ በዋና ኦዲተር ሪፖርቶች በተደጋጋሚ ሲገለጽና የማስተካከያ ምክር ሐሳብ ሲሰጥ ቢቆይም እስካሁን እርምጃ ለመውሰድ የደፈረ አካል አለመኖሩም ይህንኑ ይጠቁማል:: ይህም መንግሥት እያደረኩ ነው በሚለው የፀረ ሙስና ትግል ስኬትና ተቀባይነት ላይ የጎላ ተጽዕኖ አለው ለማለት ይቻላል::

## ሕዝብን ያገለለ "የፀረ ሙስና ትግል" የት ያደርሳል?

መንግሥት በተለያየ ጊዜ ለፀረ ሙስና ትግሉ ወሳኝ መሆኑን በመግለጽ ሕዝቡ እንዲሳተፍ ጥሪ ከማቅረብ ቦዝኖ አያውቅም:: ነገር ግን ጉዳዩን በትኩረት የሚከታተሉ አካላት ጥሪው አፋዊ ከመሆን ባለፈ ሕዝቡን ለማሳተፍ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መንግሥት አልፈጠረም በማለት ይተቻሉ:: ተቺዎቹ ሲያስረዱ ሕዝቡ ተገቢውን ተሳትፎ ለማደረግ የሚችለው ነጻ የሲቪክና የሚዲያ ተቋማት ሊኖሩ ይገባል:: አገሪቱ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ እና አሕጉር አቀፍ ኮኒቬንሽኖች ላይ መንግሥት በሙስና ትግሉ ሂደት እነዚህን ተቋማት ለማሳተፍ ቃል ቢገባም በተጨባጭ ያለው እውነታ ሲታይ ግን ኮሚሽኑ ተቋማቱ ገለልተኛ አይደሉም፤ ፖለቲካዊ ተልዕኮ አለው የሚሉ ተገቢነት የሌላቸው ምክንያቶችን በመደርደር በርካቶችን ከተሳትፎ ሲያገል የነበረ ሲሆን፣ ምርጫ ዘጠና ሰባትን ተከትሎ በወጡ አፋኝ ሕጎችና አሠራሮች ጭራሽ ህልውናቸው እንዲከስም ተደርጓል በማለት ይሞግታሉ::

መንግሥት በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ላይም ዜጎች በመንግሥት አሠራር ላይ የሚያቀርቡት ተቃውሞ በቀናነት ተቀብሎ በምክንያትና ማስረጃ የተደገፈ መልስ ከመስጠት ይልቅ ልዩ "አጀንዳ አለህ"፤ "ፀረ ልማት ነህ" የሚሉና ሌሎች ውንጀላዎችን በመጠቀም ለመሸማቀቅ ጥረት ሲደረግ ማየት የተለመደ ነው:: ታች ያሉ የቀበሌ አመራሮች ሳይቀር ሙስናን ለመሸፈንና ሕዝብን ለማግለል የተጠቀሙበት መሆኑን ሁኔታዎች ያሳያሉ:: ከላይ እንደተገለጸው የባለሥልጣናት ሀብት ምዝገባ ይፋ አለመሆን ሲደመርበት ሕዝቡ በሙስና ትግሉ ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበትና መንግሥት ሙሰኛ ባለሥልጣናትን እየተከላከለ ነው የሚል ግንዛቤ እንዲይዝ ሆኗል:: የፖለቲካ ሥርዓቱ ተቀባይነት ላይም ጥያቄ የሚያስነሳ ነው ለማለት ይቻላል::

*ተሾመ ተስፋዬ በኢሚይል አድራሻው makoman93@gmail.com ይገኛሉ።*



ጌታቸው ሽፈራው

# ቂሊንጦ ለምን ተቃጠለ?

የሰው ልጅ በወደፊት ሕይወቱ ላይ ተስፋ ሲያጣ እና በደል ሲበዛበት ነፍሱን የሚያስከፍለው እንኳ ቢሆን ከማመፅ ወደኋላ አይልም:: በመገዛቱ ቂም ሲያካብት፣ ጥላቻ ሲያዳብር ደግሞ እርምጃው የከፋ ይሆናል:: መኖርያውን ብቻ ሳይሆን እራሱን ያቃጥላል:: ቂሊንጦም የተከሰተው ይኸው ነው:: ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የሰውን ልጅ እስረኛ ነው ተብሎ የሚነፈገው ነገር አልነበረም:: በቂሊንጦ እስር ቤት እነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶች ሳይቀር በተለያየ መንገድና ደረጃ ይከለከላሉ:: ምግብ ተብሎ ለእስረኛ የሚቀርበው አሳሪዎቹ ለኢትዮጵያውያን ያላቸውን የክብር ደረጃ የሚያሳይ ነው:: “ደያስ” ተብሎ የሚጠራው ለእስረኛው የሚቀርበው ምግብ ለሰው ይቀርባል ተብሎ ለማሰብ የሚከብድ ነው:: “ምግቡን” የቀመሰ ሰው ሠሪዎቹ እህልን የማበላሸት ብቃታቸውን ያደንቃል:: እንደሰው ለማይመለከቱት እስረኛ ምግብን እንዳይበላ አድርገው በመሥራት አዲስ ግኝት የፈጠሩ ይመስላሉ:: ኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም ድረስ የጨውን ያህል የረከሰ ነገር ባይኖርም ቢያንስ ጨው እህልን እንደሚያጣፍጥ ያውቃሉና ብናኝ ጨው እንኳ አይጨምሩበትም:: ቅባትማ የሚታሰብ ነገር አይደለም:: እስረኛው ከምግቡ ጣዕም የለሽነት ባሻገር የሚጨነቀው ለሽታው ነው:: እስረኛው ለምሳና ራት ተብሎ የሚታደለውን ወጥ የሚያስቀዳው አፍንጫውን ይዞ ነው:: ሰው ይበላዋል ተብሎ የተዘጋጀ ነገር ያን ያህል ለምን እንደሚሸት አይገባኝም::

ጨው መጨመር ያልፈለጉ ሰዎች እስረኛው ሌሊት እንዳያመልጥ የሚያደነዝዝላቸውን የእንቅልፍ ክኒን ግን በገፍ ይጨምሩበታል:: በዚህም ምክንያት ወጥ ተብዬው ላይ የሚታየው የቅመምና የቅባት ሳይሆን የላርጋቲን (የእንቅልፍ ክኒን) ለኸት ነው:: ከወጡ በተጨማሪ እንጀራው ከመኮምጠጡም በላይ አንጀት የሚያርድና ለብዙዎቹ የጨጓራ በሽታ መንስኤም ሆኗል:: የእስር ቤቱ አስተዳደሮች እስር ቤቱ የሚያቀርበውን ምግብ እንደ መቅጫ ዘዴ ስለሚያዩት ይመስላል ከቤተሰብ ምግብ ሲገባ ደስ አይላቸውም:: በፈለጉ ቀን ደግሞ የቤተሰብ ምግብን ይከለክላሉ:: የምግቡን መጠን ጭምር የመወሰን መብትን ለራሳቸው አቀዳጅተዋል:: ማን ከማን ጋር መብላት እንዳለበትና እንደሌለበት ጭምር ይወስናሉ:: ይህ በመጨረሻ ያመጣውን ጦስ የምናዬው ነው::

እስር ቤት ውስጥ ሌላኛው ትልቅ ችግር ማደሪያ (መጠለያ) ነው:: ሰው ጠባብ ግቢ ውስጥ ቀኑን አሳልፎ፣ የማይከፈትም ከሆነ ሲጫወት ውሎ ሌሊት ሁሉም እስረኛ ወደ ቤት ስለሚገባ ክፍሉ ይጨናነቃል፣ በእስረኛው ጋበን ቤቱ ይግላል:: ቀን ፖሊስ ሲያዳፋው የዋለውን እስረኛ ሌሊት ደግሞ ትኋንና ቅማል ይቀበለዋል:: ቂሊንጦ ቤቶች ቢበዛ እስከ 150 ካሬ ሜትር ቢሆኑ ነው:: በእነዚህ እስር ቤቶች ውስጥ ከ130-150 እስረኛ ያድርባቸዋል:: ከቃጠሎው በኋላ እስከ 170 ሰው ታጉሮባቸዋል:: እነዚህ ቤቶች ውስጥ ተደራራቢ አልጋ ያለ ቢሆንም በርካታ እስረኛ የሚተኛው መተላለፊያ ላይ ነው:: ከአልጋ መሃል ቦታ ሊያገኙ የሚችሉት ጓደኛ እና ገንዘብ ያላቸው ብቻ ናቸው:: መንገድ ላይ በቆሻሻ ፍራሽ ላይ ወድቀው የሚያደሩት እስረኞች አላፊ አግዳሚው ሲረግጣቸው አድሮ ቀን እቃቸውን ማስቀመጫ አያገኙም::

አንድ እስረኛ አልጋ እስኪያገኝ በዚህ ሁኔታ ለወራት ይቆያል:: ከእስር ቤቱ አስተዳደሮች ጋር በሆነ ባልሆነው ግጭት ውስጥ የገቡ እስረኞች ደግሞ ቤት ውስጥ አለኝ የሚሉትን ትልቁን ንብረት (አልጋቸውን) ተቀምተው መተላለፊያ (ደቦቃ) ላይ እንዲተኙ ይቀጣሉ:: ነገሩ ሲብስ ደግሞ ሌትም ቀንም ተዘግቶ ወደሚውለውና ምንም ዓይነት የፀሐይ ብርሃን ወደማያገኙበት ጨለማ ቤት ይላካሉ:: በቂሊንጦ እስር ቤት የተገኘ እስረኛ አገሩን ብቻ ሳይሆን በጠባብ ቤቱ ውስጥ የነበረውን አልጋ፣ ይህ ባይሆን እንኳ ሰላማዊ እንቅልፍ የሚተኛበትን ወለል ሁሉ የተቀማ የባይተዋሮች ባይተዋር ነው::

> የእስር ቤቱ አስተዳደሮች እስር ቤቱ የሚያቀርበውን ምግብ እንደ መቅጫ ዘዴ ስለሚያዩት ይመስላል ከቤተሰብ ምግብ ሲገባ ደስ አይላቸውም:: በፈለጉ ቀን ደግሞ የቤተሰብ ምግብን ይከለክላሉ

እስር ቤት የሚዘነጥበት ቦታ ባይሆንም እስረኛም እንደማንኛውም ሰው ልብስ ያስፈልገዋል:: እስከ 2008 ዓ.ም. ክረምት መግቢያ ድረስ ቂሊንጦ ውስጥ ማንም የፈለገውን መልበስ ይችል ነበር:: ሆኖም በኦሮሚያ የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ አመፅና በዚህ ሰበብ መንግሥት በዜጎች ላይ የሚፈፅመውን በደል እስረኞች ጥቁር በመልበስ መቃወም ሲጀምሩ እስረኞች ዩኒፎርም እንዲለብሱ የሚያስገድድ ህግ ተግባራዊ ሆነ:: እስረኞች ጥቁር ልብስ ለብሰው ወደ ፍርድ ቤት በሚሄዱበት ወቅት በእስር ቤቱ አስተዳደሮች ትዕዛዝ ልብሳቸውን ተቀምተው፣ ራቁታቸውን ወደ ማደሪያቸው እንዲመለሱ ተደርጓል:: ብዙዎቹ ተደብድበዋል:: ፍርድ ቤት አንቀርም ያሉት እነ አቶ በቀለ ገርባ በቁምጣ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት ተገደዋል:: ልብሳቸውን አናዎልቅም ያሉ ወጣቶች እጃቸውን በካቴና ታስረው ተደብድበዋል:: እነዚህ ወጣቶች እጃቸውን ታስረው እንዲያድሩ ስለተወሰነባቸው ይህን የተቃወሙት እነ ዮናታን ተስፋዬና ፍቅረ ማርያም አስማማውን ጨምሮ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች መዳረሻቸው የፀሐይ ብርሃን ወደ ሚከለከልበት ጨለማ ቤት ሆኗል:: እስረኛው አስቦ ለበሰውም አልለበሰው ጥቁር ልብስ ተቀምቶ ሳይመለስለት ቀርቷል:: ጥቁር ልብስ ለብሰሃል ተብለው ፍርድ ቤት እንዳይሄዱ ከተከለከሉት እስረኞች መካከል እኔም አንዱ ነኝ:: ሆኖም እስረኛው ከፍርድ ቤት ስለሚያስቀሩት፣ በካቴና ስለሚታሰር ወይንም ስለሚደበደብ ብቻ የአዘቦቱን የልብስ ምርጫ ሊቀበል አልቻለም::

የእስረኛውን የጥቁር ልብስ ተቃውሞ ለማብረድ ዩኒፎርም እንደ ዋነኛ አማራጭ ተወሰደ:: ከሕወሓት ባለሀብቶች ጋር ተዋውለው ጥራቱ እጅግ የወረደ፣ መካከለኛም፣ ትልቅም ተብሎ ሳይለይ ተመሳሳይ በተለይ ሱሪው ሰፋፊና ረገጃጅም ዩኒፎርም አስፍተው እስረኛውን በግድ ለማልበስ ሞከሩ:: ይህ አንድ ዩኒፎርም በ750 ብር ዋጋ የመጣ ነው ቢባልም ኮንትራቱን ከወሰዱት አንዱ ለቂሊንጦ በ175 ብር እንዳስረከበው በሙስና ለታሰረ ዘመዱ አረጋግጦለታል:: እስረኛው በወጉ ያልተሰፋውን ዩኒፎርም መርፌ ደብቆ አስገብቶ አጥብቦና አሳጥሮ ልብስ አስመስሎ በመስፋቱ ይደበደባል:: ያን በወጉ ያልተሰፋ ልብስ ካልለበሰ ቤተሰብ አታገኝም፣ ፍርድ ቤት መሄድ አትችልም ሲባል አማራጭ ሲያጣ መልበስ ነበረበት:: እየቀፈፈውም ቢሆን ልብሱን ለመልበስ ተገዷል::

ወደሚቀጥለው ገጽ ▶

ከዚህ ወጭ እስረኛ በሆነ ባልሆነው ይደበደባል፣ ጨለማ ቤት ይገባል:: የሕወሓትን ስም በክፉ ያነሳ በእስር ቤቱ አስተዳደሮች ጥርስ ውስጥ ይገባል:: እስረኛ የሰው ልጅ እንደሆነ አይታሰብም:: ገና የፍርድ ሂደቱን እየተከታተለ ለእነሱ ግን ፍርደኛ ነው:: በሽብር የተከሰሰው ሽብርተኛ ነው:: በነፍስ የተከሰሰው ነፍሰ ገዳይ ነው:: በስርቆት የተከሰሰው ሌባ ነው:: እነሱ ከፍርድ ቤት ቀድመው ይፈርዱበታል:: የፖለቲካ እስረኛ ገና ጥፋተኛ መሆን አለመሆኑ በፍርድ ቤት ሳይወሰን የትኛውም ዓይነት ገንዘብ የሚያስገኝ ሥራ ወይንም የአስተዳደር ቦታ ውስጥ እንዳይገባ ይከለከላል:: ነጻ ሲባል እንኳን አይለቁትም:: ለማዕከላዊ ደውለው መልዕክት ያስተላልፋሉ:: ያ አሸባሪ ነጻ ተብሏል ተረከበን ብለው:: ማዕከላዊ ተቀብሎ ደብድቦ፣ የሐሰት ምስክር አዘጋጅቶ ሌላ “የሽብር” ክስ ይመሰርታል::

ይህ ሁሉ በደል በተከመረበት ሌላ እሳት ጨመሩ:: ለመብላት ይቅርና ሽታው የሚያውከውን ምግብ ብቻ እንጅ የቤት ምግብ መመገብ እንደማይቻል የሚያትት የአዛዦቹ ሕግ ወጣ:: ማንኛውም እስረኛ ከቤተሰብ የመጣ ምግብ እንዳይገባለት ተከለከለ:: ከዛ በፊት የፖለቲካ ጥያቄ ሲነሳ፣ አገራዊ ጉዳይ በተመለከተ የረኀብና ሌሎች አድማዎች ሲደረጉ ብዙ እስረኞች አይሳተፉም ነበር:: የምግብ ጉዳይ ግን የሁሉም ጉዳይ ሆነ:: በሙስና የተጠረጠሩት ሳይቀሩ በእስር ቤቱ ሕግ ደስተኛ አልነበሩም:: በነፍስ፣ በውንብድና እና በመሰል ወንጀሎች የሚገቡና በተለምዶ “ዱርዬ” ተብለው የሚጠሩት እስረኞች በቤተሰቦቻቸው ከሚጠየቁት መካከል ናቸው:: እነዚህ እስረኞች ከእስር ቤቱ አስተዳደር ጋር የማይስማሙ ከመሆናቸውም በተጨማሪ እስረኛውን ለማሳደም ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው ናቸው::

ነሐሴ 26 ቀን 2008 ዓ.ም. ከቤተሰብ ምግብ እንዳይገባ የወጣው ማስታወቂያ ለነሐሴ 28 ቀን 2008 ዓ.ም. ተግባራዊ እንደሚሆን ይደነግጋል:: ይህ የእስር ቤቱ ውሳኔ ገና ማስታወቂያው የወጣ ቀን ዞን ሦስት የሚባለው የእስር ክፍል ላይ አድማ መጀመሩ ምንም አልመሰላቸውም:: በዚህ ወቅት ከእየእስረኛው ተመርጠው የዞን ወኪሎች የሆኑ እስረኞች የእስር ቤቱን ዋና አስተዳዳሪ ኮማንደር ተክላይን “ምግብ በመከልከሉ ምክንያት እስረኛው ተቆጥቷል:: በልብሱ ተማሯል:: ብዙ የሚያስመርሩ ነገሮች አሉ:: ይህኛው ሲጨመር ችግር ይከሰታል:: ቢያንስ እናወያየው” ብለው ጠይቀው ነበር:: የኮማንደር ተክላይ መልስ “እስረኛን እሽሩሩ አንልም” የሚል ነበር::

በአስተዳደሮቹ ግትርነት የተበሳጨው እስረኛ ቅዳሜ ማንም እስር ቤቱ የሚያድለውን ምግብ (ቁርስ) እንዳይበላ ተስማማ:: የቅዳሜውን የአድማ መንፈስ አርብ ማታ የተረዱት አዛዦች በማታው ቆጠራ እስረኛውን በዱላ ለማስፈራራት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀረ:: ጠዋት ቁርስ ሲመጣ ሻይ የያዘው ጎላና ዳቦ የያዘው ኬሻ ውጭ እንዲቀመጥ ተደረገ:: ለቆጠራ የመጡት ፖሊሶች ይህ ቁርሱ እንዲገባ ቢያዙም የሚሰማቸው አላገኙም:: አድማው የበረታ መሆኑን ሲያውቁ እስረኛው ከማደሪያው ወደ ካፌ፣ ሱቅ፣ ቤተ መጻሕፍትና ሌሎች አገልግሎት የሚያገኝባቸው ቦታዎች የሚሄድበትን የግቢውን በር ዘግተው ወጡ:: ሌላ ጊዜ ጠዋት ጠዋት ይህ በር አይዘጋም:: ትንሽ ቆይተው ራቅ ብለው እስረኛውን መከታተል ጀመሩ:: በርካታ መሠረታዊ መብቶቹን ተከልክሎ የምግብ ደረጃ የሌለውን የእስር ቤቱን “ሬሽን” ብቻ እንዲበላ ለተወሰነበት እስረኛ የብሶቱ ማንደጃ ሆነ:: የግቢው በር እንዲከፈት መጮህ ጀመረ:: የእስር ቤቱን አስተዳደሮችና ፖሊስን መውቀስ፣ መስደብ ቀጠለ:: ያን በግድ እንዲለብስ የተደረገውን ዩኒፎርም አውልቆ ሜዳ ላይ አቃጠለ:: የሚታየው በቴሊቪዥን ኢቲቪ ብቻ ነው:: በየትኛውም ወንጀል የገባ እስረኛ ይሁን ሌላ አማራጭ ስለሌለው በሚዲያው ይማረራል:: በዚህም ምክንያት ኢቲቪን ያገኘ ሲመስለው “እሱን ውሸታም አውርድ!” ብሎ ቴሌቪዥኑንም እሳት ውስጥ ከተተው:: የትኋንና የቅማል መናኸሪያ የሆነውና ደቦቃ ላይ የሚተኛበትን ቆሻሻ ፍራሽ እሳት ውስጥ ጨመረ:: ከዚህ በላይ ስሜታዊ የሆነ እስረኛ ቤት እስከመለኮስ ደረሰ::

እስረኛው የብሶቱን ያህል ማመፅ ሲጀምር ወዲያውኑ ፖሊስ ከየአቅጣጫው ወደ ጠባቦቹ ግቢዎች መትረየስ መተኮስ ጀመረ:: ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው ለማምለጥ የሞከሩ እስረኞች ለሞት ተዳረጉ:: በተለይ ዞን ሁለት የሚባለው እስር ቤት ብዙዎቹ የተመቱት ለማምለጥ ሲሞክሩ እንደሆነ አብረዋቸው የነበሩት ይመሰክራሉ::

የቂሊንጦ እስር ቤት አራት ማዕዘን ሆኖ ወደ ዞኑ የሚያስገባው በር ጠባቦች ናቸው:: ፖሊስ ከእነዚህ በሮች ትይዩ ሆኖ እስረኛው ወዳለበት ሜዳ እሩምታ ተኩሷል:: በርካታ የጭስ ቦንቦች ተወርውረዋል:: ውስጥ እስረኛው ሲያቃጥላቸው ከነበሩት ቁሳቁሶች ጋር ሲዳመሩ እስር ቤቱ ስለጨለመ እስረኛ ወደ የት እንደሚሄድ እንኳ አያውቅም:: በዚህ እሩምታ መካከል በርካቶች ተመትተዋል:: በዚህ ሩምታ ምክንያት እስረኞቹ ተደግፈዋቸው የነበሩት የቤቱ ግድግዳዎች በጥይት ተበሳስተዋል፣ አግዳሚ ብረቶች በጥይት ተመትተዋል:: ይህ አሁንም በማስረጃነት ያለ ምልክት ነው:: በርካቶች ቆስለው፣ እስረኞች ተደግፈዋቸው የነበሩት ግድግዳዎች አሁንም ድረስ ተበሳስተው እየታዩ የሞቱትን እስረኞች እሳት እንደበላቸው አድርገው አቅርበዋል:: በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ዞን ሁለት በቤተሰብ መጠየቂያው በኩል ለማምለጥ፣ እንዲሁም ሜዳ ላይ በሩምታ የተገደሉትን እስረኞች እስረኛ ያቃጠላቸው ለማስመሰል በጥይት የደበደቡትን አስከሬን አንስተው እሳት ውስጥ መጨመራቸው ነው:: እስረኞች በጥይት በመደብደባቸው ደማቸው ሜዳ ላይ ፈሷል:: በዛ ሰሞን ወደ ሸዋ ሮቢት እና ዘዋይ እስር ቤት የተጓዙ እስረኞች እንነገሩን ደሙን ለመሸፈን ተብሎ ሜዳው አዲስ አፈር ለብሶ ነበር:: ይሁንና መጋቢት ላይ ዝናብ ሲዘንብና ይህ ጊዜያዊ አፈር ሲታጠብ የፈሰሰው ደምና እሳት ላይ የተጣለው የሰው ልጅ ገላ የተጣበቀበት ሜዳ ተጋልጦ ነበር::

የእስር ቤቱ አስተዳደሮች ጥፋታቸውን ለመሸፈን የሞቱትን ሰዎች እስረኛ እንደገደላቸው አድርገው ሲያወሩ ከርመዋል:: እነ ሰጠኝ ሙሉ፣ ነጻነት አበበ፣ ተሻለ በቀለና ሌሎችም በቤተሰብ መጠየቂያው በኩል (ተቃጥለው ከተገኙበት ግቢ ውጭ) እንደተመቱ ከጎናቸው የነበሩት የሚመሰክሩት ሐቅ ነው:: ሆኖም የእስር ቤቱን አስተዳደር ተጠያቂ ላለማድረግ ሲባል ከዚህ በፊት ከፖሊስ ጋር የማይስማሙ እስረኞችን ሸዋ ሮቢት ወስደው በመደብደብ የገደልናቸው እኛ ነን እንዲሉ አስገድደዋቸዋል:: መንግሥት ያቋቋመው የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እንኳ ሩምታ ተኩስ ተተኩሶ እንደነበር ለፓርላማ ባቀረበው ሪፖርቱ መግለጹ ሟቾቹ በጥይት እንደተገደሉ ማስተባበል እንደማይቻል ያሳየ ነው::

ከቃጠሎው በኋላ እነዚህ የዞን ኃላፊዎች በቃጠሎው ሰበብ እስረኞችን ሲመረምሩ ለነበሩት ደኅንነቶች የቃጠሎው ዋነኛ ምክንያት እነ ተክላይ እንደሆኑ በግልፅ ተናግረው ነበር:: እስረኞቹ “ለዚህ ሁሉ የዳረጉን፣ ለበርካቶች መሞት ምክንያት የሆኑት እነ ተክላይ ናቸው::” ብለው ተናግረዋል:: ከኮሚቴዎቹ መካከል አበበ አንዱ ነው:: ዞን አንድ ውስጥ 18 በላይ የጪስ ቦንቦች ሲወረወሩ እሱም ታፍኖ ከሞት ነው የተረፈው:: አበበ ለደኅንነቶቹ “ተጠያቂው ማንም አይደለም:: የእስር ቤቱ አስተዳደሮች ውጭ ሊጠየቅ የሚገባው ሰው የለም:: ነግረናቸው ነበር:: ለዚህ ሁሉ መከራ የዳረጉንን እነ ተክላይን ክሰሷቸውና እኔ የመጀመሪያው ምስክር እሆናለሁ:: እኔኮ እነሱ ባመጡት ጦስ ሞቼ ነበር” ብሎ በግልፅ ሲነግራቸው የእስር ቤቱን አመራሮች እንደሚያስሩ ቃል ገብተው ነበር:: በእርግጥም የእስር ቤቱ አመራሮች የችግሩ መንስኤ እንደሆኑ ታምኗል:: ግን አልታሰሩም፤ አልተከሰሱም:: ቅጣቱ ከቂሊንጦ ወደ ዝዋይ ማዘወር ብቻ ነበር::

የእስር ቤቱ አመራሮች እስረኛውን መሠረታዊ ፍላጎት ነፍገው፣ መሠረታዊ መብቱን ጥሰው በምሬት እስር ቤቱ እንዲቃጠል ሲያደርጉ የተደበደቡትና የተከሰሱት ከማንም ጋር መገናኘት የማይቻልበት ጨለማ ቤት የነበሩት እነ ማስረሻ ሰጤ፣ አበበ ኡርጌሳ … በወቅቱ ቂሊንጦ ግቢ ውስጥ እንኳን ያልነበሩት የግፍ እስረኛው ዶክተር ፍቅሩ ማሩ፣ ለወራት ያህል ጨለማ ቤት፣ ከዛም ተፈርዶበት ዝዋይ የነበረው ፍቅረ ማርያም አስማማው፣ በቃጠሎው ወቅት ከቤታቸው ያልተነቃነቁት እነ አግባው ሰጠኝ፣ ከበደ ጨመዳ እና ሌሎችም ንጹሐን ናቸው:: እነዚህ ንጹሐን ያልነበሩበትን አድርገናል ብለው እንዲያምኑ፣ የእስር ቤቱ አስተዳደሮች ለፈፀሙት እነሱ እንዲቀጡ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን መርማሪዎች ሸዋ ሮቢት ወስደው ጭካኔ ፈፅመውባቸዋል:: ተሰቅለዋል:: ተገርፈዋል:: ተከሰዋል:: ሸዋ ሮቢት የደረሰባቸውን በደል ፍርድ ቤት ሲናገሩ የችሎቱ ታዳሚ አንብቷል::



ብርሃኑ አበጋዝ (ዶ/ር)

# እውነትም መጪው ዘመን የኢትዮጵያ ከፍታ ነው!

ለበርካታ ዓመታት ስለዴሞክራታይዜሽንና ዴሞክራሲ አንብቤያለሁ፤ አስተምሬያለሁም:: በእነዚህ ሁለት ጽንሰ ሐሳቦች ላይ ያለኝን ግንዛቤ መሠረት አድርጌ የአገሬን ሁኔታ ስገመግመው ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ ይታየኛል:: ከጓደኞቼና የሥራ ባልደረቦቼ ጋር ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ አንስተን ስንጨዋወት በሚበዙት ጓደኞቼና ባልደረቦቼ ላይ የማየው ስሜት ግን ከእኔ ስሜት በእጅጉ የተለየ ነው:: ለመሆኑ ብዙ ሰዎች ኢትዮጵያ መስቀለኛ መንገድ ላይ ናት በሚሉበት በአሁኑ ሰዓት የእኔ ተስፋ ሰጪ ሁኔታ አለ ማለት ከምን የመነጨ ነው? የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ብሩኅና ተስፋ የሚሰጥ ነው ከምልባቸው መሠረታዊ ነጥቦች ውስጥ ሦስቱን ብቻ በመግለጽ አቋሜን ለማስረዳት ልሞክር::

ከሁሉ አስቀድሞ ትልቅ የተስፋ ምንጭ ነው የምለው የወጣቶቻችን የፖለቲካ ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩን ነው:: ሚሊኒያል (millennial) እየተባለ የሚጠራው ትውልድ አባላት የሆኑት የአገራችን ወጣቶች የዓለም የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ግስጋሴ የሰጣቸውን መልካም ዕድል በሚያስደንቅ ሁኔታ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ:: ወጣቶቻችን ማኅበራዊ መዲያውን እየተጠቀሙ በወሳኝ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ፤ ይከራከራሉ፤ ተቃውሟቸውን ይገልጻሉ:: በማኅበራዊ ሚዲያው የተጠሩ ተቃውሞዎች በመንግሥት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በመፍጠራቸው፣ መንግሥት አንዳንድ ውሳኔዎቹን መልሶ እንዲያይ ብቻ ሳይሆን አንዳንዶችንም እንዲያነሳ ተገድዷል:: የአዲስ አበባና ኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላን እንዲቀር የተደረገው ወጣቶች በማኅበራዊ ሚዲያ በጠሩትና ባቀጣጠሉት ተቃውሞ እንደሆነ የሚዘነጋ አይደለም:: የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ጥያቄ በአገር ደረጃ ከፍ ብሎ የተነሳው፣ በቅርቡ ደግሞ በግልጽ እንደሚታየው በሚያስደንቅ ሁኔታ የጣና ሐይቅ ጉዳይ ትልቅ አጀንዳ የሆነው ወጣቶች በማኅበራዊ ሚዲያ ባቀጣጠሉት ንቅናቄ እንደሆነም ይታወቃል:: መንግሥት አካሄዱን እንዲገመግምና የተሐድሶ እርምጃ እንዲወስድ የተገደደውም በማኅበራዊ ሚዲያው በተቀጣጠለው ሕዝባዊ ንቅናቄ ምክንያት ነው:: ስለእስረኞች በመጮኽና ድጋፍ በማሰባሰብ፣ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በማጋለጥ፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ሥር የሰደደውን ሙስናና የመልካም አስተዳደር ችግር በማጋለጥ፣ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ክብረ በዓላት ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ ንቅናቄ በመፍጠር ወዘተ. ወዘተ. ይህ ድንቅ ሚሊኒያል ትውልድ ያልተነገረለት ታሪክ እየሠራ ይገኛል:: ለእኔ ጠያቂ ማኅበረሰብ ማለት ይህ ነው:: ከዚህ የበለጠ ለዴሞክራታይዜሽን እና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ የለም:: ይህ ትውልድ "ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቁ" የሚል ትውልድ አይደለም:: ይልቁንም ትውልዱ በሁሉም የአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በያገባኛል መንፈስ የሚሳተፍና የአገር ተስፋ የሆነ የኅብረተሰብ ክፍል ነው::

ብዙ ሰዎች፣ ኢትዮጵያውያን ማኅበራዊ ሚዲያውን ለጥላቻና ለአሉባልታ እያዋልነው ሲሉ ያማርራሉ:: በዚህ ምክንያት ራሳቸውን ከማኅበራዊ ሚዲያው ያገለሉ ሰዎች እንዳሉም ይታወቃል:: በእኔ እምነት የእነዚህ ሰዎች አስተያየት የተሳሳተና የአገራችን የፖለቲካ ባሕል ግምት ውስጥ ያላስገባ ነው:: ለዘመናት በፀረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የኖረን ኅብረተሰብ በአንድ ጀንበር ዴሞክራሲያዊ ማድረግ አይቻልም:: የዴሞክራታይዜሽን ጎዳና አባጣና ጎርባጣ ነው:: ዴሞክራታይዜሽን አንድ እርምጃ ወደፊት ሄዶ ሁለት እርምጃ ወደኋላ መመለስ፣ እንደገና ሦስት እርምጃ ወደፊት እያሉ የሚሄዱት ሒደት ነው:: መውደቅና መነሳት የሚጠይቅ እልህ አስጨራሽና ፈተና የበዛበት ጎዳና ነው - የዴሞክራታይዜሽን ጎዳና:: ስለሆነም በወጣቶቻችን በኩል የሚታየው እልህ፣ የእርስ በርስ ሽኩቻ፣ መካረር፣ አንዳንዴም በጅምላ የመነዳት አዝማሚያ በሒደት እየጠራና እየሰከነ እንደሚመጣ ማወቅ ያስፈልጋል:: የቀደሙት ትውልዶችና የፖለቲካ ሥርዓቶች የዴሞክራሲያዊ ባሕል እንዳላወረሷቸው እየታወቀ ወጣቶችን በፀረ ዴሞክራሲነት መክሰስ ፍትሐዊ አይደለም:: እንዲያውም በእኔ አስተያየት ይህ ትውልድ የዓለም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት በፈጠረለት ምቹ ሁኔታ ምክንያት የሌሎችን አገሮች (እና ሕዝቦች) ተሞክሮ እየወሰደ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቡንና አሠራሩንም እያዳበረ የመጣ ትውልድ ነው:: የተወሰኑ ግለሰቦች (እና ቡድኖች) በብሔረሰባዊና ሃይማኖታዊ ማንነት ስም ወጣቱን ለመጠርነፍና ለማሽከርከር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለጊዜው ውጤታማ ቢመስልም፣ በእኔ አስተያየት ወጣቱ እነዚህ አካላት እንደፈለጉ የሚጋልቡት አይሆንም:: እንዲያውም የእነዚህ ኃይሎች አካሄድ ችግር ያለበት መሆኑን ሲገነዘብ ጥያቄ ይጠይቃል፤ ይከራከራል፤ ይተቻል፤ ይቃወማል::

ዛሬ መንግሥት ወይም የተወሰኑ ቡድኖች መረጃን በሞኖፖሊ ይዘው ብዙሃኑን ሕዝብ አፍነው የሚገዙበት ሁኔታ የለም:: ሁሉም መጻፍና መናገር የሚችልበት ዘመን ነው:: ሁሉም ባለ "ሬዲዮ"፣ ባለ"ቴሌቪዥን" እና ባለ"ጋዜጣ" የሆነበት ዘመን ነው:: ዘመኑ በፈጠረው ቴክኖሎጂ ምክንያት ሁሉም ሰው ጋዜጠኛና ተንታኝ ነው:: ሰበር ዜናዎች የሚተላለፉት በማኅበራዊ ሚዲያው አማካይነት ነው:: የአገራችን ወጣቶች ይህን ዘመኑ የሰጣቸውን ፀጋ በሚገባ መጠቀም መጀመራቸው ለኢትዮጵያ ትልቅ ተስፋ ነው::

ሁለተኛው ተስፋ ሰጭ ነገር የተቃዋሚ ፓርቲዎች እየተዳከሙና እየሞቱ መምጣት ነው:: በአገራችን ባለፉት 26 ዓመታት በጣም ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ተቋቁመው ምንም ዓይነት የፖለቲካ ግብ ሳያሳኩ እንደተንኮታኮቱ ይታወቃል:: አንዳንዶች በአንድ ተሰሚነት ያለው ግለሰብ ዙሪያ የተደራጁ የመንደር ዕድር መሰል ስብስቦች ሲሆኑ፣ የሚበዙት ደግሞ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ፕሮግራም የሌላቸው ያኮረፉ ሰዎች የተሰባሰቡባቸው የብሶት ማኅበራት ነበሩ፤ ናቸውም:: እነዚህ ብሶት ያገናኛቸው ሰዎች ለዴሞክራታይዜሽንና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ደንቀራ ከመሆን የዘለለ ገንቢ ሚና ሊኖራቸው አይችልም:: ስለሆነም የእነዚህ የብሶተኛ መሰባሰቢያ ፓርቲ ተብየዎች መንኮታኮት የሰለጠነና ምክንያታዊ የፖለቲካ ባሕል እንዲፈጠር በር ይከፍታል፤ ከብሶት ይልቅ በሐሳብና በርዕዮተዓለም መሠረት ላይ የሚደራጁ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩም ዕድል ይሰጣል::

ካለፈው ዓመት ጀምሮ ሲካሄድ የቆየው ሕዝባዊ ንቅናቄ በግልጽ እንዳሳየው እነዚህ የብሶተኛ ስብስቦች የትኛውንም የኅብረተሰብ ክፍል አይወክሉም:: ለዚህ ነው ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን አቅጣጫ ከማስያዝና ከመምራት ይልቅ ተመልካች የሆኑት:: እንዲያውም ብዙዎቹ ብሶተኞች ተገርመው፣ ተደንቀውና እንቅስቃሴውን ምን ብለው እንደሚገልጹትም ተቸግረው ነበር:: ስለሆነም በእኔ እምነት የእነዚህ ስብስቦች ከፖለቲካ ሜዳው ላይ [በራሳቸው ችግር] ተጠራርጎ መጥፋት ተስፋ የሚሰጥ ፍጻሚ ነው::

ሦስተኛው ተስፋ የሚሰጠው ነገር መንግሥት የያዘው የፀረ ሙስና ትግል ነው:: በቅርቡ 60 የሚጠጉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና በድለላ ሥራ የተሠማሩ ሰዎች በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው እንደታሰሩ ይታወቃል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ እርምጃው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል:: ስለሆነም ሕዝብ ያማረረው መረን የለሽ የሙስና ዝቅጠት መልክ እየያዘ እንደሚሄድ እንጠብቃለን:: የአገርና የሕዝብን ንብረት የዘረፉ ሌቦች በሕግ ተጠያቂ እንደሚሆኑም ይጠበቃል:: ከዚህም በላይ መንግሥት ሕዝብ ያማረረውን የመልካም አስተዳደር ችግር ለማሻሻል እየሠራ በመሆኑ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የሚታየው የመልካም አስተዳደር ችግር መልክ ይይዛል ተብሎ ይጠበቃል:: በሌላ በኩል መንግሥት ኢትዮጵያዊነት መለምለም አለበት፣ የሕዝቦች ኅብረትና አንድነት መጠናከር አለበት፣ ስለዚህም የኢትዮጵያ ቀን መከበር አለበት ማለቱ እና ማክበር መጀመሩ ለእኔ ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው:: በዚህ ዓመት የተጀመረው አከባበር እየተሻሻለና ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እያሳተፍ እንደሚሄድም እምነቴ ነው:: መልካም አዲስ ዓመት!!

ዶ/ር ብርሃኑ አበጋዝ በኢሜል አድራሻቸው brieanteneh@gmail.com ላይ ይገኛሉ::

ይሁኔ አየለ (ዶ/ር)

# የጠላና የቢራ ግብግብ....

"ለምን ጠላ ጠላ፤ ለምን ጠጅ ጠጅ፣ ጠላትን መጋበዝ ቡን አርጎ ነው እንጅ::" ጠላትን ተኖ እስኪጠፋ መደብደቡን ባልደግፈውም፣ ጠላ ምርጥ የግባዣ መጠጥ መሆኑን በማመላከቱና ትንሽ ፈገግ በማስባሉ ግጥሟን መንደርደሪያ አድርጊያታለሁ:: ዛሬ የራሳችን የሆነውን ጠላን ከመጤው ቢራ ጋር እያወዳደርሁ ትንሽ ልበል:: ጠላ ለምን "ጠላ" እንደተባለ ምንም ያገኘሁት ነገር የለም:: ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ በአንድ የጥናት መድብላቸው ውስጥ፣ ጠላ ለምን "ጠላ" እንደተባለ ምንም የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ሲያብራሩ፣ "ጠላ የሚለው የተጸውዖ ስም የዘመን እርዝመት ትርጉማቸውን ከደበቀባቸው ስሞች አንዱ ነው:: ጠላ ለምን እንደተባለ ምክንያት ይኖረዋል:: ያን ምክንያት ግን ማወቅ አይቻልም" ይላሉ::

ስሙ እንዴት እንደወጣለት ባላውቅም ጠላ ምርጥ የባሕል መጠጣችን መሆኑን ግን በደንብ አውቃለሁ:: በአሁኑ ሰዓት ግን ቢራ የሚባል ዘመናዊ መጠጥ ተግዳሮት እያመጣበት ይገኛል:: ባሕላዊው ጠላ በከተሞች አካባቢ ንግሥናውን ለዘመናዊው ቢራ ያስረከበ ይመስላል:: ግን ለምን? በመጀመሪያ ስለ አልኮል ሳይንስ ትንሽ ልበል:: በዓለም ላይ ቁጥራቸው የበዛ አልኮሎች ይመረታሉ:: ለምግብነት የሚውለው ግን ኢታኖል ብቻ ነው:: ኢታኖል (Ethanol) የጥራጥሬ አልኮል በመባልም ይታወቃል:: ኢታኖል በሰውነት ውስጥ ሁለት እጣ ፋንታ አለው:: በህዋሶች ተቃጥሎ ወደ ኃይል ተለውጦ ለሰውነታችን ኃይል መስጠት ወይም በደም ሥር ሰርጎ ወደ አንጎል በመሄድ ስካር ማምጣት:: ጥቅሙ በጠጪው ምርጫ ይወሰናል:: ጠጪው ቀስ ብሎ ፋታ እየሰጠ ከጠጣ ወይም ከመጠጣቱ በፊት የጨጓራውን ግድግዳ በምግብ ከሞላ (ከመጠጥ በፊት መብላት ስካርን ይቀንሳል፤ ምክንያቱም አልኮል በብዛት ወደ ደም የሚሰርገው በጨጓራ ግድግዳ ስለሆነ ቦታውን በምግብ መድፈን ነው:: ከመጠጣትህ በፊት ብላ ነው መመሪያው) ከመጠጡ ኃይል በማግኘት ተጠቃሚ ይሆናል ማለት ነው::

ቢራም ሆነ ጠላ የሚመረቱት ይስት (yeast) በተባሉ ረቂቅ ተዋስያን ነው:: እነዚህ ባለ አንድ ህዋስ ፈንገስ (one-celled fungus) በሳይንሳዊ አጠራራቸው ሳካሮማይሲስ ሰረቪሴ ይባላሉ:: እነዚህ ሳካሮ ማይሲስ ሕይወታቸውን ለማቆየት ምግብ ያስፈልጋቸዋል:: ለዚህ ደግሞ ስኳር ዋና ምርጫቸው ነው:: ስኳሩን ወደኃይልና ወደ ኢታኖል ይለውጡታል:: ኃይሉን ተጠቅመው ኢታኖሉን እንደ ቆሻሻ ያስወግዱታል:: የሰው ልጅ፣ "ወይን ያስተፈስህ ልበ ሰብ" እያለ ልቡን የሚያስደስተው በዚህ በረቂቅ ተዋስያን ተረፈ ምርት ነው::

አልኮል ጠቃሚ ነው ወይስ ጎጂ ወደሚል ክርክር አልገባም:: አንድ በጥናት የተደገፈ ነገር ግን ማለት ይቻላል:: የተመጠነ (moderate) አልኮል የሚወስዱ ሰዎች አልኮል አብዝተው ከወሰዱትም ካልወሰዱትም በበሽታ ያለመጋለጥ ጥንካሬ አሳይተዋል (American dietary guideline, 2015)::

ስለ አልኮል ይህን መረጃ ካካፈልሁ ወደ ጠላና ቢራ ልዩነት ልዝለቅ:: ቢራና ጠላ አንድነትም ልዩነትም አላቸው:: አንድነታቸው በውስጣቸው ያለው አልኮል (ኢታኖል) አንድ ዓይነት ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ የምግብ ይዘታቸው (food content)፣ አመራረታቸውና አቀራረባቸው ነው::

ይስቶች (አልኮሉን የሚሠሩት ረቂቅ ተዋስያን) በራሳቸው ምርጥ የምግብ ምንጭ ከሆኑ ቆየት ብሏል:: ካምፓኒዎች እያመረቱ ጤናማ ምግብ በማለት በመሸጥ ላይ ናቸው:: የቢራና የጠላ ልዩነት እዚህ ላይ ይጀምራል:: ጠላ በውስጡ አልኮል ሠሪዎችን (ይስቶችን) ሲይዝ፣ በቢራ ውስጥ ግን ይስቶቹ በሙቀት እንዲሞቱ ቢራው ፓስቸራይዝድ ይደረጋል ወይም በረቀቀ ማጣሪያ ይወገዳሉ:: ይህ የሚሆነው ቢራው ጥርት ያለ እንዲሆንና እንዳያበላሹት ነው:: ጠላ ግን ከነ ሕይወታቸው ይዟቸዋል:: ስለዚህ ጠላ ሕይወት ያለው ምግብ ነው::

እነዚህ ረቂቅ ተዋስያን በውስጣቸው ብዙ ነገሮችን ይዘዋል:: በዋናነት ፕሮቲን፣ ቪታሚን (በተለይ የቪታሚን "ቢ" ዘሮችን) እና በጣም ጠቃሚ የሆኑ ማዕድናትን (ሴሊኒየምንና ክሮሚየም የተባሉትን):: ክሮሚየም የተባለው ማዕድን የደም ግሉኮስ እንዳይዋዥቅ ይረዳል:: ቪታሚን "ቢ" የሚባሉት ደግሞ ዋና ዋና የምግብ ክፍሎችን (ካርቦሃይድሬት፣ ፕሮቲን እና ቅባት) ተሰባብረው ኃይል እንዲሰጡ ያስችላሉ:: በተጨማሪም የዐይን፣ ቆዳ፣ ጸጉር፣ ጉበት፣ አፍ ጤንነታቸው እንዲጠበቅ ይረዳሉ:: ከዚያም ባለፈ የአንጎል ሥርዓታችን በደንብ እንዲሠራ ያግዛሉ:: የእያንዳንዱ ንጥረ ነገር ተዘርዝሮ አያልቅም:: እነዚህ ተዋስያን በተፈጥሮ ካላቸው ምላዕተ-ምግብ ባለፈ ለጠላው የዋለውን እህል ስለሚጠቀሙበት በተዘዋዋሪ ከእነሱ እናገኘዋለን:: እነዚህን ተዋስያን የያዘ ምግብ በተለይ ስጋ ለማይበሉ ሰዎች በጣም ጠቃሚ ነው - ከእነዚህ ተዋስያን የሚገኙት ፕሮቲንና ቪታሚን በብዛት የሚገኙት ከዶሮ፣ ከዐሣና ከስጋ ስለሆነ::

በተጨማሪ ጠላ፤ የጌሾን የምግብ በረከቶች የምናገኝበት ባሕላዊ መጠጣችን ነው:: ጌሾ በተክሎች ቅስም (phytochemicals) የተሞላ ነው:: ሁሉም ክፍሉ (ሥሩ፣ ግንዱ፣ ቅርፊቱ፣ ቅጠሉ፣ አበባውና ፍሬው) ለመዳኃኒትነት ጥቅም የሚሰጡ የኬሚካሎች ውሕድ የተሞላ ነው:: እንደሚታወቀው ተፈጥሮ የፈውስ ኃይሏን የደበቀችው በተክሎች ውስጥ ነው:: አንድ እውነታ ላንሳ፤ ተክሎች መራራ የሚሆኑት እራሳቸውን ከበሊታ (herbivorous) እና ከበሽታ አምጭ ተዋስያን አልያም ከአካባቢ መጥፎ ሁኔታ (ከጨረር ሊሆን ይችላል) ለመከላከል ነው:: የጌሾን መራራነት ከዚህ አኳያ ልናየው እንችላለን:: ጌሾ በሌሎች አገሮች ለመድኃኒትነት በብዛት ጥቅም ላይ ይውላል:: ፍሬውም "ቶኒክ" ለተባሉ መጠጦችና ሌሎች መሥሪያነት ይውላል:: እኛ የጌሾን ቱሩፋት የምናገኘው ከጠላና ከጠጅ ነው:: ጠላ ከጠፋ፣ ጌሾም ይጠፋል::

ስለጌሾና የሌሎች ተክሎች ለጤና ጠቃሚነት ትንሽ ባብራራ:: ተክሎችን ለመድኃኒትነት ስናውላቸው ጥቅም ላይ የሚውሉት በሳይንሳዊ አጠራር ሰከንደሪ ሜታቦላይት (secondary metabolite) ተብለው የሚጠሩትን የኬሚካል ውሕዶች ነው:: ቀደም ብለው ቪታሚኖች (A, B, C, D, E, K,) እንደ ንጥረ ምግብ አይታወቁም ነበር:: ዘግይተው ነው በምግብ ክፍል ውስጥ የተካተቱት:: የወደፊቱ ተደማሪ የምግብ ክፍሎች የሚሆኑት እነዚህ ሰከንደሪ ሜታቦላይት እንደሚሆኑ ምንም ጥርጥር የለኝም:: በጃፓን አገር ጥቅም ላይ የዋለ ሌላ የምግብ ክፍል አለ:: ይህም ምግበ-መድኃኒት (Functional food)፤ እንደ ምግብም እንደ መድኃኒትም የሚሠራ የምግብ ዓይነት ነው:: እነዚህ ምግቦች የያዙት ከላይ የገለጽሁትን የተክሎች ቅስም ነው:: ለምሳሌ ከምግብ መድኀኒት አንዱ አረንጓዴ ሻይ ነው::

ወይን (ቀዩ፤ ከወይን የሚጠመቀው) ለጤና ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ የፈረንሳይ እንቆቅልሽን (French paradox) ጨምሮ ለብዙ በሽታዎች ፍቱን እንደሆነ ብዙ ጥናቶች አረጋግጠዋል:: የወይን የጤና አጋርነት የመጣው በውስጡ ከያዘው ከወይኑ ፍሬ ውስጥ የሚገኝ ፖሊ ፌኖል (polyphenols) ከሚባሉ ከተክሉ የተክል ቅስሞች ነው:: በጠላ ውስጥ የጌሾን ቅስም እናገኛለን:: ባጠቃላይ፤ ከተክሎች የሚገኙ ነገሮችን ትኩረት አንንፈጋቸው::

ከላይ ከዘረዘርኩት ባሻገር፣ ጌሾ በጠላ ውስጥ ሁለት የታወቁ ጥቅሞች አሉት:: ለጠላው የተለየ ጣዕም ለመስጠትና ጎጅ የሆኑ በሽታ አምጭ ተዋስያን (ባክቴሪያዎች) እንደይራቡ ማድረግ ነው:: ከላይ የዘረዘረሁት የምግብ ጥቅም እንዳለ ሆኖ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታውን ከግምት በማስገባት ጠላን ልናጠናው፣ ልናሻሽለው፣ ልንጠብቀው የሚገባን ባሕላዊ መጠጣችን ይመስለኛል::

ይህን ስል፣ ጠላ እንከን የሌለው ጤነኛ መጠጥ ነው፤ ሁሉም ሊወስደው ይገባል እያልኩ አይደለም:: በንጽሕና ጉድለትና በአጠማመቅ ሂደት ጎጅ ነገሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ:: አንድ ነገር ልጠቁም፤ እህሎች በጣም አርረው በሚቆሉበት ጊዜ የተለያዩ ጎጂ ኬሚካሎች ሊፈጠሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ አክሪል አማይድ (Acryl amide) የተባለ የጤና ጠንቅ የሆነ ኬሚካል እህልን አሳርሮ በመቁላት የሚፈጠር ነው:: ሆኖም ግን ይህ ጥርጣሬ ነው:: ነገሩ በጥናት መረጋገጥ አለበት:: አመራረቱን በማዘመን ጠላን ለሌሎች የዓለም አገሮች ሲሳይ ማድረግ ይቻላል ብየ አስባለሁ::



ሜሪ ፈለቀ

# የማይጠራ ድፍርስ

"ለምን ዋሸሽኝ?" አልኳት በሆነው ሁሉ ግራ እንደተጋባሁ።

የቆዳዋ መገርጣት፣ የሰውነቷ ክሳት ከድሜዋ ሃያ ዓመታት አስረጅቲታል። ከድምጿ ውጪ ምኗም የኔን ውቧን ኤልሳን አትመስልም። ያለችበት ሁኔታ የከፋ መሆኑን ማወቅ ውስብስብ ነገር አልነበረም።

"አሳመምሺኝ ኤልሲ.... ...... ትተሽኝ ከሄድሽበት ጊዜ ይልቅ አሁን ጎዳሽኝ።" ያልኩትን ሰምታኛለች። እንዳልሰማ ችላ ብላ

"ልጅህ ነው? ቆንጆ ልጅ ወልደሃል!!" አለችኝ። በሩን ተደግፎ ሲያዳምጠን የቆየውን ዘሩባቤልን እያየች።

"አዎ ትንሹ ልጄ ነው።" አልኳት የማስበው እየተመሳቀለብኝ።

የባለቤቴ እህት ታማ እሷን ለማየት ነበር ከባለቤቴ ጋር ወደ ሆስፒታሉ የመጣነው። እና ከስቃዩ ጋር የተፋጠጠው ዘሩባቤል ከበሽተኛዋ ክፍል ወጥቶ ሲመለስ ክፍሉ ጠፍቶት ሲደናበር ነው የኤልሲ ክፍል የገባው። ልፈልገው ስወጣ አንደኛዋ ነርስ ጠቆመችኝና ስገባ ዐይኔ ያየውን ማመን አቃተው። የኔዋ ኤልሲ አልጋው ላይ ተጋድማለች። ከስድስት ዓመታት በፊት እየሳሳሁላት ነው ትታኝ የሄደችው።

ትታኝ ከመሄዷ አስቀድማ ስልኳንም ቤቷንም ለሁለት ሳምንታት ዘግታ በጭንቅ ካንገላታችኝ በኋላ ጠዋት ደውላ ቀጠረችኝ። ኤልሲን እወዳታለሁ! የመውደድ ልኬት ሚዛኑ እስኪያንስብኝ እወዳታለሁ። ድምጿን ስሰማ ከየትኛውም ሐሳቤ ወጣለሁ፣ ስትነካኝ የሲኦል አፋፍ ላይ ቆሜ እንኳን ቢሆን እስቃለሁ፣ ስትስመኝ እንኳን ያለሁበት ሁኔታና ቦታ ስሜም ይጠፋኛል። ስትስቅ 'እናትህ ሞታለች' እያለችኝ እንኳን ቢሆን እገለፍጣለሁ። ስታለቅስ 'የሞተው አባቴ ከሞት መነሳቱን' እየነገረችኝ ቢሆን እንኳን አለቅሳለሁ። ከኤልሲ ውጪ ያሉ ክስተቶች የሚወሰኑብኝ ለእርሷ በሚፈጥሩት ስሜት ነው። የቀጠረችኝ ቀን ጠዋት የልቤ ንግሥት ፀሐይን የሚያስንቅ የፊቷ ፀዳል ከስሞ እንዳቀረቀረች

"ላገባ ነው!" አለችኝ። አሳቀኝ! ቀልድ እንደተነገረው ሰው ሳቅኩኝ።

"መቼ ነው የምታገቢኝ?" አልኳት አገጯን በጣቴ ቀና አድርጌ ዓይኖቿን እየፈለግኩ።

"እየቀለድኩ አይደለም። ዳዊትን ላገባው ነው። ከዚህ በተሻለ ከአገር ውጪ የተሻለ ሕክምና የማግኘት ዕድል አለኝ። ይዞኝ ሲሄድ፣ ሙሉ የሕክምናውን ወጪ ሊሸፍንልኝ ቃል ገብቶልኛል።" የቃሏ ምሬት የእውነቷን እንደሆነ ያስታውቃል። ሕልምም መሰለኝ። የኔ ኤልሲ ከእኔ ሌላ ባል አታገባም።

"ዳዊት ማነው? እንዴት? እኔስ? ቆይ ለምን?"

የዳዊት ማንነት ጠፍቶኝ አልነበረም። ዳዊትን ልታገባው መወሰኗን እስከነገረችኝ ሰዓት ድረስ ዳዊት ማለት ለኔ ከአገር ከመውጣቱ በፊት ይከታተላት የነበረ ዶክተር ነበር። ልታገባው መሆኑን ካወቅኩ በኋላ አምርሬ የምጠላው ሰው ሆነ። ኤልሲን አጥቼ ለኖርኳቸው ሕይወት አልባ ቀናት እሷን መውቀስ አይሆንልኝም እሱን እንጂ! ዓይኖቼን አላየቻቸውም።

"ተወኝ! ልታገኘኝ አትሞክር። አትረብሸኝ።" ብላኝ በተቀመጥኩበት ጥላኝ ሄደች። ብቻዬን ሳይሆን ዓለምም አብራኝ የደነዘዘች፣ የፈዘዘች፣ የደነገጠች መሰለኝ። ኤልሲ የኔ ብቻ ሳይሆን የዓለም ፍቅረኛ የሆነች ይመስል ዓለም ሁሉ አብሮኝ ዘጭ ብሎ የወረደ መሰለኝ። ሁሉም ነገር ሕይወት አልባ ሆነብኝ። ኤልሲን ላገኛት በሞከርኩ ቁጥር ትርቀኝ እና እሷን የማገኝበትን መንገድ መዝጋት ጀመረች።

"እርሳኝ!" ትለኛለች።

ወድጄ ነው እንዴ ጥላኝ የሄደችን ልጅ የማስባት? አብራኝ ከእናቴ ማሕፀን የወጣች ይመስል ብቻዬን ራሴን ማሰብ አቃተኝ። ኤልሲ ያልነበረችበትን የዘመኔን ቀናት ላስታውስ ተቅበዘበዝኩ።

መች ነበር የማውቃት? ራሴን ሳውቅ ኤልሲንም አውቃታለሁ። ሰፋፊ ክፍተት ያለውን የኛንና የእነሱን ቤት በሚለየው የእንጨት አጥር መሃል ወደኛ ጊቢ ስትሾልክ፣ እናቴ ለሁለታችንም የሚበላ ሰጥታን ስንጣላ፣ አባቷ እኔን ከፊት እሷን ከኋላ በሞተር ሳይክላቸው ጭነውን ሲነዱ.... ኤልሲን ሁሌም ነው የማውቃት።

ምን ቀን ነው የወደድኳት?

አብረን ትምህርት ቤት ስንሄድ? ወንድ የጻፈላትን ደብዳቤ አስነብባኝ ስቀና? ልብስ ሊገዛላት አብረን ሄደን ስትለካ በልብስ ከልያት ቆሜ ልብሷን ስታወልቅ ሰርቄ ገላዋን ያየሁት ቀን? ለክረምት ክፍለ አገር ሄዳ በናፍቆት የነደድኩኝ ወቅት? 'ወድሻለሁ!' ስላት ፍንክንክ ብላ እየሳቀች 'ምን አድርጌህ ትጠላኛለህ?' ብላ ያበሸቀችኝ እለት? የማትሪክ ውጤት አምጥተን በደስታ አመሻኝታ ከንፈሬን የሳመችኝ እለት? አንድ ዩኒቨርስቲ ደርሶን በጉዞ አመሻኝተን አንድ ክፍል ስናድር ሰውነታችን የተጋባ እለት?

በአንዱ ቀን ይሆናል የወደድኳት ወይም በሁሉም ቀናት ነበር እወዳት የነበረው። እሷ ያልነበረችበት የሕይወት ዘመን የለኝም። ስትስቅ ገልፍጫለሁ፣ ስታዝን አልቅሻለሁ፣ ስትታመም አጣጥሪያለሁ።

ተመርቀን ወደቤታችን የተመለስን ሰሞን ኤልሲ ድንገት ታመመች። ከልቧ ወደ ሰውነቷ ደም የሚረጨው የደም አዘዋዋሪ ቱቦ ተዘግቷል ተባለች። እጅግ በፈጠነ ቅፅበት ብዙ ለውጦች ተከወኑ።

የአካሏ ለውጥ፡- ተበላሽ የተባለው የደም ቱቦ በባእድ ፕላስቲክ ተቀየረ። ይሄን ተከትሎ ኤልሲ ብዙ ነገር ማድረግ እንደማትችል ተነገራት። ሙቀት የበዛበት አካባቢ መቆየት፣ የበዛ መደሰት፣ የበዛ ሐዘን፣ ወሲብ ማድረግ፣ ማርገዝ ወይም መውለድ.... እንደማትችል አወቀች። እነዚህ ነገሮች ራስን ከመሳት እስከ ሞት የሚያደርሷት ክስተቶች ነበሩ።

በአንዱ ቀን ማታ ከስራ ወጥቼ ይዣት ወጣሁ። የናፈቀኝ ከንፈሯን ሳምኩት፣ መለሰችልኝ፣ ስትስመኝ ምንም አላስታውስ አይደል? ተንገብግቤ ጎረስኳት ተመሳሳዩን አደረገች። ከዛ በኋላ የተፈጠረውን አላስታውስም። እጄ ላይ ራሷን ስታ መውደቋን አየሁ።

ከቤተሰቦቿ ቤት ወጥታ ቤት በተከራየች ሰሞን እቤቷ አልጋዋ ላይ ቁጭ ብዬ መፅሀፍ አነብላታለሁ። ክንዴን ተንተርሳ እያዳመጠችኝ እጆቿን ልብሴን ከላዬ እንዲገፉላት ላከቻቸው። እጇን በቀስታ ከልክዬ አገላብጬ ከሳምኳቸው በኋላ እንድታቆም በአንደኛው እጄ ያዝኳት። ወደጆሮዬ ተጠግታ

"ምንም አልሆንም'ኮ። እሺ በለኝ ስሞትልህ...... ናፍቀሽኛል።" ሹክሹክታዋ ይነዝራል። እጇን ለቀቅኩላት። እኔ ማንበቤን ቀጠልኩ እንደማትሰማኝ አውቃለሁ። በአንደኛው እጇ ስትነካካኝ ማንበቤን የት ቦታ እንዳቆምኩት አላስታውስም። ሲኦል እየታየኝ መሳቄን ወደድኩት። ኤልሲ እንደራበችኝ እንጂ ሌላ ማሰብ እንደነበረብኝ አልተገለጠልኝም። ራቁቷን አልጋው ላይ ተንጋላ ከነፍሷ እየፈገገች ታየኛለች። እስከየትኛው ቅፅበት ትንፋሿን እንደሰማሁት አላስታውስም።

"ፍቅሬ እንዴት ላድርግሽ? እርበሽኛል።" አልመለሰችልኝም። ትንፋሿ ደክሟል። ራሷን ስታለች። ከነዚህ ለውጦች በኋላ ኤልሲ በሆነው ባልሆነው የሚከፋት ነጭናጫ እየሆነች መጣች።

ኤልሲን ይበልጥ በፍቅር አበድኩላት። አንጀቴ ስፍስፍ ይልላት ጀመር። ለምንም ሰዓት ትቻት ባልሄድ ደስ ይለኛል። ያልገባኝ ነገር አልነበረም። ሁሉም ለውጥ ግልፅ ሆኖ ይገባኛል። ግን የፍቅሬ መጨመር የማይካድ ለውጥ ነው።

ኤልሲን ከነዚህ ሁሉ ለውጦች በፊት አውቃታለሁ። ዛሬ እንደጨው እጄ ላይ ይቀልጣል ብዬ የምሳቀቅበት ገላዋ ትናንት የእርካታዬ ጥግ ነበር። ብቻዬን የማውቀው የኔ ብቻ!!! ዓመት እንደቀልድ ነጎደ። በዚህ ወቅት ነው ልታገባ እንደሆነ የነገረችኝ። ብዙም ሳትቆይ ከሀገር ወጣች። ነፍሴም ከስጋዬ ተፋታ!! አብሯት ከሃገር ወጣ። በቀረው ስጋዬ አገባሁ፣ ሁለት ልጆች ወለድኩ እናም ዛሬ ሆነ።

ይኸው ከኤልሲ ጋር ........... ሆስፒታሉ ውስጥ!!

"ስለማፈቅርህ!! እመነኝ ከራሴ ይልቅ ላንተ ስላደላሁ ነው። ባልተውህ አትተወኝም። የራስህን መኖር ገድለህ ከኔ ጋር ስታጣጥር ስድስት ዓመታት ያልፉ ነበር። እንደዛሬው ደስታህንም ፍሬህንም አታይም ነበር።" አለችኝ የሆስፒታሉ አልጋ ላይ በአፍንጫዋ ነጭ ቱቦ ገብቶ፣ በፕላስቲክ ያለ ደም ከአናቷ ተንጠልጥሎ እንደተጋደመች።...... በዐይኖቿ ጠርዞች እንባዋ በቀጭኑ እየወረደ።

ኤልሲ ልታገባ አልነበረም። ኤልሲ አላገባችም። ኤልሲ እኔን ማፍቀሯን አቁማ አታውቅም።

ፀፀትን አከናነበችኝ። ምን ማሰብ እንዳለብኝ፣ በማን መፍረድ እንዳለብኝ፣ የቱ ልክ እንደነበር...... ድብልቅልቅ አለብኝ።

ጨርሰናል!!

*ሜሪ ፈለቀን በኢሜይል አድራሻዋ meazafeleke23@yahoo.com ሊያገኙት ይችላሉ።*



እስክንድር መስፍን

# የሞባይል ባንክ አገልግሎት
# እና ስጋቶቹ

የሞባይል ባንክ አገልግሎት ማለት የተንቀሳቃሽ ስልኮችን በመጠቀም መሠረታዊ የሆኑ የባንክ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስችል የቴክኖሎጂ አገልግሎት ነው:: አንዳንድ የሞባይል ባንክ አገልግሎቶች የራሳቸው የሆነ መጠቀሚያ ሶፍትዌር ሲኖራቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ የሞባይል ኔትዎርክ ካገኙ በአጭር ቁጥር መስመር በመደወል የሚገኙ አገልግሎቶች ናቸው:: በሶፍትዌር የሚደረግ የሞባይል ባንክ አገልግሎት ዘመናዊ የሆኑ ስልኮችን የሚፈልግ ሲሆን መጠቀሚያ ፕሮግራሙ ደግሞ በባንኩ የለማና የተመሰከረለት መሆን ይገባዋል:: በሶፍትዌር የታገዘ የሞባይል ባንክ አገልግሎት ማንኛውንም የባንክ አገልግሎት ለማግኘት ግዴታ የኢንተርኔት አገልግሎት ስልኩ ላይ መኖር አለበት:: ሶፍትዌር አልባ የባንክ አገልግሎት ግን በማንኛውም ዓይነት ስልክ ላይ ምንም ዓይነት የኢንተርኔት አገልግሎት ሳይፈልግ ያሠራል:: የሶፍትዌር አልባ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ለመጠቀም የሞባይል ቁጥራችን በባንኩ የሞባይል ባንክ አገልግሎት ላይ ማስመዝገብ ይጠይቃል::

በሞባይል የሚደረጉ የባንክ አገልግሎቶች ሊያጠቃልሉ የሚችሉት መሠረታዊ የባንክ መረጃ፣ ተቀማጭ ሒሳብ ማውቅ፣ ምንዛሬ ማውቅ እንዲሁም ክፍያ መፈፀም እና ብር የማስታላለፍ አገልግሎት ናቸው:: ይህ አገልግሎት ካገር አገር የሚለያይ ቢሆንም ኢትዮጵያን ጨምሮ በበርካታ አገሮች ተግባራዊ ሆኖ በማገልገል ላይ ነው::

የሞባይል ባንክ አገልግሎት ከባንክ አገልግሎት ሰጪዎች እይታ አንጻር ስናየው በየባንኩ ቅርንጫፍ የሚኖረውን የደምበኛ ብር ለመላክ፣ ብር ለማውጣት፣ የሒሳብ መረጃ ለማግኘት የሚመጡ የአገልግሎት ጠያቂዎችን ቁጥር የሚቀንስ ሲሆን ባንኮችም ተጨማሪ ቅርንጫፍ ለመክፈት የሚያወጡትን ወጪም ይቀንስላቸዋል:: የሞባይል ባንክ ተጠቃሚ የሆነ ደንበኛ በእጁ የካሽ ብር ማግኘት ከፈለገ ግን ግዴታ የባንክ ቅርንጫፎችን፣ የባንክ ኤቲኤምችን ወይም ወኪል ባንኮችን መጎብኘት ይጠበቅበታል::

በሞባይል ባንክ አገልግሎት ላይ በተደረገ ጥናት በዓለም ላይ ካሉ አገራት ውስጥ ደቡብ ኮሪያ ቁጥር አንድ የሞባይል ባንክ አገልግሎት




ተጠቃሚ ስትሆን ሆንክ-ኮንግ እና ሲንጋፖርም ይጠቀሳሉ:: አፍሪካን ካየን በሞባይል ባንክ አገልግሎት ደቡብ አፍሪካ ቀዳሚውን ስፍራ ትይዛለች::

በአገራችንም አብዛኛዎቹ ባንኮቹ የሞባይል ባንክ አገልግሎት እንደሚሰጡ ይታወቃል:: ከእነዚህ ውስጥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኅብርት ባንክ፣ ዳሸን ባንክ፣ አቢሲንያ ባንክ በዋናነት የጠቀሳሉ:: ሌሎችም የግል ደርጅቶች እንደ ሄሎ ካሽ እና ኤም-ብር በዋነኝነት ገቢያቸውን በሞባይል ባንክ አገልግሎት ላይ የመሠረቱ ናቸው::

## የኢንተርኔት ባንክ አገልግሎት

የኢንተርኔት ባንክ ከሞባይል ባንክ የሚለየው አገልግሎቱን ለማግኘት በቀጥታ በባንኩ ድረ-ገጽ ላይ በመሄድ ከባንኩ የተሰጠንን የሚስጥር ስምና ድብቅ ማለፊያ ቃል በመጠቀም የምናገኘው አገልግሎት በመሆኑ ነው:: ይህን አገልግሎት ከማንኛውም ኢንተርኔት አገልግሎት ሊያገኝ ከሚችል ኮምፒውተር ወይም ላፕቶፕ ላይ መጠቀም ይቻላል:: እንደ ሞባይል ባንክ አገልግሎት ሁሉ ይህ አገልግሎትም ብር ለማስተላለፍ፣ የሒሳብ ቀሪን ለማወቅ እና ሌሎች መረጃዎችን ከባንኩ ለማግኘት ያገለግላል::

## የኤሴምኤስ ባንክ አገልግሎት

ይህ የሞባይል ባንክ አገልግሎት ዓይነት ሲሆን፣ የዚህ የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች የባንክ ሒሳብ ወጪና ገቢ መረጃዎችን ለባንኩ ተጠቃሚ ለማድረስ ያገለግላል:: በዚህ አገልገሎት ምንም ዓይነት ብር ለማንቀሳቀስ እና ሒሳብ ነክ የሆኑ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ አይቻልም::

## የሞባይል ባንክ እና ተግዳሮቶቹ

በአሁኑ ሰዓት በአገራችን እየተጠቀምንበት ያለው የሞባይል ባንክ አገልግሎት ብዙ ተግዳሮቶችን አልፎ እዚህ የደረሰ ቢሆንም አሁንም አብዛኛዎቹ ባንኮች የሚከተሉት ችግሮች ያጋጥሟቸዋል::

➢ ***የስልክ መሣሪያዎች በየጊዜው መራቀቅ***፦ የሞባይል ቴክኖሎጂ አመራቾች እርስ በራሳቸው ገበያውን ለመቆጣጠር የሚያድጉት የፈጠራ አብዮት የዚህን የሞባይል ባንክ አገልግሎት ላይ እንከን እየፈጠረ ይገኛል:: ምክንያቱም በዚህ የሞባይል አብዮት ሂደት ባንኮችም ያላቸውን የሞባይል ባንክ አገልግሎት በአብዮቱ ውስጥ መለወጥ የግድ ስለሚላቸው ነው::

➢ ***ደኅንነት***፦ በአሁኑ ወቅት ለሞባይል ባንክ አገልግሎት የምንጠቀምባቸው ስልኮች በጣም የረቀቁ ነገር ግን ለተጠቃሚዎች ቀላል የሆኑ ሲሆኑ እነዚህ ስልኮች በማንኛውም ቦታ ልናስቀምጣቸው እና ልንረሳቸው ስለምንችል፣ እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚዎች በሦስተኛ ሰው እጅ ሊገቡ ስለሚችሉ የተጠቃሚውን የባንክ ሒሳብ አደጋ ላይ ይጥላሉ::

➢ ***የተጠቃሚ አስተሳሰብ***፦ አብዛኛዎቹ ባንኮች ብዙ ሚሊዮን ብር አውጥተው የሞባይል ባንክ አገልግሎት ቢጀምሩም እንደታሰበው ብዙ የአገልግሎት ተጠቃሚ ማግኘት እንዳልተቻለ ባንኮቹ ይናገራሉ:: ስለሆነም ይህንንም የባንክ አገልግሎት ወደ ተጠቃሚ ለማድረስ ብዙ የማስተዋወቅያና የማስተማሪያ ሥርዓት በባንኮች አማካይነት መዘርጋት ያስፈልጋል::

*እስክንድር መስፍን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካሪ ናቸው:: በኢሜይል አድራሻው emesfin@askiibez.com ይገኛሉ::*

# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ




በመጽሐፉ
የኢትዮጵያ ፖለቲካ
ችግሮች
ተተንትነዋል

የመፍትሔ ሐሳቦች
ተጠቁመዋል

# PAGUMEN TOUR AND TRAVEL S.C

## ጳጉሜን አስጎብኚ እና የጉዞ ወኪል አክሲዮን ማኅበር

+251-118 22 69 29 / +251-909 56 59 59
E-mail:info@pagumen.com
www.pagumen.com

ጳጉሜና የኢትዮጲያ መልክዐ እና ድርሳን!!!

With paguumen, Ethiopia narrated truly!!!

